የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ መጋቢት ፫ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No.28
ADDIS ABABA 12th, March , 2025

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷/፪ሺ፲፯

የባንክ ሥራ አዋጅ.....................................ገጽ ፲፯ሺ፯፻፸

**Content**

Proclamation No. 1360/2025

Banking Business Proclamation..........Page 17770

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷/፪ሺ፲፯

## ስለባንክ ሥራ የወጣ አዋጅ

ባንኮች ገንዘብ በማሰባሰብ እና ወደ ተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች በማሰራጨት ለኢኮኖሚ ልማት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው እና በሀገሪቱ ኢኮኖሚ የክፍያና የሒሳብ ማወራረድ ሥርዓት ውስጥ ቁልፍ ቦታ የሚይዙ በመሆኑ፤

በጥንቃቄ በተዘጋጀ የሕግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ መሠረት የባንክ ዘርፍን ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ማድረግ የዘርፉን ተወዳዳሪነትና ውጤታማነት በማሻሻል ለዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ የሚታመን በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 1360/2025

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR BANKING BUSINESS

**WHEREAS,** banks play an important role in economic development through mobilization of funds and channeling same to various sectors and occupy a central place in the payment and settlement system of the country's economy;

**WHEREAS**, opening the banking sector for foreign investment with a carefully designed legal and regulatory framework, is believed to improve competitiveness and efficiency of the sector and contribute to sustainable economic growth;

አዋጭነቱ ያበቃ እና መልሶ አዋጭ የመሆን ተስፋ የሌለው ተደርጎ ለሚቆጠር ማንኛውም ባንክ ከፍተኛ የሥርዓት መናጋትን እና ኪሳራን በማያስከትል መልኩ እልባት ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ በርካታ የተለያዩ ሥልጣኖችን እና አማራጮችን ለእልባት ሰጪ ባለሥልጣን አካሉ ማለትም ለብሔራዊ ባንክ የሚሰጥ ውጤታማ የእልባት ሥርዓት መኖር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

**WHEREAS,** it is found essential to have an effective resolution regime that provides the resolution authority that is, National Bank with a broad range of powers and options needed to resolve a bank considered no longer viable and has no reasonable prospect of becoming so in a manner that does not cause severe systemic disruption and loss;

የባንክ ሥራ በአግባቡ ካልተመራ በፋይናንስ ሥርዓቱና በማክሮ ኢኮኖሚው ላይ ያለመረጋጋትን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ፤

**WHEREAS**, the banking business, if not properly managed, would have the potential to generate financial system and macroeconomic instability;

የፋይናንስ ሥርዓትና የማክሮ ኢኮኖሚ ያለመረጋጋት ሕዝብ እና መንግሥትን ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል በመሆኑ፤

**WHEREAS**, the cost of financial system and macroeconomic instability to the general public and the Government is significant;

የባንክ ዘርፍ ፈቃድ አሰጣጥንና ቁጥጥርን በሚመለከት አሁን ካለው እና ወደፊት ከሚኖረው የዘርፉ ለውጥ ጋር የሚጣጣም የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ በመዘርጋት የባንክ ሥራን ደህንነት፣ ጤናማነትና መረጋጋት ቀጣይነት ባለው መልኩ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

**WHEREAS,** it is found essential to continually ensure safety, soundness and stability of the banking business by having a comprehensive legal framework for the licensing and supervision of the banking sector which is well aligned with the current and emerging development of the sector;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ **"ግዢ"** ማለት የአንድ ባንክ በሌላ የሀገር ውስጥ ወይም የውጭ ባንክ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መገዛት ወይም መጠቅለል ነው፤

፪/ **"የወኪል የባንክ አገልግሎት"** ማለት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚወሰነው መሠረት ሕጋዊ የውክልና ስምምነት በመፈጸም በወኪል በኩል የሚቀርብ የባንክ አገልግሎት ነው፤

፫/ **"ሀብት እና ዕዳ ማስተላለፍ"** ማለት ፋይናንስ ነክ የሆኑ እና ያልሆኑ ሀብቶችን እና ዕዳዎችን ጨምሮ የአንድን ባንክ የባንክ ሥራ ኢትዮጵያ ውስጥ በባንክ ሥራ ለተሰማራ ሌላ ባንክ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማስተላለፍ ነው፤

፬/ **"የንብረት አስተዳደር ተቋም"** ማለት አዋጭ ላልሆነ አንድ ባንክ እልባት ከመስጠት ጋር በተያያዘ ችግር ያለባቸውን የባንኩን ንብረቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲገዛ፣ እንዲያስተዳድር እና እንዲያስወግድ በመንግሥት ወይም በግሉ ዘርፍ የሚቋቋም ተቋም ነው፤

፭/ **"ባንክ"** ማለት የባንክ ሥራ ለመሥራት ከብሔራዊ ባንክ ፍቃድ የተሰጠው በግል ወይም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ባንክ፣ የውጭ ሀገር ባንክ ተቀጥላ ወይም የውጭ ሀገር ባንክ ቅርንጫፍ ነው፤

## PART ONE

## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Banking Business Proclamation No.1360/2025"

**2. Definitions**

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1/ **"Acquisition"** means a full or partial purchase or takeover of a bank by another domestic or foreign bank;

2/ **"Agent Banking Service"** means the provision of banking service through an agent, under a valid agency agreement, as prescribed in National Bank Directive;

3/ **"Assets and Liabilities Transfer"** means full or partial transfer of banking business including financial and non-financial assets and liabilities of a bank to another bank operating in Ethiopia;

4/ **"Asset Management Vehicle"** means an entity established by the Government or private sector for the purpose of acquiring, managing, and disposing some or all of the problem assets of a bank which is no longer viable, as part of its resolution;

5/ **"Bank"** means a private or state owned bank, a foreign bank subsidiary or a branch of a foreign bank licensed by the National Bank to undertake banking business;

፮/ "የባንክ ሥራ" ማለት የሚከተሉትን ሥራዎች ያጠቃልላል፡-

ሀ/ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ወይም ባለው አሰራር ተቀባይነት አለው ብሎ በፈቀደው የገንዘብ መቀበያ ዘዴ ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ የመቀበል፤

ለ/ የባንክ ሥራ በሚሠራው ሰው ሒሣብና ኃላፊነት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ የተመለከተውን ገንዘብ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ወይም ተቀባይነት ባለው አሠራር ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በብድር ወይም ንብረትን ማዕከል ባደረገ ፋይናንሲንግ ወይም በኢንቨስትመንት ላይ የማዋል፤

ሐ/ በገንዘብ መልክ ያልተቀረጸ ወርቅና ብር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ የመግዛትና የመሸጥ፤

መ/ በባንኮቹ በራሳቸውም ሆነ በደንበኞቻቸው ስም ለሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ሰዎች ገንዘብ የማስተላለፍ፤

ሠ/ በገንዘብ ማስከፈያ፣ በሐዋላና በተስፋ ሰነዶች እንዲሁም በሌሎች የዕዳ ማረጋገጫ ሰነዶች አማካኝነት በቅናሽ የማበደርና የማስተላለፍ፣

ረ/ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት፤

ሰ/ የወኪል የባንክ አገልግሎት፤

ሸ/ ዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎቶች፤

ቀ/ ዋስትና መስጠት፤ እና

በ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል "ሀ" እስከ "ቀ" በተመለከቱት ተግባራት የተሰማራ ባንክ እንዲሠራቸው በብሔራዊ ባንክ የሚፈቀድለት በተለምዶ እንደ ባንክ ሥራ የሚታወቁ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን፡፡

6/ **"Banking Business"** means any business that consists of the following activities:

a) receiving deposits from the public through means that National Bank, through a Directive or Practice, has declared to be an authorized manner of receiving funds;

b) using the funds referred to under paragraph (a) of this Sub-Article, in whole or in part, for the account and at the risk of the person undertaking banking business, for loans, asset based financing or investments in a manner determined by National Bank Directive or practice;

c) the buying and selling of gold and silver bullion and foreign exchange;

d) the transfer of funds to other local and foreign persons on behalf of the banks themselves or their customers;

e) the discounting and negotiation of promissory notes, drafts, bills of exchange and other evidence of debt;

f) interest free banking service;

g) agent banking service;

h) digital financial services;

i) issuance of guarantee; and

j) any other activity recognized as customary banking business, which a bank engaged in the activities described from paragraph (a) to (i) of this Sub-Article, may be authorized to undertake by the National Bank.

፯/ **“የባንክ ቡድን”** ማለት ብሔራዊ ባንክ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲል ከግምት በሚያስገባው መሠረት የአንድ ባንክ የሀገር ውስጥ እንዲሁም የውጭ ባንክ ሁሉም ተቀጥላዎች፣ ቅርንጫፎች፣ አጋሮች እና ሆልዲንግ ኩባንያውን በሙሉ የሚያጠቃልል ሲሆን የሚገኙበት ቦታ የትም ሊሆን ይችላል፤

፰/ **“ተጠቃሚ የሚሆነው ባለቤት”** ማለት ደንበኛን ወይም አንድን ሒሳብ በፍጹም ባለቤትነት የሚይዝ ወይም የሚቆጣጠር ግለሰብ፣ ግብይት በስሙ የሚካሄድለት ሰው ወይም አንድን በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል ወይም ከሕግ የመነጨ አደረጃጀትን ለመቆጣጠር ሥልጣን ያለው ሰው ነው፤

፱/ **“የሽግግር ባንክ”** ማለት የአንድን የወደቀ ባንክ ሀብት እና ዕዳዎች እንዲረከብ እና ባንኩ በግዢ እና በርክክብ ለሌላ ባንክ እስኪተላለፍ ወይም ንብረት አጣሪ እስከሚረከበው ድረስ የባንኩን ወሳኝ እና አዋጭ ሥራዎች እንዲያስቀጥል በገንዘብ ሚኒስቴር የሚቋቋም ጊዜያዊ ተቋም ነው፤

፲/ **“በቂ የካፒታል ምጣኔ”** ማለት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ባንክ የተስተካከለ ካፒታል የስጋት ተጋላጭነት መጠንን ታሳቢ በማድረግ ከተሰላ የባንኩ ሀብት አንጻር በመቶኛ የሚገለጽ ምጣኔ ነው፤

፲፩/ **“የካፒታል ወጪ”** ማለት በመቋቋም ላይ ባለ ባንክ የሚከፈል የቅድሚያ ወጪ፣ የአክሲዮን ሽያጭ ኮሚሽንና የድለላ አገልግሎት ክፍያ እንዲሁም ቋሚ ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት በሌለው ንብረት መልክ የማይታይ ሌላ ወጪ ነው፤

7/ **“Bank Group”** means both domestic and foreign bank and all of its subsidiaries, branches, affiliates and holding company, wherever located, that the National Bank determines to be taken into account for the purpose of implementing this Proclamation;

8/ **“Beneficial Owner”** means any natural person who ultimately owns or controls a customer or an account, the person on whose behalf a transaction is being conducted, or the person who ultimately exercises effective control over a legal person or arrangement;

9/ **“Bridge Bank”** means a temporary institution established by the Ministry of Finance on interim basis, to acquire assets and assume liabilities of a failed bank and continue critical and viable operation until the bank is transferred to another bank through purchase and assumption or until taken over by the liquidator;

10/ **“Capital Adequacy Ratio”** means the ratio expressed as a percentage of the adjusted capital base to the risk weighted exposures as determined by National Bank Directive;

11/ **“Capitalized Expenditure”** means preliminary expenses, share selling commission and brokerage fees paid by a bank under formation, and any other item of expenditure not represented by tangible assets;

፲፪/ **"ዋና ሥራ አስፈጻሚ"** ማለት በማንኛውም ሥያሜ የሚጠራ ቢሆንም የአንድን ባንክ የዕለት ተዕለት ሥራዎች በዋና ኃላፊነት የመምራት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤

፲፫/ **"የንግድ ሕግ"** ማለት የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፫/፪ሺ፲፫ ነው፤

፲፬/ **"ቀውስ"** ማለት የአንድ ባንክ የፋይናንስ ሁኔታ ከፋይናንስ ጤናማነት መለኪያ መስፈርቶች አኳያ በከፍተኛ ደረጃ እያሽቆለቆለ መምጣት ሆኖ ይህም ባንኩ ዕዳውን የመክፈል አቅም እንዳይኖረው ወይም የተረጋጋ እንዳይሆን ሊያደርገው የሚችልበት እና አጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓቱን ሊያውክ የሚችልበት ዕድል የመፈጠር ሁኔታ ሲስተዋል እና ቀውስ ውስጥ ያለ ባንክ እንደሆነ በብሔራዊ ባንክ ውሳኔ ሲሰጥ ነው፤

፲፭/ **"የቀውስ ሁኔታ አመራር"** ማለት አንድን የቀውስ ሁኔታ ለመፍታት እና የፋይናንስ መረጋጋትን መልሶ ለመገንባት በብሔራዊ ባንክ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚወሰዱ የተቀናጁ እርምጃዎች እና ምላሾች ናቸው፤

፲፮/ **"ዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎት"** ማለት በዲጂታል መንገዶች የሚሰጡ የባንክ አገልግሎቶች ማለትም ብድር፣ ቁጠባ፣ ገንዘብ መላክ፣ ክፍያ እና ሌሎች መሰል ተዛማጅ የባንክ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፤

፲፯/ **"በቀጥታ የተያዘ የአክሲዮን ድርሻ"** ማለት አንድ ሰው በቀጥታ በራሱ ስም ወይም ከባለቤቱ ወይም ለአካለ መጠን ካልደረሰ በአንደኛ ደረጃ ከሚዛመደው ሰው ጋር በጋራ በአንድ ባንክ ውስጥ የያዘው የአክሲዮን ድርሻ ወይም ሌሎች ብሔራዊ ባንክ በሚወስናቸው ሁኔታዎች የተያዘ የአክሲዮን ድርሻ ነው፤

12/ **"Chief Executive Officer"** means a person, by whatever title that person may be referred to, who is primarily responsible for the day-to-day management of the affairs of a bank;

13/ **"Commercial Code"** means Commercial Code of Ethiopia Proclamation No. 1243/2021;

14/ "**Crisis**" means significant deterioration of a bank's financial condition in respect of financial soundness indicators in a manner threatening its solvency or stability and could potentially disrupt the broader financial system as determined by National Bank;

15/ **"Crisis Management"** means the coordinated actions and responses taken by National Bank and other relevant stakeholders to address a crisis and restore financial stability;

16/ **"Digital Financial Service"** means provision of banking service including credit, savings, remittances, payments and other related services accessed or delivered through digital channels;

17/ **"Direct Shareholding"** means shareholding in a bank, by a person directly on his own name, or jointly with his spouse or with a person who has not attained the age of legal majority related to him by the first degree or through any other conditions as may be determined by National Bank;

፲፰/ **"ዳይሬክተር"** ማለት በማንኛውም ሥያሜ የሚጠራ ማንኛውም የባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፤

፲፱/ **"የሀገር ውስጥ ባንክ"** ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ እና በኢትዮጵያ የባንክ ሥራ በመሥራት ላይ ያለ ባንክ ነው፤

፳/ **"ሠራተኛ"** ማለት የአንድን ባንክ የዕለት ተዕለት ሥራዎች እንዲያከናውን በባንኩ የተሾመ ወይም የተቀጠረ ወይም በሠራተኛ ዝውውር አማካኝነት የተመደበ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው ነው፤

፳፩/ **"የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ"** ማለት የፋይናንስ ተቋምን ሳይጨምር የባንክ አገልግሎቶችን የሚጠቀም፣ የተጠቀመ፣ ለመጠቀም የሚፈልግ ሰው ነው፤

፳፪/ **"የፋይናንስ ተቋም"** ማለት ባንክ፣ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ አነስተኛ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ፣ የክፍያ ሥርዓት አንቀሳቃሽ፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የሃዋላ ድርጅት፣ የውጭ ባንክ እንደራሴ ቢሮ፣ የፖስታ ገንዘብ አስተላላፊ ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን እና ፈቃድ የሚሰጠው ሌላ ተመሳሳይ ተቋም ነው፤

፳፫/ **"የአደራ ተግባር"** ማለት አብዛኛውን ጊዜ ክፍያ በማስከፈል በባንክ የሚከናወን ንብረትን ተቀብሎ በአደራ የማስቀመጥ ወይም በሌሎች ሰዎች ስም ገንዘብ የማስተዳደር ተግባር ነው፤

፳፬/ **"የሒሳብ ዓመት"** ማለት እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ በቀጣዩ ዓመት ሰኔ ፴ ቀን የሚያበቃ የባንክ የሒሣብ ዓመት ነው፤

18/ **"Director"** means any member of the board of directors of a bank, by whatever title he may be referred to;

19/ **"Domestic Bank"** means a bank incorporated in Ethiopia; and is conducting banking business in Ethiopia;

20/ **"Employee"** means a chief executive officer, a senior executive officer or any other person who is appointed or hired by a bank or assigned through staff transfer to carry out its day-to-day activities;

21/ **"Financial Service Consumer"** means a person who uses, has used, or is contemplating to use any of the services of a bank excluding a financial institution;

22/ **"Financial Institution"** means a bank, an insurance company, a reinsurer, a micro finance institution, a micro insurance company, payment instrument issuer, payment system operator, a capital goods finance company, a money transfer institution, representative office of a foreign bank, a postal money transfer institution or such other similar institution as determined and licensed by National Bank;

23/ **"Fiduciary Function"** means the trustee function of a bank whereby the bank provides safe keeping services or administers funds on behalf of others, usually for a fee;

24/ **"Financial Year"** means the financial year of a bank running from July 1st to June 30th of the following year;

፳፭/ **"የውጭ ባንክ"** ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ በሌላ ሀገር ሕግ መሠረት ተቋቁሞ በተቋቋመበት ሀገር ተቆጣጣሪ የባንክ ፈቃድ ያገኘ ባንክ ወይም የባንክ ቡድን ሆኖ የባንክ ሥራን በተቋቋመበት ሀገር ወይም እንደ ሁኔታው በሌሎች ሀገሮች የሚያከናውን ባንክ ነው፤

፳፮/ **"የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ"** ማለት የራሱ የሆነ ሕጋዊ ሰውነት የሌለው ሆኖ ከሕዝብ የተቀማጭ ገንዘብ የሚቀበል ወይም የማይቀበል የውጭ ሀገር ባንክ ቅርንጫፍ ነው፤

፳፯/ **"የውጭ ባንክ ተቀጥላ"** ማለት በንግድ ሕግ የተሰጠውን ትርጓሜ የያዘ እና በውጭ ባንክ ስትራቴጂክ ኢንቨስተር ቁጥጥር ሥር ያለ ሆኖ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ ተቀጥላ ነው፤

፳፰/ **"የውጭ ሀገር ገንዘብ"** ማለት የውጭ ሀገር ዜጎች ወይም በውጭ ሀገር ዜጎች በባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች በባንክ ላይ ለሚያደርጉት ኢንቨስትመንት ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰን ከኢትዮጵያ ሕጋዊ ገንዘብ ውጭ የሆነ እና ከኢትዮጵያ ውጭ በሌላ ማንኛውም ሀገር ሕጋዊ ገንዘብ የሆነ ማንኛውም ገንዘብ ነው፤

፳፱/ **"የውጭ ሀገር ዜጋ"** ማለት የኢትዮጵያ ዜጋ ያልሆነ ማንኛውም ሰው ነው፤ ይህም የውጭ ባንኮችን ያካትታል፤

25/ **"Foreign Bank"** means a bank or a bank group incorporated under the laws of a country other than Ethiopia with a banking license issued from its home country regulator and conducts its banking business in its country of incorporation or other jurisdictions as the case may be;

26/ **"Foreign Bank Branch"** means deposit or non-deposit taking branch of a foreign bank, having no separate legal existence;

27/ **"Foreign Bank Subsidiary"** means a subsidiary as defined under the Commercial Code, and controlled by a foreign bank strategic investor, and incorporated under the laws of, and having its head office in Ethiopia;

28/ **"Foreign Currency"** means any currency other than Ethiopian legal tender, which is a legal tender in any country outside Ethiopia and to be determined by National Bank Directive as acceptable for investment in a bank by foreign nationals or foreign owned Ethiopian organizations;

29/ **"Foreign National"** means a person who is not an Ethiopian national and includes foreign banks;

፴/ **“የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ”** ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣ አዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬ መሠረት ትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጭ ሀገር ዜጋ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሕጋዊ መታወቂያ ያለው ሰው ነው፤

፴፩/ **“በውጭ ሀገር ዜጎች በባለቤትነት የተያዘ የኢትዮጵያ ድርጅት”** ማለት ሙሉ በሙሉ በውጭ ሀገር ዜጎች በባለቤትነት የተያዘ ወይም ከኢትዮጵያውያን ጋር በጋራ በባለቤትነት የተያዘ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ ተቋም ነው፤

፴፪/ **“የውጭ ሀገር እናት ባንክ”** ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ በባንክ ሥራ ላይ የተሰማራ የውጭ ባንክ ተቀጥላ ላይ ከሀምሳ በመቶ በላይ የሚሆነውን የባለቤትነት ድርሻ የያዘ የውጭ ባንክ ወይም የባንክ ቡድን ነው፤

፴፫/ **“ቋሚ ንብረት”** ማለት ዝርዝሩ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ግዙፋዊ ህልውና ያለው እና ገቢ ከተደረገበት ግዜ አንስቶ ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ ንብረት ነው፤

፴፬/ **“ገንዘብ ማስተላለፍ”** ማለት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ማንኛውም የውጭ ባንክ ኢትዮጵያ ወደሚገኘው ቅርንጫፉ ወይም ተቀጥላው የሚያደርገው የገንዘብ ዝውውር ነው፤

፴፭/ **“ዋስትና”** ማለት ግዴታ ያለበት ሰው ግዴታውን ሳይወጣ የቀረ እንደሆነ በተስማሙት መጠን መሠረት ግዴታውን ለመሸፈን አንድ ባንክ ለማንኛውም ሰው በጽሑፍ የሚሰጠው ማረጋገጫ ነው፤

30/ **“Foreign National of Ethiopian Origin”** means a person with valid identification card obtained pursuant to Providing Foreign Nationals of Ethiopian Origin with Certain Rights to be Exercised in their Country of Origin Proclamation No.270/2002 attesting that he is foreign national of Ethiopian origin;

31/ **“Foreign Owned Ethiopian Organization”** means an entity that is fully owned by Foreign Nationals or jointly owned with Ethiopians, and registered under the laws of, and having its head office in Ethiopia;

32/ **“Foreign Parent Bank”** means a foreign bank or bank group that owns more than fifty percent of the foreign bank subsidiary engaged in banking business in Ethiopia;

33 **“Fixed Asset”** means a tangible asset that has a useful economic life of more than one year from the date it is received as determined by National Bank Directive;

34/ **“Fund Transfer”** means transfer of funds from a foreign bank to its branch or subsidiary in Ethiopia as per National Bank Directive;

35/ **“Guarantee”** means a written assurance made by a bank to a person to cover an agreed amount if another person fails to meet his obligation;

፴፮/ **"የገንዘብ-አከል ንብረት እጥረት"** ማለት አንድ ባንክ የአጭር ጊዜ ግዴታዎቹን መወጣት በማይችልበት ወቅት የሚፈጠር የባንክ የፋይናንስ ሁኔታ ነው፤

፴፯/ **"ገለልተኛ ዳይሬክተር"** ማለት በባንኩ በማንኛውም አስተዳደር ውስጥ የማይሳተፍ የቦርድ አባል ሆኖ የቦርድ አባሉን ነጻ እና ሚዛናዊ አተያየት ከሚያዛባ ማንኛውም ዓይነት ውስጣዊ፣ ውጫዊ፣ የፖለቲካና ሌሎችም ተፅዕኖዎች ነጻ የሆነ እና የባንኩ አክሲዮን ባለቤት ያልሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፤

፴፰/ **"የውጭ ኦዲተር"** ማለት የኦዲት አገልግሎት እንዲሰጥ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ፈቃድ የተሰጠው ገለልተኛ ኦዲተር ነው፤

፴፱/ **"ዕዳ መክፈል የማይችልበት ወሰን ላይ የደረሰ"** ማለት ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት የአንድ ባንክ ጠቅላላ ዕዳ ከጠቅላላ ሀብቱ የበለጠ የሚሆንበት የፋይናንስ አቋም ነው፤

፵/ **"በተዘዋዋሪ የተያዘ የአክሲዮን ድርሻ"** ማለት በአንድ ባንክ ውስጥ ቀጥተኛ ባለአክሲዮን በሆነ አንድ ሰው አስር በመቶ እና ከዚያ በላይ የአክሲዮን ባለቤት በሆነበት ድርጅት ስም ወይም ዕድሜያቸው ለአካለ መጠን በደረሱ ልጆች ስም ወይም ሌሎች ብሔራዊ ባንክ በሚወስናቸው ሁኔታዎች በባንክ ውስጥ የተያዘ የአክሲዮን ድርሻ ነው፤

፵፩/ **"ከወለድ ነጻ ባንክ"** ማለት ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎቶች እንዲሰጥ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ባንክ ነው፤

፵፪/ **"ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት"** ማለት ወለድ ያለመቀበልን ጨምሮ ከሸሪዓ መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ በወለድ ነፃ ባንኮች እና ከወለድ ነፃ አገልግሎት መስኮት በሚሰጡ ባንኮች የሚሰጥ የባንክ አገልግሎት ነው፤

36/ **"Illiquid"** means the financial condition of a bank where such bank becomes unable to meet its short term obligations;

37/ **"Independent Director"** means non-executive member of the board who does not have any management responsibilities within the bank, who is not shareholder of the bank and is not under any other influence, internal or external or political that would impede the board members exercise of objective judgment;

38/ **"External Auditor"** means an independent auditor licensed by the pertinent Government organ to provide audit service;

39/ **"Insolvent"** means a financial stance of a bank when the liabilities of such bank exceed its assets as determined by National Bank;

40/ **"Indirect Shareholding"** means shareholding in a bank through an entity owned by a direct shareholder with ten percent or more ownership in the entity or through his children who attained the age of legal majority or through any other conditions as may be determined by National Bank;

41/ "**Interest Free Bank**" means a bank licensed by the National Bank to engage in interest free banking services;

42/ **"Interest Free Banking Services"** means provision of banking service by full-fledged interest free banks and banks providing interest free banking window in compliance with Shari'ah Principles, including non-acceptance of interest;

፵፫/ **"የኢንቨስትመንት ባንክ"** ማለት በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፰/፪ሺ፲፫ ውስጥ የተሰጠው ትርጓሜ ያለው ነው፤

፵፬/ **"ንብረት ማጣራት"** ማለት የአበዳሪዎችን የይገባኛል ጥያቄዎች ለመመለስ የአንድን የወደቀ ወይም እንዲፈርስ የተወሰነበት ባንክን ንብረቶች መሰብሰብን፣ ዋጋቸውን መገመትን፣ መጠበቅን እና ወደ ገንዘብ መቀየርን ጨምሮ ይህን ባንክ የማፍረስ ሂደት ነው፤

፵፭/ **"ንብረት አጣሪ"** ማለት የአንድን የወደቀ ባንክ ንብረት እንዲያጣራ በብሔራዊ ባንክ የተሾመ ሰው ነው፤

፵፮/ **"ብድር"** ማለት፦

ሀ) በተወሰነ ቀን ወይም ቀናት ወይም በተጠየቀ ጊዜ በተለምዶ ከወለድ ጋር ተመልሶ እንዲከፈል ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ወይም ግዴታ በማስገባት ለማንኛውም ሰው ከተሰጠ ወይንም ለመስጠት ቃል ከተገባ ገንዘብ፤

ለ) እንዳልታቀደ ኦቨርድራፍት ያለ በተዘዋዋሪ የሚሰጥ ገንዘብ፤

ሐ) ከሌላ አበዳሪ ጋር በትብብር በሚሰጥ ብድር ከመሳተፍ እና ከሌላ አበዳሪ ብድር ከመግዛት፣

መ) ከዋስትና፤

ሠ) ከወለድ ነጻ ፋይናንስ፤

ረ) በማንኛውም ሰው ስም ከሚሰጥ የኦቨርድራፍት ብድር ፤ እና

ሰ) በየጊዜው በብሔራዊ ባንክ ከሚወሰኑ ሌሎች ማናቸውም የፋይናንስ ሀብቶች የሚመነጭ ማንኛውም የአንድ ባንክ የፋይናንስ ሀብት ነው።

43/ **"Investment Bank"** means as defined under Capital Market Proclamation No.1248/2021;

44/ **"Liquidation"** means the winding-up process that includes collecting, valuing, servicing, and converting the assets of a failed bank or a bank decided to be liquidated to cash to satisfy the claims of its creditors;

45/ **"Liquidator"** means a person appointed by National Bank to undertake the liquidation of a failed bank;

46/ **"Loans"** means any financial assets of a bank arising from:

a) an advance or a commitment to advance funds to a person that is conditioned on the obligation of the person to repay the funds, either on a specified date or dates or on demand, usually with interest;

b) indirect advances such as unplanned overdrafts;

c) participation in loan syndication and the purchase of loans from another lender;

d) a guarantee;

e) interest free financing;

f) an overdraft facility to be funded on behalf of a person; and

g) any other financial assets as may be determined by National Bank from time to time.

፵፯/ **"ውህደት"** ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ባንኮች በፈቃደኝነት ወይም በሕግ አስገዳጅነት በመዋሃድ ከመካከላቸው አንድ ወይም ከአንድ በላይ ባንኮች ህልውናቸው ከስሞ አዲስ ባንክ የሚቋቋምበት ነው፤

፵፰/ **"ብሔራዊ ባንክ"** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

፵፱/ **"መደበኛ የሥራ ሂደት"** ማለት ነባር የንግድ ልማዶችን፣ አሠራሮችን እና ደረጃዎችን በመከተል የባንክ ሥራ ማከናወን ነው፤

፶/ **"የሞግዚት አስተዳዳሪ"** ማለት አንድ ችግር ያለበት ባንክ እስከሚረጋጋ ወይም ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳደሩን ለማቆም እስከሚወስን ድረስ ባንኩን ጠብቆ ለማቆየት፣ ሥራውን ለመምራት እና ንብረቱን ለመጠበቅ ሲባል ባንኩን ተረክቦ ሥራውን እንዲመራ እና እንዲያስኬድ እንዲሁም ተቀባይነት ያለው የእልባት ዕቅድ እንዲያዘጋጅ በብሔራዊ ባንክ የተሾመ ሰው ነው፤

፶፩/ **"የሞግዚት አስተዳደር"** ማለት አንድ ባንክ በብሔራዊ ባንክ ውሳኔ መሠረት በጊዜያዊነት በሞግዚት አስተዳዳሪ ቁጥጥር ሥር የሚሆንበት ሁኔታ ነው፤

፶፪/ **"እናት ባንክ"** ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠራ ተቀጥላ ውስጥ ከሀምሳ በመቶ በላይ የባለቤትነት ድርሻ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የያዘ የሀገር ውስጥ ባንክ ነው፤

፶፫/ **"ችግር ያለበት ባንክ"** ማለት በደህንነቱ እና በጤንነቱ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ከፍተኛ የፋይናንስ፣ የሥራ ሂደት ወይም የሥራ አመራር ድክመቶች የሚታዩበት እና ጥብቅ እርምጃዎችን በጊዜ በመውሰድ የገንዘብ ሀብቱ፣ የሥራ ሞዴሉ፣ የስጋት አመራር ሥርዓቶቹ እና የቁጥጥር እና/ወይም የአስተዳደር ሥርዓቱ በከፍተኛ ሁኔታ መሻሻል ያለበት ማንኛውም ባንክ ነው፤

47/ **"Merger"** means a voluntary or statutory fusion of two or more banks where one or more banks lose their existence and a new bank is formed;

48/ **"National Bank"** means the National Bank of Ethiopia;

49/ **"Normal Course of Business"** means the conduct of banking business within the scope of existing commercial customs, practices and standards;

50/ **"Official Administrator"** means a person appointed by the National Bank to takeover and assume management and operate a problem bank so as to conserve, manage, and protect its assets and prepare legitimate resolution plan for the bank until the bank is stabilized or National Bank decides to cease official administration;

51/ **"Official Administration"** means the state of a bank being temporarily controlled by an official administrator as per National Bank decision;

52/ **"Parent Bank"** means a domestic bank that fully or partially owns more than fifty percent of the subsidiary operating in Ethiopia;

53/ **"Problem Bank"** means a bank exhibiting significant financial, operational, or managerial weaknesses affecting its safety and soundness and requires stringent actions and major improvement in its financial resource, business model, risk management systems and controls and/or governance in a timely manner;

፶፬/**“የብቃት መመዘኛ”** ማለት ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ የብቃት፣ የተገቢነት እና የሥነ-ምግባር መመዘኛ ነው፤

፶፭/**“የሙከራ የቁጥጥር ማዕቀፍ”** ማለት ፈጠራ የታከለባቸዉ አዳዲስ የባንክ አገልግሎቶች በብሔራዊ ባንክ ይሁንታ ወይም መደበኛ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር እና ክትትል ሥር ሆነው በተገደበ ጊዜ በሙከራ ሂደት ውስጥ እንዲያልፉ የሚያስችል የቁጥጥር ማዕቀፍ ነው፤

፶፮/ **“የእንደራሴ ቢሮ”** ማለት ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ በሚወስነው መሠረት እንደ ጉዳይ ማስፈጸም፣ ማስተዋወቅ፣ ጥናት እና መሰል የእንደራሴ ሥራዎችን የሚሠራና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ባንክ እንደራሴ ቢሮ ነው፤

፶፯/ **“የማገገም ዕቅድ”** ማለት ሊፈጠሩ የሚችሉ ከፍተኛ ጫናዎችን እና አስጊ ሁኔታዎችን ከወዲሁ በመለየት እና በመገምገም እነዚህን አስጊ ሁኔታዎች ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመፍታት እና የፋይናንስ እና የንግድ አዋጭነትን ለማረጋገጥ በባንኩ መወሰድ ያለባቸውን ተጓዳኝ የማገገሚያ እርምጃዎች እና አሠራሮች በማካተት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት በአንድ ባንክ የተዘጋጀ ዝርዝር እና ሁሉን አቀፍ ሰነድ ነው፤

፶፰/ **“እልባት”** ማለት የመውደቅ ዕድላቸው ሰፊ የሆነ ወይም የወደቁ ባንኮች ላይ ገንዘብ ተቀማጭ ያደረጉ ሰዎችን ከጉዳት ለመጠበቅ ወይም በአበዳሪዎች ላይ የሚደርስን ኪሳራ ለመቀነስ የተለያዩ የእልባት ዘዴዎችን በመጠቀም በብሔራዊ ባንክ የሚተገበር እልባት የመስጠት ሂደት ነው፤

54/ **“Qualification of Competency”** means required education, experience, competence, fitness and propriety as determined by Directive to be issued by National Bank;

55/ **“Regulatory Sandbox”** means a regulatory framework that allows for a live and time bound testing of innovative banking services under National Bank’s control and oversight, prior to authorization or licensing by the National Bank;

56/ **“Representative Office”** means an office of a foreign bank located in Ethiopia and engaged in representational functions such as liaison, marketing, research and other similar activities as may be determined by National Bank Directive;

57/**“Recovery Plan”** means detailed and comprehensive document prepared by a bank as per National Bank Directive and includes the identification and assessment of possible severe situations of stress and corresponding recovery measures and arrangements to be taken by a bank so as to effectively address the stress and ensure financial and business viability;

58/ **“Resolution”** means a process undertaken by National Bank to deal with likely to fail or a failed bank so as to protect depositors, or minimize losses to creditors through adoption of various resolution tools;

፶፱/ **"የእልባት ዕቅድ"** ማለት አንድን የመውደቅ ዕድሉ ሰፊ የሆነ ወይም የወደቀ ባንክ ባህሪያት እና ወሳኝ ተግባራት በዝርዝር በመለየት በሥራ ላይ የሚውለውን ተመራጭ የእልባት ስትራቴጂ እና ዘዴዎች የሚያስቀምጥ እና ዓላማውም ገንዘብ አስቀማጩን ከጉዳት ለመጠበቅ፣ ባንኩ መውደቁን ተከትሎ በሚጣራው ንብረት ላይ የሚደርስ ኪሳራን ለመቀነስ፣ የወሳኝ ተግባራት ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እና ለፋይናንስ ሥርዓቱ መረጋጋት ስጋት የሚሆኑ ጉዳዮችን ለመከላከል የሚያስችል በብሔራዊ ባንክ የተዘጋጀ ሁሉን አቀፍ ሰነድ ነው፤

፷/ **"በዋስትና የተጠበቀ የይገባኛል ጥያቄ"** ማለት በንብረት መያዣነት ወይም በውል መሠረት በሌሎች ንብረቶች ላይ ተፈፃሚ በሚሆን ዋስትና የተደገፈ የማንኛውም ባንክ የይገባኛል ጥያቄ ነው፤

፷፩/ **"ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ"** ማለት በማንኛውም ሥያሜ የሚጠራ ሆኖ፦

ሀ) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ መምሪያዎችን ወይም ዳይሬክቶሬቶችን በሥሩ የሚያስተዳድር ወይም በብሔራዊ ባንክ በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት አንድን ወሳኝ መምሪያ የሚያስተዳድር እና ተጠሪነቱ በቀጥታ ለዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆነ፤

ለ) ተጠሪነቱ በቀጥታ ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሆነ፣

ሐ) የኩባንያ ፀሐፊ የሆነ፤

መ) የውጭ ባንክ ቅርንጫፍን (ፎችን) በበላይነት የሚያስተዳድር እንዲሁም ከብሔራዊ ባንክ ጋር ለሚኖር የሥራ ግንኙነት ባንኩን የሚወክል ከፍተኛ የሀገር ኦፊሰር፤ ወይም

59/ **"Resolution Plan"** means a comprehensive document prepared by National Bank detailing the characteristics and critical functions of a likely to fail or failed bank and puts forward preferred resolution strategy and tools to be employed with the view of protecting depositors, minimizing the losses to the resultant liquidation estate, ensuring continuity of critical functions and avoid threat to the stability of the financial system;

60/ **"Secured Claim"** means any claim of a bank guaranteed by property or secured by assignment of rights to other assets on the basis of a contract to that effect;

61/ **"Senior Executive Officer"** means any officer of a bank by whatever title that officer may be referred to, who:

a) manages two or more departments or directorates under its portfolio or manages one department of critical importance as defined by National Bank and is directly reporting to the chief executive officer;

b) reports directly to the board of directors;

c) is company secretary;

d) is senior country officer of a foreign bank branch who is responsible to manage the operation of the local branch/es and represent the bank in respect of its business relationship with the National Bank; or

ሠ) በብሔራዊ ባንክ መመሪያ እንደ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ሊቆጠር የሚችል፣ ማንኛውም የባንክ የሥራ ኃላፊ ነው፡፡

፷፪/ **"ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ"** ማለት ከአንድ ባንክ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ በአንድ ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተያዘ ሁለት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የአክሲዮን ድርሻ ነው፤

፷፫/ **"ልዩ ባንክ"** ማለት ኢንቨስትመንት ባንክን ሳይጨምር እንደ ወጪና ገቢ ንግድ፣ የቤት ግንባታ፣ ግብርና፣ የህብረት ሥራ እና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲሁም በየጊዜው በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ የኢኮኖሚ ወይም የገበያ ዘርፍ ላይ በማተኮር ልዩ የባንክ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ባንክ ነው፤

፷፬/ **"የሠራተኛ ዝውውር"** ማለት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት የውጭ ዜግነት ያላቸው ሠራተኞችን ከአንድ የውጭ ባንክ በኢትዮጵያ ወደሚገኝ የባንኩ ቅርንጫፍ ወይም ተቀጥላ ማዛወር ነው፤

፷፭/ **"በሕግ አስገዳጅነት የሚፈጸም ውህደት"** ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ባንኮች በብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው ውሳኔና አቅጣጫ መሠረት እንዲሁም የዚህን አዋጅ እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎችን በተከተለ መልኩ የሚያከናውኑት ውህደት ነው፤

e) may be designated as senior executive officer by National Bank Directive.

62/ **"Significant Ownership"** means direct or indirect shareholding of two or more percent of the total subscribed capital of a bank by a person;

63/ **"Specialized Bank"** means a bank, other than investment bank, licensed by the National Bank to provide a focused and specialized banking services, tailored to specific sector of the economy or market segment such as export import, mortgage, agriculture, cooperative, micro and small enterprises and other similar sectors as may be determined by National Bank Directive from time to time;

64/ **"Staff Transfer"** means the transfer of foreign national employees from a foreign bank to its branch or subsidiary in Ethiopia in accordance with National Bank Directive;

65/ **"Statutory Merger"** means a merger where two or more banks are merged as per the National Bank decision and direction; and in line with the provisions of this Proclamation and other relevant laws;

፷፮/ **"ስትራቴጂክ ኢንቨስተር"** ማለት ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ የሚቀመጡ የማጣሪያ መስፈርቶችን የሚያሟላ ሆኖ በተቋቋመበት ሀገር ዕውቅና እና መልካም ዝና ያለው የውጭ ባንክ ወይም የባንክ ቡድን ወይም በተቋቋመበት ሀገር መንግሥት በባለቤትነት የተያዘ ባንክ ወይም ዓለም አቀፍ የልማት የፋይናንስ ተቋም፣ የግል ኢኩዊቲ ፈንድ ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰኑ ሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች ናቸው፤

፷፯/ **"ተቀጥላ"** ማለት በንግድ ሕግ የተሰጠውን ትርጓሜ የያዘ ሆኖ በእናት ባንክ ቁጥጥር ሥር ያለ፣ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ ነው፤

፷፰/ **"በፈቃደኝነት መፍረስ"** ማለት አንድ ዕዳ መክፈል የማይችልበት ወሰን ላይ ያልደረሰ ባንክ ሕጋዊ በሆነ እና ሥርዓት በጠበቀ መንገድ ሥራውን አቁሞ ሀብቱን ለባለድርሻ አካላት የሚያከፋፍልበት ሂደት ነው፤

፷፱/ **"በፈቃደኝነት የሚደረግ ውህደት"** ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ባንኮች በፈቃደኝነት በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት እንዲሁም በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የሚያከናውኑት ውህደት ነው፤

፸/ **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፸፩/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠ አገላለጽ ሁሉ የሴት ጾታን ይጨምራል፡፡

66/ **"Strategic Investor"** means a foreign bank or a bank group with inbuilt good reputation in its country of incorporation or owned by the Government of the country where it was incorporated or International Development Finance Institution, private equity fund or other similar entities to be determined by National Bank and meet the minimum vetting criteria to be set by National Bank Directive;

67/ **"Subsidiary"** means as defined under the Commercial Code, and controlled by a parent bank, registered under the laws of, and having its head office in Ethiopia;

68/ **"Voluntary Liquidation"** refers to the process by which a solvent bank, through a formal and orderly procedure, ceases its operations and distributes its assets to stakeholders;

69/ **"Voluntary Merger"** means where two or more banks are merged as per a voluntary agreement, and in line with the provisions of this Proclamation and other relevant laws;

70/ **"Person"** means any natural or juridical person;

71/ An expression in the masculine gender includes the feminine.

## ክፍል ሁለት

## ስለባንክ ሥራ ፈቃድ

### ፫. የባንክ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

፩/ ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ የባንክ ሥራ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ሳያገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ የባንክ ሥራ ማካሄድ አይችልም።

፪/ በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ፈቃድ ከተሰጠው የኢንቨስትመንት ባንክ በስተቀር ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ “ባንክ” የሚለውን ቃል ወይም ተዛማጅ የሆነ ስያሜ የማንኛውም የፋይናንስ ተቋም ስም አካል አድርጎ መጠቀም አይችልም።

፫/ ለውጭ ባንክ እንደራሴ ቢሮ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ መሠረት ፍቃድ ይሰጣል። በሌላ የመንግሥት አካል ከዚህ ቀደም ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም የውጭ ባንክ እንደራሴ ቢሮ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ መጠየቅ እና ማግኘት አለበት።

፬/ ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ በጽሑፍ ፈቃድ ካላገኘ በቀር ማንኛውም ባንክ፦

ሀ) ብሔራዊ ባንክ ከፈቀደው ቦታ ውጭ የባንክ ሥራ ማካሄድ ወይም ነባር የሥራ ቦታን መዝጋት ወይም ማዛወር፤

ለ) አዲስ የባንክ አቅርቦት እና አገልግሎት መጀመር፤

ሐ) የተፈቀደለትን የባንክ ሥራ ዓይነት በጉልህ መቀየር፤

## PART TWO

## LICENSING BANKING BUSINESS

### 3. Requirements for Banking Business License and Authorization

1/ No person shall engage in banking business in Ethiopia without obtaining banking business license or authorization from the National Bank.

2/ No person, except investment bank licensed by Ethiopian Capital Market Authority, shall use the word ‘bank’ or its derivatives as part of the name of any financial institution unless it has obtained a license from the National Bank.

3/ National Bank shall license representative office of a foreign bank as per National Bank Directive. Representative office of a foreign bank, previously licensed by other Government body, shall request for and get relicensed by the National Bank.

4/ Without the prior written approval of National Bank, no bank shall:

a) transact a banking business at any place other than that authorized by National Bank, or close or relocate an existing place of business;

b) introduce new banking products and services;

c) effect major changes in its line of business;

መ) በመደበኛ የሥራ ተግባሩ አፈፃፀም ሳቢያ ካልሆነ በቀር የንብረት ባለቤትነቱን በሙሉም ሆነ በከፊል በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ማስተላለፍ ወይም በሌላ መንገድ ማዛወር፤

ሠ) የራሱን አክሲዮን መልሶ መግዛት ወይም በመደበኛ ተግባሩ በተከሰተ ኪሳራ ምክንያት ካልሆነ በቀር ካፒታሉን መቀነስ፤

ረ) የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሁፉን ወይም በባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መልክ የተቋቋመ የውጭ ባንክን በተመለከተ በግል የሚሰጥ መግለጫን ማስመዝገብ፤ ወይም

ሰ) የባንክ ሥራ እንዲያካሂድ ፈቃድ ያገኘበትን ስም መቀየር አይችልም።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን በመተላለፍ ማንኛውም ሰው ተቀማጭ ገንዘብ ለመቀበል ማስታወቂያ ሲያስነግር ወይም የባንክ ሥራ እያካሄደ መሆኑን ብሔራዊ ባንክ ለማመን ምክንያት ሲኖረው ይህንኑ ሁኔታ ለማጣራት በዚሁ ሰው ይዞታ ሥር የሚገኙትን የንግድ መዝገቦች፣ ቃለ ጉባዔዎች፣ ሒሳቦች፣ ጥሬ ገንዘብ፣ የዋስትና ሰነዶች፣ ማስታወሻዎች፣ የገንዘብ ማዘዣዎችና ሌሎች ሰነዶች እንዲቀርቡለት ማድረግና መመርመር ወይም ማስመርመር ይችላል።

d) transfer or otherwise dispose whole or any part of its property, within or outside of Ethiopia, other than in the normal course of its business;

e) redeem its own shares or effect a reduction of its capital other than through reduction due to operating losses;

f) register its amended memorandum of association or unilateral declaration in case of a foreign bank established in the form of a single member PLC; or

g) alter the name under which it is licensed to do banking business.

5/ Where National Bank has a reason to believe that a person, in contravention of Sub-Article (1) of this Article, is advertising for or soliciting deposits of money or transacting banking business, it may, in order to ascertain the situation, require that all books, minutes, a ccounts, cash, securities, records, vouchers and other documents which are in the possession or custody of such person be submitted to it and examine or cause the same to be examined.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም አንድ ባንክ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሲያገኝ የአጭር ጊዜ ቁጠባን ለማሰባሰብ የሚደረግ ዘመቻ ሊያከናውን ወይም በልዩ ኩነት ላይ የባንክ አገልግሎቶችን ሊሰጥ እና/ወይም ወደ ደንበኛው የሥራ ቦታ በመሄድ ጥሬ ገንዘብ የማሰባሰብ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።

፯/ ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ የባንክ ሥራ በማካሄድ በዚህ ድርጊት አማካኝነት የተቀበለው ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት በእጁ የሚገኝ ከሆነ ብሔራዊ ባንክ ይኸው ገንዘብ ወይም ንብረት ለአስቀማጮቹ ወይም ለባለንብረቶቹ በአፋጣኝና በተቀላጠፈ መንገድ እንዲመለስ አስፈላጊው ትዕዛዝ እንዲሰጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያመለክታል። በተመሳሳይ ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ የውጭ ባንክ እንደራሴ ሥራ ሲያከናውን ከተገኘ ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊውን ትዕዛዝ እንዲሰጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያመለክታል።

፰/ በተለየ ሁኔታ ለመደራጀት ከሚፈልግ የውጭ ባንክ ተቀጥላ ወይም የመንግሥት ባንክ በስተቀር ማንኛውም ባንክ መደራጀት እና መቋቋም የሚችለው እንደ አክሲዮን ማህበር ነው።

## ፬. <u>የፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎች</u>

፩/ የባንክ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት እንደ አግባብነቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፦

ሀ) በተወሰነው ቅጽ መሠረት በሚገባ የተሞላ የፈቃድ መጠየቂያ ቅጽና ብሔራዊ ባንክ የሚጠይቃቸው ሌሎች በመመሪያ የሚወሰኑ አባሪ ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፤

6/ Notwithstanding paragraph (a) of Sub-Article (4) of this Article, upon securing authorization by the National Bank, a bank may engage in short time saving mobilization campaigns for a short period, or provide banking services at special event and/or cash collection services at customer's premises.

7/ Where any person undertakes banking business without license and holds money or other property obtained through such act, National Bank shall apply to the Federal High Court for ordering the immediate and efficient return of such money or property to the depositors or owners thereof. Similarly, if a person operates as representative office of a foreign bank without license, the National Bank shall apply to the Federal High Court to order the necessary actions as appropriate.

8/ Except for a foreign bank subsidiary or a Government bank that may be established in other forms, the form of organization of any bank shall be Share Company.

## 4. <u>Preconditions of Licensing</u>

1/ The following conditions shall be fulfilled, as appropriate, to obtain a banking business license:

a) a duly completed application form and other accompanying documents as specified by National Bank Directive, shall be submitted;

ለ) ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት የሰነድ መመርመሪያ ክፍያ መከፈል አለበት፤

ሐ) ማመልከቻው ለብሔራዊ ባንክ እንደቀረበ አደራጆቹ ወይም መሥራቾቹ ወይም አንድ የውጭ ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው ቅጽ መሠረት በባንክ ሥራ ለመሰማራት መፈለጋቸውን በመግለጽ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ያላቸውን ባለአክሲዮኖች ዝርዝር በስፋት በሚሰራጭ ጋዜጣ ላይ እንዲሁም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ለሁለት ተከታታይ ሳምንታት ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ አሳትመው ማውጣት አለባቸው፤

መ) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋም ማንኛውም ባንክ እንደ አግባብነቱ የመመሥረቻ ጽሑፉን፣ በግል የሚደረግ መግለጫውን፣ የፈራሚዎች ጉባዔ ወይም የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔውን በሚመለከተው የመንግሥት አካል ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ ማጸደቅ አለበት፤

ሠ) ያወጣቸው አክሲዮኖች በሙሉ የተፈረሙ ሆነው ከእነዚህም ውስጥ ቢያንስ አንድ አራተኛው በጥሬ ገንዘብ መከፈል አለበት፤ የውጭ ባንክ ተቀጥላን በተመለከተ ደግሞ ካፒታሉ ሙሉ በሙሉ አስቀድሞ በጥሬ ገንዘብ መከፈል አለበት፤

ረ) በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል በጥሬ ገንዘብ መከፈልና በምስረታ ላይ ባለው ባንክ ወይም ፈቃድ በሚሰጠው የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ ስም በዝግ የባንክ ሒሳብ ውስጥ መቀመጥ አለበት፤

b) an investigation fee, as determined by National Bank, shall be paid at the time of submitting the application;

c) upon filing the application with the National Bank, the promoters or founders or a foreign bank shall, at least once a week for a period of two consecutive weeks, publish in a widely circulating newspapers and in electronic form notice of intention to engage in banking business that also contains a list of shareholders with significant ownership, in a form prescribed by National Bank;

d) a bank incorporated in Ethiopia shall get its memorandum of association, unilateral declaration, minutes of subscribers meeting or general meetings of shareholders, as appropriate, approved by National Bank before registration with the appropriate Government organ;

e) all its issued shares shall be subscribed and at a minimum, one-fourth of the subscribed shares shall be fully paid in cash; and in case of foreign bank subsidiary, the capital should be fully paid in cash in advance;

f) the minimum paid-up capital prescribed by the National Bank shall be paid in cash and deposited in a blocked bank account opened in the name of the bank under formation or a foreign bank branch to be licensed;

ሰ) የአመልካቹ ባንክ ተጠቃሚ ባለቤቶች ሙሉ በሙሉ ቀጣይነት ባለው መልኩ ይፋ መደረግ አለባቸው፤

ሸ) የባንኩ ዳይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎች የብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚያስቀምጣቸውን የተገቢነት እና የሥነ-ምግባር መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፤

ቀ) ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ያላቸው የባንክ ባለአክሲዮኖች የብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚያስቀምጣቸውን የተገቢነት እና የሥነ-ምግባር መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፤ እና

በ) የባንኩ ህንፃና ግቢ፤ የጥበቃ ሥርዓትና የገንዘብ ማስቀመጫ ካዝና ብሔራዊ ባንክ የሚያስቀምጣቸውን መስፈርቶች ያሟሉ መሆን አለባቸው።

፪/ ሊቋቋም በታሰበው ባንክ ውስጥ ማንኛውም ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን መካተቱን የሚቃወም ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሐ) በተመለከተው መሠረት የመጨረሻው ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከማስረጃ ጋር በጽሑፍ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ ይችላል። ብሔራዊ ባንክ ተቃውሞውን ለመመርመር የሚያስችል እርምጃ ይወስዳል። የምርመራው ውጤት በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ተደርጎ ፈቃዱን ለመስጠት ወይም ለመከልከል ታሳቢ ይደረጋል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የባንክ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት ተጨማሪ ሁኔታዎችን ለመደንገግ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

g) beneficial owners of the applicant bank shall be fully disclosed, on an ongoing basis;

h) the directors, the chief executive officer and senior executive officers of the bank shall meet the fit and proper criteria prescribed by National Bank Directive;

i) shareholders of a bank with significant ownership shall meet the fit and proper criteria prescribed by National Bank Directive; and

j) the premises, security arrangements and cash vault of the bank shall meet the standards prescribed by National Bank.

2/ Any person who objects the involvement of any shareholders of a bank with significant ownership in the proposed bank may submit, no later than fifteen days starting from the date of the last publication under Sub-Article 1(c) of this Article, his objection in writing, with supporting evidence, to the National Bank. The National Bank shall initiate an inquiry into the objection. The results of such an inquiry shall be published and be considered in deciding whether or not to issue the license.

3/ Without prejudice to the requirements specified under Sub-Article (1) of this Article, National Bank may issue Directive to prescribe additional conditions of licensing.

፬/ ብሔራዊ ባንክ የፈቃድ ሁኔታዎችን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በመመሪያ ተጨማሪ ሁኔታዎችን የደነገገ እንደሆነ እነዚህ ሁኔታዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ ካሰበበት ጊዜ ሠላሳ ቀን ቀደም ብሎ የሚመለከታቸው ባንኮች እንዲያውቁት ያደርጋል።

፭/ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም የውጭ ባንክ እንደራሴ ቢሮ ፈቃድ ለማግኘት ሊያሟላቸው የሚገቡ ዝቅተኛ ሁኔታዎችን እና መስፈርቶችን እንዲሁም በቀጣይ ቁጥጥር ማድረግን በተመለከተ በመመሪያ ይወስናል።

## ፭. ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፬) መሠረት መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች ተሟልተው ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ባሉት ዘጠና ቀናት ውስጥ በባንክ ሥራ ፈቃድ ማመልከቻው ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

፪/ ፈቃዱ የሚሰጠው በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የፈቃድ ክፍያ ሲከፈል ይሆናል።

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት በብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ፈቃድ የባንክ ሥራን ለማካሄድ የሚያስችል የመጨረሻው ፈቃድ ይሆናል።

4/ Where the National Bank prescribes additional conditions of licensing in accordance with Sub-Article (3) of this Article, it shall notify such additional condtions to the concerned banks thirty days prior to the date on which such condtions becomes effective.

5/ National Bank by a Directive shall determine the minimum conditions and requirements for licensing and supervision of a representative office of a foreign bank.

## 5. Issuance of License

1/ The National Bank shall decide on a banking business license application within 90 days from the last date of receipt of all information to be submitted in accordance with Article 4 of this Proclamation.

2/ The license shall be issued upon payment of the licensing fee determined by National Bank.

3/ A license granted by National Bank pursuant to this Proclamation shall constitute final license to carry on a banking business.

**፮. ሥራ ስለመጀመር**

ፈቃድ የተሰጠው ባንክ፣

፩/ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የወንጀል እንቅስቃሴዎችን ከመለየት እና ከመከላከል ጋር የተያያዙ ሥርዓቶችን ጨምሮ አስተማማኝ የመረጃ አስተዳደር እና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቶችን፣ የስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲዎችንና ሥነ-ሥርዓቶችን እና የሰው ኃይል አደረጃጀትን እንዲሁም የባንክ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መሰል ግዴታዎችን ማሟላት፤ እና

፪/ ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት አሥራ ሁለት ወራት ውስጥ ሥራ መጀመር አለበት።

**፯. የፈቃድ እድሳት**

የባንክ ሥራ ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ የሚኖርበት ሲሆን የሚታደስበት ሁኔታዎችን በተመለከተ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ይወሰናል።

**፰. ፈቃድ የተሰጣቸውን ባንኮች ዝርዝር ስለማሳተም**

ብሔራዊ ባንክ በዓመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸውን ባንኮች ዝርዝር አትሞ ያወጣል። በተጨማሪም በዚህ ዝርዝር ላይ የተጨመሩትን ወይም ከዝርዝሩ የተሰረዙትን ባንኮች ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች እና በድረ-ገጹ ላይ አሳትሞ ያወጣል።

**፱. ቅርንጫፍ ወይም ንዑስ ቅርንጫፍ ስለመክፈት**

፩/ ማንኛውም ባንክ ከብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ወይም ንዑስ ቅርንጫፍ መክፈት ወይም የተከፈተ ቅርንጫፍ መዝጋት አይችልም።

**6. Commencement of Operation**

A bank to which a license is granted shall:

1/ fulfill, before commencing operation, sound information management and internal control systems, including those related to the detection and prevention of criminal activities, risk management policies and procedures, and human resource organization and such other essential obligations to carry out banking business as determined by a Directive to be issued by National Bank; and

2/ commence its operation within twelve months from the date of issuance of the license.

**7. Renewal of License**

The license of a bank shall be renewed annually as per conditions for renewal of banking business license to be specified in National Bank Directive.

**8. Publication of Licensed Banks**

National Bank shall, in its annual report, publish the list of licensed banks. It shall also publish, in newspapers of wide circulation and in its web-site, any additions to or cancellations from the said list.

**9. Opening of a Branch or a Sub Branch**

1/ A bank shall not open a branch or a sub-branch or close an opened branch or sub-branch in Ethiopia without obtaining prior written approval from National Bank.

፪/ የባንክ ቅርንጫፍ ወይም ንዑስ ቅርንጫፍ ለመክፈት ወይም ለመዝጋት መሟላት ያለባቸው ዝቅተኛ ሁኔታዎች እና መስፈርቶች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ይወሰናል።

2/ The minimum conditions and requirements to get an approval and open a branch or a sub-branch or close an opened branch or sub-branch shall be determined by National Bank Directive.

## ክፍል ሦስት

## በባንክ ሥራ ላይ የውጭ ዜጎች ስለሚሳተፉበት አግባብ

## PART THREE

## MODES OF FOREIGN NATIONALS PARICIPATION IN BANKING BUSINESS

### ፲. የውጭ ዜጎች በባንክ ሥራ የሚሳተፉበት ሁኔታ

፩/ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

ሀ) በጥሩ መሠረት ተቋቁሞ መልካም ስም እንዲሁም ጤናማ የፋይናንስ አቋም ያለው ማንኛውም የውጭ ባንክ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት የሚይዘው የውጭ ባንክ ተቀጥላ እንዲያቋቁም ወይም የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ እንዲከፍት ወይም እንደራሴ ቢሮ እንዲከፍት ወይም የባንክ አክሲዮኖችን እንዲይዝ ሊፈቀድለት ይችላል።

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የውጭ ባንክ ያልሆኑ የውጭ ሀገር ዜጎች እንዲሁም በውጭ ሀገር ዜጋ በባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች የባንክ አክሲዮን እንዲይዙ ሊፈቀድ ይችላል።

### 10. Banking Business by Foreign Nationals

1/ General Provisions:

a) A foreign bank which is well established, reputable and financially sound may be allowed to establish partially or fully owned foreign bank subsidiary or open a foreign bank branch or a representative office or acquire shares of a bank.

b) Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1(a) of this Article, foreign nationals other than foreign banks and foreign owned Ethiopian organizations may be authorized to acquire shares in banks.

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) እና ፩(ለ) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ስትራቴጂክ ኢንቨስተር በአንድ ነባር ወይም አዲስ የሀገር ውስጥ ባንክ የሚይዘው ቀጥተኛ የአክሲዮን ድርሻ ከባንኩ አጠቃላይ የተፈረመ ካፒታል ከአርባ በመቶ መብለጥ አይችልም፤ እንዲሁም እንደ ስትራቴጂክ ኢንቨስተር የማይቆጠር ማንኛውም የውጭ ዜጋ የሆነ የተፈጥሮ ሰው ወይም በውጭ ሀገር ዜጋ ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት በአንድ ነባር ወይም አዲስ የሀገር ውስጥ ባንክ የሚይዘው ቀጥተኛ የአክሲዮን ድርሻ ከባንኩ አጠቃላይ የተፈረመ ካፒታል በቅደም ተከተል ከሰባት በመቶ እና ከአስር በመቶ መብለጥ አይችልም።

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሐ) የተደነገገው ቢኖርም በአንድ ባንክ ውስጥ የውጭ ዜጎች እና በውጭ ሀገር ዜጋ በባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች የሚይዙት አጠቃላይ የአክስዮን መጠን ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል ከአርባ ዘጠኝ በመቶ መብለጥ አይችልም።

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) እና (መ) ሥር የተደነገጉት የኢንቨስትመንት ገደቦች ቢኖሩም ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች በሚገባ መሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢኮኖሚው ጠቀሜታ ያላቸው ስትራቴጂክ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ እና/ወይም ችግር ውስጥ ላለ ባንክ እልባት በመስጠት የፋይናንስ መረጋጋትን ለማስጠበቅ ሲባል ብሔራዊ ባንክ በልዩ ሁኔታ በአግባቡ የተቋቋሙ፣ መልካም ስም እንዲሁም ጤናማ የፋይናንስ አቋም ያላቸው የውጭ ባንኮች በግዢ አማካኝነት ነባር የሀገር ውስጥ ባንኮችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ እንዲይዙ ሊፈቅድ ይችላል።

c) Notwithstanding the provisions of Sub - Articles 1(a) and 1(b) of this Article, direct shareholding by a strategic investor in an existing or a new domestic bank shall be limited to forty percent of total subscribed shares of a bank; and such holding by non-strategic foreign national natural person and foreign juridical person shall be limited to seven percent and ten percent of subscribed shares of a bank, respectively.

d) Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1(c) of this Article, aggregate shareholding by foreign nationals and foreign-owned Ethiopian organizations in a bank shall be limited to 49 percent of the total subscribed shares of a bank.

e) Notwithstanding the investment limits stipulated under Sub-Article (1) (c) and (d) of this Article, for the purpose of attracting strategic investments that would benefit the economy and/or as way of resolving a distressed bank and preserve financial stability, National Bank on exceptional basis and subject to fulfillment of other preconditions, may allow well established, reputable and financially sound foreign banks to partially or fully acquire existing domestic banks through acquisition.

ረ) የውጭ ዜጎች እና ሙሉ በሙሉ በውጭ ሀገር ዜጎች በባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች በአንድ ባንክ ኢንቨስት ማድረግ የሚችሉት በውጭ የቀጥታ ኢንቨስትመንት አማካኝነት በውጭ ሀገር ገንዘብ ብቻ ነው።

ሰ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ረ) የተደነገገው ቢኖርም በከፊል በውጭ ሀገር ዜጎች በባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች የውጭ ሀገር ዜጎች በድርጅቱ ውስጥ ባላቸው አጠቃላይ የባለቤትነት ድርሻ መሠረት በውጭ የቀጥታ ኢንቨስትመንት አማካኝነት በውጭ ሀገር ገንዘብ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ሊፈቀድ ይችላል።

ሸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ረ) እና (ሰ) የተደነገገው ቢኖርም የውጭ ዜጎችን የባለቤትነት ድርሻ መጠን በተመለከተ በአጠቃላይ እና በግል የተቀመጠው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ ዜጎች እና በውጭ ሀገር ዜጎች በባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች በእያንዳንዱ የሒሳብ ዓመት መጨረሻ ከአክሲዮን ባለቤትነት የሚያገኙትን የትርፍ ድርሻ በኢትዮጵያ ብር መልሰው ኢንቨስት ሊያደርጉ ይችላሉ።

ቀ) የውጭ ዜጎች በማንኛውም ባንክ ውስጥ ካደረጉት ኢንቨስትመንት የሚያገኙት የትርፍ ድርሻ እና የውጭ ዜግነት ያላቸው ሠራተኞች ደመወዝ እንዲሁም ከአክሲዮን ሽያጭ ወይም ከአንድ ባንክ ንብረት መጣራት የሚገኝ ገንዘብ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ወደ ውጭ ሀገር ሊላክ ይችላል።

f) Foreign nationals and foreign-owned Ethiopian organizations fully owned by foreign nationals shall invest in a bank only through foreign direct investment in foreign currency.

g) Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1(f) of this Article, foreign-owned Ethiopian organizations partially owned by foreign nationals may invest according to aggregate percentage shareholding by foreign nationals, through foreign direct investment in foreign currency.

h) Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1(f) and 1(g) of this Article, dividend earnings at the end of every financial year may be reinvested in Ethiopian Birr by foreign nationals and foreign owned Ethiopian organizations, given foreign ownership is within the aggregate and individual shareholding limit.

i) Dividends earned from investment by foreign nationals in a bank and salaries of foreign national employees, and proceeds from sales of shares or liquidation of a bank may be repatriated as per the provisions of National Bank Directive and other pertinent laws.

በ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ቀ) የተደነገገው ቢኖርም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በውጭ ዜጎች በባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች የሚያገኙትን ማንኛውንም ገንዘብ መጀመሪያ ላይ በውጭ ሀገር ገንዘብ ከመቶ በተከፈለው የአክሲዮን ስሌት መጠን መሠረት ወደ ውጭ ሀገር ሊልኩ ይችላሉ።

ተ) ማንኛውም የውጭ ባንክ ተቀጥላ ወይም የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ ለባንክ ሥራ ዓላማ የሚውል ንብረት ሊይዝ ይችላል፤ እንዲሁም ለዕዳ ክፍያ በዋስትና ተይዘው የተወረሱትን ጨምሮ ሌሎች ንብረቶች በባለቤትነት መያዝ የሚችለው አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ሕጎች መሠረት ይሆናል።

ቸ) ማንኛውም የውጭ ባንክ ተቀጥላ ወይም የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ ወይም በኢትዮጵያዊያን እና በውጭ ዜጎች በጋራ በባለቤትነት የተያዘ ባንክ የሚተዳደርባቸውን የኩባንያ አመራር ሁኔታዎች እና መንገዶች በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

ኀ) ማንኛውም ተቀማጭ ገንዘብ የሚቀበል እንዲሁም የማይቀበል የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ ወይም የውጭ ባንክ ተቀጥላ ብሔራዊ ባንክ ያወጣቸውን ማናቸውም የጤናማነት መለኪያ መስፈርቶች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቆጣጣሪ አካላት ያወጡትን ሕጎች እንደ አግባብነቱ ከሀገር ውስጥ ባንኮች እኩል ማክበር አለበት።

j) Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1 (i) of this Article, foreign-owned Ethiopian organizations fully or partially owned by foreign nationals may repatriate any proceeds in accordance with percentage shareholding initially paid in foreign currency.

k) A foreign bank subsidiary or foreign bank branch may own property for its banking business purpose while ownership of other properties including foreclosed and acquired mortgaged property shall be in accordance with the relevant laws of the country.

l) National Bank through Directive may determine conditions and manner of corporate governance of a foreign bank subsidiary or a foreign bank branch or a bank jointly owned by foreign nationals and Ethiopians.

m) Both deposit taking and non-deposit taking foreign bank branch, or a foreign bank subsidiary shall comply with all prudential requirements of the National Bank as well as laws issued by other relevant authorities equally with domestic banks, as may be appropriate.

ነ) ለማንኛውም የውጭ ባንክ ተቀጥላ ወይም የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ ወይም የውጭ ባንክ እንደራሴ ቢሮ ፈቃድ መስጠትን እና ፈቃድ ማደስን፣ በውጭ ዜጎች ወይም በውጭ ዜጎች በባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች በማንኛውም ባንክ የሚያደርጉትን ኢንቨስትመንት፣ ፈቃድ የሚሰጣቸው የውጭ ባንክ ተቀጥላዎች እና ቅርንጫፎች ቁጥር የተመለከተ ገደብ ማውጣት እንዲሁም ተያያዥ የማጣሪያ መስፈርቶችን እና አጠቃላይ የባንክ ዘርፍ ካለው ሀብት በውጭ ዜጎች በባለቤትነት ሊያዝ በሚችለው እና በመቶኛ የሚገደብ የሀብት መጠን የተመለከቱ ተጨማሪ ዝቅተኛ ሁኔታዎችን እና መስፈርቶችን ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

ኘ) ለዚህ አዋጅ አፈጻፀም በውጭ ዜጎች እና ኢትዮጵያዊያን ወይም እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት በሚቆጠር የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በጋራ ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት አንድ ባንክ ላይ አክስዮን ሲይዝ ባንኩ ላይ የተደረገው የውጭ ኢንቨስትመንት መጠን የሚሰላው አክስዮን በገዛው ድርጅት ላይ የውጭ ዜጎች ያላቸውን የባለቤትነት ድርሻ መጠን መሠረት በማድረግ ይሆናል።

፪/ የውጭ ባንክ ተቀጥላ በባንክ ሥራ ስለሚሳተፍበት ሁኔታ፡-

ሀ) የውጭ ባንክ ተቀጥላ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ የካፒታል መጠን ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ይወሰናል፣

n) National Bank through Directive may determine additional minimum conditions and requirements on licensing and license renewal of a foreign bank subsidiary or a foreign bank branch, or a representative office of a foreign bank; investment by foreign nationals or foreign-owned Ethiopian organizations in a bank; limits on number of foreign bank subsidiaries and branches to be licensed including related vetting criteria and limits on percentage of the total assets of the banking system to be owned by foreign nationals.

o) For the purpose of implementing this Proclamation, in the event that an enterprise jointly owned by foreign nationals and Ethiopians or foreign nationals of Ethiopian origin treated as domestic investor acquire share in a bank, the amount of foreign investment made in the bank shall be determined in accordance with the respective ownership share the foreign nationals held in the enterprise that acquired share in a bank.

2/ Banking Business by Foreign Bank Subsidiary:

a) The minimum initial capital required to establish a foreign bank subsidiary shall be determined by National Bank Directive;

ለ) ማንኛውም የውጭ ባንክ ቅቀጥላ ማንኛውም ዓይነት የኩባንያ ቅርጽ ቢኖረውም ከውጭ እናት ባንኩ፣ ከሌሎች ባለአክሲዮኖች (ያሉት ከሆነ) እንዲሁም ባለአክሲዮን ካልሆኑ ነዋሪነታቸው በኢትዮጵያ ከሆነ ኢትዮጵያዊያን የተውጣጣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይኖረዋል፤ የቦርድ አባላትን ተዋጽኦ እና የአግባብነት እና የሥነ-ምግባር መስፈርቶች በተመለከተም ዝርዝሩ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

፫/ የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ በባንክ ሥራ ስለሚሳተፍበት ሁኔታ:-

ሀ)ማንኛውም የውጭ ባንክ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀማጭ ገንዘብ የሚቀበል ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ብድርን ጨምሮ ገንዘብ ከሌሎች ምንጮች ለማግኘት በማሰብ ተቀማጭ ገንዘብ የማይቀበል የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ እንዲከፍት ሊፈቀድ ይችላል፤ ሆኖም ሁለቱንም ዓይነት ቅርንጫፎች በአንድ ጊዜ እንዲከፍት አይፈቀድም፤

ለ) ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ በሚሠራበት ወቅት የሚፈቀዱለትን ተግባራት በግልጽ የሚያስቀምጥ መመሪያ ያወጣል፤

ሐ) ማንኛውም የውጭ ባንክ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚከፍተው የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ ቋሚ ካፒታል መመደብ አለበት፤ ይህም ካፒታል በውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር መተላለፍ ይኖርበታል:: በሀገር ውስጥ የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ ለመክፈት የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ የካፒታል መጠን እና ሌሎች መስፈርቶች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

b) A foreign bank subsidiary, irrespective of the form of company, shall have board of directors composed of foreign parent bank, other shareholders (if any) and local resident non-shareholder Ethiopians and details of their composition and fit and proper criteria shall be determined by National Bank Directive.

3/ Banking Business by Foreign Bank Branch:

a) A foreign bank may be allowed to open deposit taking or non-deposit taking foreign bank branch intending to be funded by other sources including borrowings in Ethiopia, but may not be allowed to open both types of branches at the same time;

b) National Bank shall issue Directive that clearly defines permissible activities that a foreign bank branch may undertake while operating in Ethiopia;

c) A foreign bank shall permanently assign capital for its foreign bank branch that shall be inwardly remitted and transferred to the country. The minimum amount of capital required to open foreign bank branch and other related conditions shall be determined by National Bank Directive;

መ) ማንኛውም የውጭ ባንክ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚከፍተው የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ(ፎች) ሁሉንም የቅርንጫፉን(ፎቹን) ዕዳ በፍጥነት ለመክፈል እና የሠራተኞቹን ሕገ-መንግሥታዊ መብት ለማክበር ዋስትና መስጠት ይኖርበታል፤

ሠ) ማንኛውም የውጭ ባንክ በሀገር ውስጥ የከፈተው የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ በማናቸውም ጊዜ ጤናማ እና ዕዳ የመክፈል አቅም የሚኖረው ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት፡፡

ረ) ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ የከፈተ ማንኛውም የውጭ ባንክ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የተደነገጉትን የአግባብነት እና የሥነ-ምግባር መስፈርቶች የሚያሟላ ሆኖ የውጭ ባንኩን የሚወክል፣ የውጭ ባንኩን ቅርንጫፍ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ የሚያስተባብር፣ የተጠቃለሉ የሥራ ሪፖርቶችን የሚያቀርብ እንዲሁም ባንኩን በግንባር ቀደምነት በመወከል ከብሔራዊ ባንክ ጋር የሥራ ግንኙነት የሚያደርግ ከፍተኛ የሀገር ኦፊሰር መመደብ አለበት።

፬/ እንደራሴ ቢሮ ስለሚሠራው ሥራ፡-

ማንኛውም የውጭ ባንክ እንደራሴ ቢሮ መሰማራት የሚችለው እንደ ጉዳይ ማስፈጸም፣ ማስተዋወቅ እና ጥናት እና ምርምር ማከናወን ባሉ የእንደራሴ ሥራዎች እና ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ በሚወስናቸው ሌሎች መሰል ሥራዎች ላይ ብቻ ነው።

d) A foreign bank shall guarantee for prompt payment of all liabilities of the foreign bank branch(es) and observance of the constitutional right of its employees;

e) A foreign bank shall ensure the soundness and solvency of its foreign bank branch at all times;

f) A foreign bank having branch in Ethiopia shall appoint senior country officer who fulfills the minimum fit and proper criteria determined by National Bank Directive and be responsible to represent the foreign bank, manage the overall operation of the foreign bank branch, submit consolidated reports, and serve as central point of contact with the National Bank.

4/ Operation of Representative Office:

A representative office of a foreign bank shall engage only in representational functions such as liaison, marketing, research and other similar activities as may be determined by National Bank Directive.

**፲፩. በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ ዜጋ በባንክ ሥራ ስለሚሰማራበት ሁኔታ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ ላይ የተደነገገው ቢኖርም አግባብነት ባለው ሕግ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ሰው ወይም በእነዚህ ሰዎች ሙሉ በሙሉ የተያዘ እና የተቋቋመ ድርጅት እና እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ የባንክ አክሲዮን በብር ስለሚገዛበት አግባብ ወይም ባንክ ስለሚያቋቁምበት አግባብ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ከዚሁ ኢንቨስትመንት የሚያገኘውን ማንኛውንም ክፍያ ወይም ገቢ በውጭ ምንዛሪ ከኢትዮጵያ ውጭ ማዛወር አይችልም፡፡

**11. Banking Business by a Foreign National of Ethiopian Origin**

Notwithstanding the provision of Article 10 of this Proclamation, the manner of share purchase in a bank in Birr or establishment of a bank by a person considered as foreign national of Ethiopian origin as per the relevant law or by an enterprise fully owned and established by these individuals and preferred to be treated as domestic investor shall be determined by National Bank Directive; however, any proceed or income generated from this investment shall not be transferred abroad in foreign currency.

## ክፍል አራት
## ስለአክሲዮኖችና የባለአክሲዮኖች ጉባዔ

**፲፪. አክሲዮኖችና የአክሲዮን መዝገብ**

፩/ የባንክ አክሲዮኖች እኩል ዋጋ ያላቸው፣ አንድ ዓይነት የሆኑና የተመዘገቡ ተራ አክሲዮኖች ይሆናሉ።

፪/ በሌሎች ሕጎች ላይ ሰነደ ሙዓለንዋዮች ግዑዝ አልባ ተደርገው በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲመዘገቡ የሚደነግገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባንክ በብሔራዊ ባንክ በሚወሰነው መሠረት የባለአክሲዮኖችን ስም ዝርዝር፣ አድራሻ፣ ጾታ የተፈረሙ እና የተከፈሉ አክሲዮኖቻቸውን ብዛት እና የገንዘብ መጠን እንዲሁም ድምጽ የመስጠት መብታቸውን የሚያሳይ የአክሲዮን መዝገብ መያዝ አለበት።

## PART FOUR
## SHARES AND SHAREHOLDERS MEETINGS

**12. Shares and Register of Shares**

1/ Bank shares shall be of one class and registered as ordinary shares of the same par value.

2/ Notwithstanding the provisions stipulated in other laws regarding the dematerialization and recording of securities in an electronic format, a bank shall keep a register of shares as determined by National Bank, which shall show names, addresses and gender of shareholders; number and amount of subscribed and paid shares and voting right.

፫/ በሌሎች ሕጎች ላይ የሰነደ ሙዓለ-ንዋዮች ግብይት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚካሄድበትን አግባብ አስመልክቶ የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአክሲዮን መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ ማንኛውም የአክሲዮን ዝውውር የሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው አክሲዮን መዝገብ በባንኩ መደበኛ የሥራ ሰዓት ሕዝብ ያለክፍያ ማየት በሚችልበት ሁኔታ በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት መቀመጥ አለበት። ሆኖም የአክሲዮን መዝገቡን ቅጂ በሙሉ ወይም በከፊል የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በባንኩ የሚወሰነውን ክፍያ በመፈጸም ማግኘት ይችላል።

## ፲፫. አክሲዮን የመያዝ ገደብ

፩/ በዚህ አዋጅ በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት በስተቀር፡-

ሀ) ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ከአንድ ባንክ ጠቅላላ የተፈረመ አክሲዮን ውስጥ ከሰባት በመቶ በላይ ቀጥተኛ የአክሲዮን ድርሻ ሊይዝ አይችልም፤ እና

ለ) ማንኛውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከአንድ ባንክ የተፈረመ አክሲዮን ውስጥ ከአሥር በመቶ በላይ ቀጥተኛ የአክሲዮን ድርሻ ሊይዝ አይችልም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ወደ ባንክ በተሸጋገረ ባንክ ውስጥ ማንኛውም የክልል መንግሥት እና የክልል መንግሥት የልማት ድርጅቶች ሊኖራቸው የሚችለው የአክሲዮን መጠን በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ይወሰናል።

3/ Notwithstanding the provisions stipulated in other laws regarding the exchange of securities electronically, any transfer of shares not recorded in the register of shares shall be null and void.

4/ The register maintained under Sub-Article (2) of this Article shall be open to the public, without charge, at the bank's head office during its normal working hours. However, any person may obtain a copy of or an extract from the register upon payment of the fee prescribed by a bank.

## 13. Limitations on the Acquisition of Shares

1/ Unless explicitly provided in this Proclamation and with exception of the Federal Democratic Republic of Ethiopia:

a) A natural person shall not directly hold more than seven percent of a bank's total subscribed shares; and

b) A juridical person shall not directly hold more than ten percent of a bank's total subscribed shares.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the maximum shareholding that may be held by Regional Government and their enterprises in a bank transformed from a micro-finance institution shall be determined by National Bank Directive.

፫/ ማንኛውም ሰው በባንክ ውስጥ በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ሊይዘው የሚችለው አጠቃላይ የአክሲዮን ድርሻ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

፬/ በአንድ ባንክ ውስጥ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ያለው ማንኛውም ባለአክሲዮን በሌላ ባንክ አክሲዮን መያዝ አይችልም።

፭/ ማንኛውም ሰው ከባንክ በተገኘ ብድር የአንድን ባንክ አክሲዮን መግዛት አይችልም። ይህን ክልከላ በመተላለፍ የአክሲዮን ግዥ ተፈጽሞ ሲገኝ መወሰድ ስላለበት እርምጃ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## ፲፬. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

፩/ ብሔራዊ ባንክ በማንኛውም ባንክ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ወይም የዳይሬክተሮች ስብሰባ ላይ የሚሳተፉ ታዛቢዎችን ሊመድብ ይችላል።

፪/ የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የባለአክሲዮኖችን ጥቅም ለማስከበር ወይም የባንኩን ዘርፍ መረጋጋትና ጤናማነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ብሔራዊ ባንክ የማንኛውንም ባንክ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በመጥራት ባንኩን በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ ውይይት እንዲደረግ እና ውሳኔ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል።

፫/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው መሠረት ብሔራዊ ባንክ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የጠራ እንደሆነ፦

ሀ) የስብሰባውን አጀንዳ ያዘጋጃል፤

ለ) የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ወይም በብሔራዊ ባንክ የተሰየመ ሌላ ማንኛውም ሰው ስብሰባውን ይመራል፤

3/ Maximum limit on aggregate direct and indirect shareholding by a person shall be determined by National Bank Directive.

4/ A shareholder with significant ownership in a bank shall not acquire shares in another bank.

5/ No person may buy shares of a bank using bank loans. Measures to be taken on purchase of shares against this provision shall be determined by National Bank Directive.

## 14. Shareholders General Meeting

1/ National Bank may assign observers to attend any general shareholders meeting or board meetings of a bank.

2/ Where it finds necessary in the interest of depositors or shareholders or the stability and soundness of the banking sector, National Bank may call a general shareholders meeting of a bank to discuss and resolve any issues related to the bank.

3/ Where the National Bank calls general shareholders meeting as stipulated under Sub Article (2) of this Article:

a) it shall prepare the agenda for the meeting;

b) its officer or any other person assigned by it shall preside over the meeting;

ሐ) የባለአክሲዮኖችን ጠቅላላ ጉባዔ ምልዐተ ጉባዔ እና በጉባዔው የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በሚመለከት በንግድ ሕጉ የተደነገጉት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፣ እና

መ) ከጉባዔው መካሄድ ጋር የተያያዙ ወጪዎች ጉዳዩ በሚመለከተው ባንክ ይሸፈናል።

**፲፭. <u>ድምጽ የመስጠት እና ኢኮኖሚያዊ መብቶችን ስለመገደብ</u>**

፩/ ብሔራዊ ባንክ እንደ አግባብነቱ፦

ሀ) በማንኛውም የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ላይ በወኪል አማካኝነት ሊሰጥ በሚችለው ድምጽ ብዛት፣

ለ) የባንክ ሠራተኞች እና የቦርድ አባላት የባለአክስዮኖች ስብሰባ ላይ በውክልና መሳተፍ ስለመቻላቸው እና

ሐ) ከባንኩ የተበደረ ማንኛውም ባለአክሲዮን በሚኖረው ድምጽ የመስጠት መብት ላይ ገደብ ሊያስቀምጥ ይችላል።

፪/ በማንኛውም ባንክ ውስጥ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ያለው አንድ ባለአክሲዮን ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ የሚወስናቸውን የሥነ ምግባርና የተገቢነት መስፈርቶች ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ የባለአክሲዮኑን ድምፅ የመስጠት መብት ሊያግድ፣ ባለአክሲዮኑ በባንኩ ውስጥ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ እንዲኖረው ካስቻለው የአክሲዮን ድርሻ የተወሰነውን እንዲያስተላልፍ ሊያስገድድ እና አክሲዮኑ በዚህ መልኩ እስኪተላለፍ እና ሌሎች ጉድለቶች በአግባቡ እስኪታረሙ ድረስ የትርፍ ክፍፍል ድርሻ እንዳይከፈል ሊያግድ ይችላል።

c) pertinent provisions of the Commercial Code with respect to quorum and resolutions of shareholders meeting shall apply; and

d) expenses incurred in relation to the meeting shall be borne by the concerned bank.

**15. <u>Limitations on Voting and Economic Rights</u>**

1/ National Bank may, as appropriate, limit:

a) the number of votes by proxy in any meeting of shareholders;

b) participation of employee and board of a bank in any meeting of shareholders through proxy; and

c) voting right of a shareholder, who borrowed from the bank.

2/ Where a shareholder with significant ownership in a bank fails to fulfill the prescribed ethical and propriety requirements, National Bank may suspend the voting rights of such person, require such person to dispose part of the share that enabled it to assume significant ownership in the bank, and suspend dividend until such shareholding is disposed and rectification of other identified deficiencies are duly made.

## ክፍል አምስት

## ስለባንክ ሠራተኞችና ዳይሬክተሮች

### ፲፮.የውጭ ሀገር ዜጎች በባንክ ውስጥ ስለሚቀጠሩበት ሁኔታ

፩/ ማንኛውም ባንክ ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ በሚሰጥ ፈቃድ በዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም በከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ የሥራ መደቦች ወይም ልዩ ዕውቀትን ወይም ሙያን በሚጠይቁ ሌሎች የሥራ መደቦች ላይ የውጭ ሀገር ዜጎችን በመመልመል ወይም በሠራተኛ ዝውውር አማካኝነት ከአምስት ዓመታት ላልበለጠ ጊዜ በጊዜያዊ ሠራተኛነት መቅጠር ይችላል። በአንድ ባንክ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ሠራተኞች ከፍተኛ ብዛት እና/ወይም መቶኛ ድርሻ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የአምስት ዓመት ጊዜ ሲያበቃ የሥራ መደቡ በኢትዮጵያ ዜጋ እንዲተካ እና እንዲሟላ መደረግ ይኖርበታል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም አንድ ባንክ በቂ ምክንያት አቅርቦ ጥያቄው በብሔራዊ ባንክ ከጸደቀለት በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተቀጠረ ወይም በሠራተኛ ዝውውር አማካኝነት የተመደበ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ሠራተኛ የአገልግሎት ዘመን ለተጨማሪ አምስት ዓመታት ሊራዘም ይችላል፡፡

## PART FIVE

## EMPLOYEES AND DIRECTORS OF A BANK

### 16. Employment of Foreign Nationals in a Bank

1/ A bank, after securing approval from the National Bank, may be allowed to employ foreign nationals for chief executive officer or senior executive officer positions or other positions requiring specialized knowledge or expertise through recruitment or staff transfer, on contract with a maximum term of five years. The maximum number and/or percentage share of foreign employees in a bank may be determined by National Bank Directive.

2/ Upon expiry of the five years period stated under Sub-Article (1) of this Article, the position shall be replaced and filled with Ethiopian national.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, if a bank files a request supported by adequate justification, National Bank may extend the service period of a foreign national hired or assigned as per Sub-Article (1) of this Article for additional five years period.

፬/ ማንኛውም ባንክ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ሰው ከቀጠረ ወይም በሠራተኛ ዝውውር አማካኝነት ከመደበ በኋላ በቂ እና አጥጋቢ በሆነ መልኩ ለኢትዮጵያውያን የዕውቀት እና የክህሎት ሽግግር መደረጉን ማረጋገጥ አለበት፤ እንዲሁም የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ሠራተኞች ምደባ ለኢትጵያውያን በአግባቡ የዕውቀትና የክህሎት ሽግግርን መደረጉን በሚያረጋግጥ ሁኔታ መከናወን ይኖርበታል።

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተቀጠረ ወይም በሠራተኛ ዝውውር አማካኝነት የተመደበ ማንኛውም የውጭ ሀገር ዜጋ በሌላ የውጭ ሀገር ዜጋ የተተካ እንደሆነ በምትክነት የተቀጠረው ወይም የተመደበው ሠራተኛ የአገልግሎት ዘመን ከመጀመሪያው ሠራተኛ የአገልግሎት ዘመን ላይ ከቀረው ጊዜ የበለጠ ሊሆን አይችልም።

፮/ ማንኛውም የውጭ ሀገር ዜጋ የሆነ ሠራተኛ ወይም ዳይሬክተር በብሔራዊ ባንክ የተቀመጡትን የአግባብነት እና የሥነ-ምግባር መስፈርቶች ሳያሟላ ከቀረ፣ በኢትዮጵያ የውስጥ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ ተሳትፎ ከተገኘ ወይም በማንኛውም የእምነት ማጉደል ወይም የማጭበርበር ወንጀል በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በሌላ ሀገር ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ባንኩ ሠራተኛውን ወይም ዳይሬክተሩን ወዲያውኑ ከሥራ በማሰናበት ጉዳዩን ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ ይኖርበታል።

4/ A bank after hiring or assigning foreign national through staff transfer shall ensure that knowledge and skill transfer to Ethiopian nationals is made adequately and satisfactorily and assignment of foreign national employees shall be made in a manner that ensures proper transfer of knowledge and skill to Ethiopian nationals.

5/ In the event a foreign national hired or assigned through staff transfer as per this Article is replaced by another foreign national, the replaced employee's service period shall not exceed the remaining term of the original service period.

6/ A bank shall immediately remove a foreign national employee or director if he fails to pass the fit and proper test prescribed by National Bank, is found involved in political affairs of Ethiopia or convicted of any offence involving a breach of trust or a fraud in Ethiopia or elsewhere and report same to National Bank.

፯/ የውጭ ሀገር ዜጎችን በባንክ ውስጥ ከመቅጠር ወይም በሠራተኛ ዝውውር ከመመደብ፣ ለውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ በብሔራዊ ባንክ ከመስጠት እና ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ከመቆጣጠር እንዲሁም አንድ ባንክ ለተተኪ ኢትዮጵያዊያን ሠራተኞች የሥልጠና መርሐ ግብር በማዘጋጀት የዕውቀት እና የክህሎት ሽግግር እንዲኖር የማድረግ ግዴታ እንዲወጣ ከማድረግ ጋር የተያያዙ ተጨማሪ ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

## ፲፯. የዳይሬክተሮች እና የሥራ አስፈጻሚዎች ሹመት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዳይሬክተር ታማኝ፣ ሀቀኛ፣ ጠንቃቃና መልካም ዝና ያለው እንዲሁም አግባብነት ባለው መመሪያ ውስጥ የተቀመጡትን የብቃት መመዘኛ መስፈርቶች በማንኛውም ጊዜ ለብሔራዊ ባንክ አጥጋቢ በሆነ መልኩ ማሟላት የሚችል ሰው መሆን አለበት።

፪/ የባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ገለልተኛ የሆኑ ዳይሬክተሮችን በውስጡ ማካተት ይኖርበታል።

፫/ የባንክ ሥራ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜም ሆነ በሌላ ማናቸውም ጊዜ የሚደረግ የማንኛውም ባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ሹመት በብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ካልፀደቀ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም።

፬/ ብሔራዊ ባንክ አዲስ የተመረጡ የባንክ ዳይሬክተሮችን ሹመት በጽሑፍ እስኪያጸድቅ ድረስ የነባር ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን ሳይቋረጥ መቀጠል ይኖርበታል።

7/ Any additional conditions related to employment or staff transfer of foreign nationals in a bank, issuance of work permit by National Bank, supervision of same in collaboration with pertinent Government organs and the responsibility of a bank in designing and providing training programs to substitute Ethiopian workers and ensuring transfer of knowledge and skills may be determined by National Bank Directive.

## 17. Appointment of Directors and Executive Officers of a Bank

1/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of Article 18 of this Proclamation, a director shall be a person with honesty, integrity, diligence, and good reputation and able at all times to pass the qualification of competency prescribed in the relevant Directive to the satisfaction of the National Bank.

2/ Board of Directors of a bank shall include independent directors.

3/ Appointment of any director, chief executive officer or senior executive officer of a bank at the time of licensing or at any time may not be valid unless written approval is granted by National Bank.

4/ The term of office of outgoing directors of a bank may not terminate until written approval for the incoming directors is granted by National Bank.

፭/ ብሔራዊ ባንክ፦

ሀ) ዳይሬክተሮች ማሟላት የሚገባቸውን የብቃት መመዘኛዎች፤

ለ) የአንድ ባንክ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሊኖረው የሚገባውን ዝቅተኛ የዳይሬክተሮች ቁጥር እና ገለልተኛ ዳይሬክተሮችን ጨምሮ ሊኖር ስለሚገባው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብጥር፤

ሐ) የአንድን ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባራት እና ኃላፊነቶች እንዲሁም መልካም የኩባንያ አስተዳደር፤

መ) አንድ ዳይሬክተር በማንኛውም ባንክ ሊያገለግል የሚችልበትን ከፍተኛ የሥራ ዘመንና በድጋሚ ለመመረጥ የሚያበቁትን ሁኔታዎች፤ እና

ሠ) ለዳይሬክተሮች የሚከፈለውን የክፍያ ጣሪያ፣ በሚመለከት

መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፮/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ቢኖርም የአንድ ባንክ ሠራተኞች የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው እንዲያገለግሉ የሚፈቀድ ወይም የማይፈቀድ መሆኑን በተመለከተ እንዲሁም የሚፈቀድ ከሆነ በአንድ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ በአባልነት እንዲያገለግሉ ሊመረጡ የሚችሉ የባንኩ ሠራተኞች ከፍተኛ ቁጥር በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

5/ National Bank may issue Directive on:

a) competence to be fulfilled by directors;

b) the minimum number and composition of directors, including independent directors in the membership of the board of a bank;

c) the duties and responsibilities of board of directors and manner of good corporate governance of a bank;

d) the maximum number of years a director may serve in any bank and the conditions for his re-election; and

e) the maximum amount of remuneration for directors.

6/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (4) of Article 18 of this Proclamation; National Bank may issue Directive to determine whether or not bank employees are permitted to serve as members of the board of directors of a bank and if allowed may determine the maximum number of employees of a bank who may be elected as members in the board of directors of the bank.

## ፲፰. ክልከላዎች

፩/በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ማንኛውም ሰው የባንክ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ መሆን አይችልም።

፪/ ብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ ካልፈቀደለት በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በሚገኝ በአመራር ጉድለት፣ በኪሳራ ወይም በሌሎች ማናቸውም ተያያዥ ምክንያቶች የተነሣ የፈረሰ ባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ የነበረ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባንኩ ሥራ አመራር ውስጥ በሌላ መልኩ የተሳተፈ ማንኛውም ሰው የባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ሊሆን ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሌላ ማንኛውም የባንክ ሥራ አመራር ውስጥ ሊሳተፍ አይችልም።

፫/ የማንኛውም ፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተር በተመሳሳይ ጊዜ የማንኛውም ባንክ ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም። በተጨማሪም አሥር በመቶና ከዚያ በላይ የባለቤትነት ድርሻው እንዲህ ባለው ዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚ የተያዘ የንግድ ድርጅት የባንኩ ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም።

፬/ ማንኛውም የባንክ ሠራተኛ የዚያው ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ወይም የማንኛውም ሌላ ባንክ ዳይሬክተር ሊሆን አይችልም።

## 18. Prohibitions

1/ No person who has been convicted of breach of trust or a fraud, whether in Ethiopia or elsewhere may be a director or an employee of a bank.

2/ Without prior approval of the National Bank, no person who had been a director, chief executive officer or senior executive officer or otherwise directly or indirectly participated in the management of any bank that wound up due to management failure or bankruptcy or any other related causes, whether in Ethiopia or abroad, may act as a director, chief executive officer or senior executive officer or otherwise directly or indirectly participate in the management of a bank.

3/ A director of a financial institution may not, at the same time, serve as a director of a bank. Moreover, a business entity in which such director or chief executive officer has ten percent or more equity interest may not serve as a director of the bank.

4/ An employee of a bank may not be a chairperson of the board of directors of that bank or a director of any other bank.

**፲፱. ከባንክ ሥራ አመራር ራስን ስለማግለል**

ማንኛውም የባንክ ዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባንክ ሥራ አመራር የሚሳተፍ ሰው፦

፩/ እርሱ ዳይሬክተር ወይም ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የሚሠራበት የንግድ ድርጅት ከስሬያለሁ ብሎ ያመለከተ ወይም በፍርድ ቤት የኪሳራ ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ ወይም የእራሱ ወይም የኩባንያው ንብረት በኪሳራ ምክንያት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ሥር የዋለበት ወይም ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት በባንክ የተወረሰበት እንደሆነ፤

፪/ የባንክም ሆነ ሌላ ብድር ወይም ግብር ባለመክፈሉ ተከሶ የተፈረደበት እንደሆነ፤

፫/ እራሱ ወይም እርሱ ዳይሬክተር ወይም ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የሚሠራበት የንግድ ድርጅት ከማናቸውም የፋይናንስ ተቋማት የተወሰዱ ብድሮች ጊዜያቸውን ጠብቀው ባለመከፈላቸው ምክንያት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት የተበላሸ የብድር መደብ ውስጥ የተካተቱ እንደሆነ፤ ወይም

፬/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወሰናቸውን ማናቸውም የብቃት መመዘኛዎች ያላሟላ እንደሆነ እራሱን ከባንክ ሥራ አመራር ማግለል አለበት።

**፳. በብሔራዊ ባንክ ስለሚወሰድ የማገድና የማሰናበት እርምጃ**

፩/ ብሔራዊ ባንክ በቂ ነው ብሎ በሚያምንበት ምክንያት የማንኛውንም ባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ከሥራ ማገድ ወይም ማሰናበት ይችላል።

**19. Cessation of Banking Management Functions**

Any person who is a director or chief executive officer or senior executive officer or otherwise participates, directly or indirectly, in the management of a bank shall cease to exercise such function if:

1/ he or the business organization in which he is a director or executive officer, has instituted bankruptcy proceedings or declared bankrupt, or his or the business organization assets have been sequestrated because of bankruptcy or been foreclosed by a bank because of failure to repay a loan granted by the bank;

2/ he has been convicted of default on repayments of bank or other credits or tax payment;

3/ he or the business organization in which he is a director or executive officer carries non-performing loans, as defined by National Bank Directive, from any financial institutions; or

4/ he fails to fulfill any of the competence requirements set by National Bank.

**20. Suspension and Removal Measures to be Taken by National Bank**

1/ National Bank may, for sufficient cause, suspend or remove a director, a chief executive officer or a senior executive officer of a bank.

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ ሲባል “በቂ ምክንያት” የሚለው የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ እና ፲፰ የተደነገጉትን አለማክበር፤

ለ) ማንኛውም ባንክ የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎችን በስፋት ጥሶ ሲገኝ፤ እና

ሐ) በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት የሚወሰን ሆኖ የማንኛውም ባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ የፈፀመው ማንኛውም ድርጊት የፋይናንስ ክፍለ ኢኮኖሚውን መረጋጋት፣ ኢኮኖሚውን ወይም የሕዝብን ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል እንደሆነ።

፫/ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውንም የባንክ ዳይሬክተር ከኃላፊነት በሚያሰናብትበት ጊዜ የዳይሬክተሩ መሰናበት የቀሪዎቹን ዳይሬክተሮች ቁጥር ከአጠቃላይ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከግማሽ በታች የሚያወርደው ከሆነ ብሔራዊ ባንክ ወዲያውኑ የዳይሬክተሮች ቦርዱን ኃላፊነት ተረክቦ በሠላሳ ቀናት ውስጥ የባለአክሲዮኖች ስብሰባ በመጥራት በተሰናበተው (ቱት) ዳይሬክተር (ሮች) ምትክ ምርጫ እንዲካሄድ ያደርጋል።

፬/ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውንም የባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ከሥራ ያሰናበተ እንደሆነ የዚያ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ክፍት ቦታውን የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች የሚያስቀምጧቸውን መስፈርቶች በሚያሟላ ሰው ወዲያውኑ መተካት አለበት።

2/ For the purpose of Sub-Article (1) of this Article, “sufficient cause” shall include the following:

a) failure to comply with the provisions of Article 17 and 18 of this Proclamation;

b) gross violation of National Bank Directives and other relevant laws by the bank; and

c) any action carried out by director, chief executive officer or a senior executive officer of a bank detrimental to the stability of the financial sector, the economy or the general public interest; to be determined by National Bank Directive.

3/ Where National Bank removes a director of a bank and as a result of the removal the number of surviving directors is less than half of the board of directors, it shall immediately assume the powers of the board of directors and shall, within thirty days call a meeting of shareholders to elect director/s to replace the removed director/s.

4/Where the National Bank removes the chief executive officer or senior executive officer of a bank, the board of directors of that bank shall fill the vacant post immediately with a person who fulfills the required criteria set by National Bank Directive and other relevant laws.

## ክፍል ስድስት

## የፋይናንስ ግዴታዎችና ገደቦች

**፳፩. ተፈላጊውን ካፒታል ስለመያዝ**

፩/ ባንኮች መያዝ ያለባቸው አነስተኛ የካፒታል መጠንና መጠባበቂያ እንዲሁም እነዚህ የሚሰሉባቸው ቀመሮች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ።

፪/ ብሔራዊ ባንክ እያንዳንዱ ባንክ ያለውን የሥራ ባህሪ እና የአደጋ ተጋላጭነት መጠን እንዲሁም ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ አንድ ባንክ ከዝቅተኛው መጠን ከፍ ያለ ካፒታል እና መጠባበቂያ እንዲይዝ በየጊዜው ሊያስገድድ ይችላል።

፫/ ብሔራዊ ባንክ የማንኛውም ባንክ ካፒታል ከተወሰነው አነስተኛ መጠን በታች ነው ብሎ ሲያምን ባንኩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሁኔታውን ለማስተካከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንዲወስድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

፬/ ማንኛውም ባንክ በካፒታሉ ላይ ያሉ ችግሮች በሙሉ መወገዳቸው በብሔራዊ ባንክ ሳይረጋገጥ ማንኛውንም የትርፍ ድርሻ ማወጅ፣ የባለአክሲዮኖች ሒሣብ ውስጥ ማስገባት ወይም ለባለአክሲዮኖች መክፈል አይችልም።

**፳፪. ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሒሳብ ስለመያዝ**

፩/ ማንኛውም ባንክ የእያንዳንዱ ሒሳብ ዓመት መጨረሻ ላይ ካገኘው የተጣራ ትርፍ ቢያንስ ሀያ አምስት በመቶ ወደ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሒሳቡ ማዛወር አለበት።

## PART SIX

## FINANCIAL OBLIGATIONS AND LIMITATIONS

**21. Maintenance of the Required Capital**

1/ The minimum capital and reserves to be maintained by banks and the rules for their computation shall be determined by National Bank Directive.

2/ Based on the type of business and risk profile of each individual bank, as well as international standards, National Bank may require a bank to hold capital and reserves in excess of the minimum required from time to time.

3/ Where the National Bank considers that the capital of a bank is below the prescribed minimum, it may require the bank to take, within a specified period of time, measures necessary to rectify the situation.

4/ Unless the National Bank approves that all impairments of the bank's capital are rectified, no bank may at any time declare, or credit the account of, or pay to shareholders any dividend.

**22. Maintenance of Legal Reserve**

1/ A bank shall, at the end of each financial year, transfer to its legal reserve account at least twenty five percent of its net profit.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የባንኩ የመጠባበቂያ ሒሳብ ከካፒታሉ ጋር እኩል በሚሆንበት ጊዜ ባንኩ ከተጣራ ትርፉ ላይ በየዓመቱ የሚይዘው የመጠባበቂያ ሒሳብ መጠን ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ ብሔራዊ ባንክ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሒሳብ ዝቅ የሚደረግባቸውን ሁኔታዎች በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

**፳፫. በቂ ገንዘብ-አከል ንብረትና የመጠባበቂያ ገንዘብ ስለመያዝ**

፩/ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ማንኛውም ባንክ በቂ ገንዘብ-አከል ንብረቶችን መያዝ አለበት።

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም “ገንዘብ-አከል ንብረት” ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

ሀ) ጥሬ ገንዘብ፤

ለ) በብሔራዊ ባንክ ያለ ተቀማጭ ገንዘብ፤እና

ሐ) በብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ተቀባይነት አላቸው ተብለው የሚወሰኑ ሌሎች ገንዘብ-አከል ንብረቶች።

፫/ እያንዳንዱ ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በብሔራዊ ባንክ በተከፈተ ሒሳብ መጠባበቂያ ገንዘብ በጥሬ ገንዘብ ማስቀመጥ አለበት።

፬/ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት የሚሰጥ ባንክ “የትርፍ ማረጋጊያ መጠባበቂያ” እና “የኢንቨስትመንት አደጋ መጠባበቂያ” እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ መጠባበቂያዎችን ከብሔራዊ ባንክ በሚሰጥ ፈቃድ ሊይዝ ይችላል፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, when the legal reserve equals the capital of the bank, the amount to be retained by the bank as a legal reserve from the net profit each year shall be determined by National Bank Directive.

3/ National Bank may, by Directive, specify the circumstances under which the legal reserve account may be reduced.

**23. Maintenance of Adequate Liquidity and Reserve Balance**

1/ A bank shall maintain adequate liquid assets in accordance with the Directive to be issued by National Bank.

2/ For the purpose of Sub-Article (1) of this Article, “Liquid Assets” shall include:

a) cash;

b) deposits with the National Bank; and

c) such other assets as the National Bank may declare to be liquid assets from time to time.

3/ A bank shall maintain a cash reserve balance with the National Bank in accordance with the Directive to be issued by National Bank.

4/ A bank offering interest-free banking services may maintain "Profit Stabilization Reserve" and "Investment Risk Reserve" as well as other related reserves with permission from the National Bank.

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ገንዘብ-አከል ንብረትና የመጠባበቂያ ገንዘብ ግዴታዎችን ያላሟላ ማንኛውም ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የገንዘብ መቀጫ እንዲከፍል እና ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱበት ይደረጋል።

**፳፬. ፕሮቪዥን፣ የእርጅና ቅናሽ የመያዝ እና ኪሳራ የመሸፈንና የማጣጣት ግዴታዎች**

፩/ ማንኛውም ባንክ ለሚከተሉት ሒሳቦች ፕሮቪዥን መያዝ አለበት፡-

ሀ) ለተበላሹ ብድሮች፣ ቅድመ ክፍያዎች እና ሌሎች ተሰብሳቢ ሒሳቦች፤

ለ) ባንኩ የካፒታልና መጠባበቂያ ግዴታዎቹን ማሟላቱን ለማረጋገጥ ስሌት ሲሠራ ከግምት ውስጥ ላልገቡ ዕዳዎችና ሊያጋጥም ለሚችል የዕዳ ተጠያቂነት ጭምር በዋስትና ለተሰጡና በዋስትና መሠረት ባንኩ ከሕዝብ ለሚፈለግበት ዕዳ ክፍያ ሊያገለግሉ ለማይችሉ ንብረቶች ዋጋ፤ እና

ሐ) ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሚወሰኑ ሌሎች ሒሳቦች።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚያዘው የፕሮቪዥን መጠንና የሚሰላበት ዘዴ ሰፊ ተቀባይነት ባላቸው ዓለም አቀፍ የሒሳብ አያያዝ ደረጃዎች መሠረት ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ ማንኛውም ባንክ ለቋሚ ንብረቶች የሚይዘውን የእርጅና ቅናሽ ተቀባይነት ባለው የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃ መሠረት ማስላት አለበት።

5/ A bank that fails to meet the liquidity and reserve requirements in accordance with this Article shall be subject to a fine and other administrative measures specified by National Bank Directive.

**24. Provisioning, Depreciation Loss Coverage and Amortization Requirements**

1/ Provisions shall be made by a bank for the following items:

a) loans and advance that are impaired or other uncollected receivables;

b) the value of any assets lodged or pledged to secure liabilities including contingent liabilities, that are not included in the calculation made to ascertain the bank's compliance with capital and reserves requirement, where the effect of such lodging and pledging is that such assets are not available for the purpose of meeting the liabilities of the bank to the public; and

c) such other items as the National Bank may prescribe by its Directive.

2/ The provisions to be made pursuant to Sub-Article (1) of this Article and the manner of calculating the provisions shall be prescribed by National Bank Directive in accordance with widely accepted international accounting standards.

3/A bank shall depreciate its fixed assets in accordance with acceptable International Financial Reporting Standard.

፬/ ማንኛውም ባንክ የካፒታል ወጪዎችን ቢበዛ በአምስት ዓመት ውስጥ ማጣጣት አለበት።

፭/ ማንኛውም ባንክ በሥራ ሒደት የደረሱና የተጠራቀሙ ኪሳራዎችን በየዓመቱ በሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት። እንዲህ ዓይነት ኪሣራዎች ሙሉ በሙሉ እስከሚሸፈኑ ድረስ ባለአክሲዮኖች ትርፍ አይከፋፈሉም።

፮/ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ባንክ የፕሮቪዥን፣ የእርጅና ቅናሽ ሒሣብ እና የካፒታል ወጪዎች ማጣጣት ግዴታዎቹን ማክበሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆነውን ስሌት በሚሠራበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፫) እና (፬) መሠረት የተያዘውን ፕሮቪዥን፣ የቋሚ ንብረቶች የእርጅና ቅናሽ ሒሣብና የተደረገውን የካፒታል ወጪዎች ማጣጣት በቂነት ታሳቢ በማድረግ አስፈላጊውን ማስተካከያ ያደርጋል።

፯/ ማንኛውም ባንክ፦

ሀ) ማንኛውም የባንኩ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ በቸልተኝነት ወይም እምነት በማጉደል የሚያደርሰውን ኪሳራ እና በሌላ ማንኛውም ያልተጠበቀ ክስተት ወይም ሁኔታ የተነሳ የሚደርስ ማንኛውንም ኪሳራ ለመሸፈን የሚያስችልና ለዚሁ ጉዳይ ብቻ የተያዘ የመጠኑ በቂነት በብሔራዊ ባንክ የተረጋገጠ ልዩ የመጠባበቂያ ሒሣብ ይይዛል፣ ወይም

ለ) እንዲህ ዓይነቱን ኪሳራ ለመሸፈን የመጠኑና የውሉ በቂነት በብሔራዊ ባንክ የተረጋገጠ የመድን ውል ይገባል፤

ሐ) ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃ አተገባበር ጋር በተያያዘ አስፈላጊ የሆኑ መጠባበቂያዎችን ይይዛል።

4/ A bank shall amortize its capitalized expenditure within a maximum period of five years.

5/ A bank shall fully cover its operating and accumulated losses from its annual net profit. No dividend shall be paid to shareholders until such losses are fully covered.

6/ National Bank shall take into account the adequacy of the provisions, depreciations and amortization stated under Sub-Articles (1), (3) and (4) of this Article, and make the necessary adjustments, in making the calculations necessary to ascertain that a bank is complying with the provisions and capital and reserves.

7/ A bank shall:

a) either maintain a special reserve account that is, in the opinion of the National Bank, adequate and is reserved exclusively for any loss resulting from the negligence or dishonesty of any director or employee of the bank and any losses caused by any other unexpected events or circumstances; or

b) insure itself against such losses to an amount and on terms that the National Bank deems adequate;

c) maintain necessary reserves arising from adoption and implementation of International Financial Reporting Standard.

**፳፭. በአንዳንድ የባንክ አገልግሎቶች ላይ ስለሚጣሉ ገደቦች**

፩/ ማንኛውም ባንክ በሚያደርገው ኢንቨስትመንትና ለባንኩ ተዛማጅነት ያላቸውን ጨምሮ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለማንኛውም ሰው በሚሰጠው ብድር ወይም ሌላ የብድር አገልግሎት፣ የገንዘብ ዋስትና ወይም ባንኩ በሚገባቸው ሌሎች ግዴታዎችና ውሎች ላይ የሚጣሉ ገደቦችና ሁኔታዎችን በሚመለከት ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ያወጣል።

፪/ ማንኛውም ባንክ የራሱን አክሲዮን በዋስትና በመያዝ ብድር ማበደር አይችልም።

## ክፍል ሰባት
## ስለፋይናንስ መዝገቦችና የውጭ ኦዲተር ሹመት

**፳፮. ስለፋይናንስ መዝገቦች**

፩/ ማንኛውም ባንክ፦

ሀ) የባንኩን ሁኔታ በግልጽና በትክክል ለማሳየት፤

ለ) የባንኩን ሥራና የገንዘብ ቁመና ለማስረዳት፤ እና

ሐ) ባንኩ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ሥራውን እያካሄደ መሆን ያለመሆኑን ብሔራዊ ባንክ መወሰን እንዲችል ማረጋገጥ በሚያስችል፤

ሁኔታ የፋይናንስ መግለጫ መዝገቦችን መያዝ አለበት።

፪) ማንኛውም ባንክ ለእያንዳንዱ የሥራ እንቅስቃሴ ዓይነት መዝገብና ሰነዶችን መያዝ አለበት። የእነዚህን ሰነዶች አቀራረብና በውስጣቸውም የሚመዘገቡትን ጉዳዮች ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

**25. Limitations on Certain Banking Business Services**

1/ The conditions and limitations on investments of banks, loans or other credit facilities, guarantee or any other commitment or contracts given by a bank, directly or indirectly to a person, including related parties shall be determined by National Bank Directive.

2/ No bank shall grant loans against the security of its own shares.

## PART SEVEN
## FINANCIAL RECORDS AND APPOINTMENT OF EXTERNAL AUDITOR

**26. Financial Records**

1/ A bank shall keep records of financial statements as are necessary to:

a) exhibit clearly and correctly the state of its affairs;

b) explain its transactions and financial position; and

c) enable the National Bank to determine whether the bank had complied or not complied with the provisions of this Proclamation, Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation.

2/ A bank shall register and keep documents for each type of transaction. The type of format and required entries of such documents shall be determined by National Bank Directive.

**፳፯. የውጭ ኦዲተሮችን ስለመሾም**

፩/ ማንኛውም ባንክ የውጭ ኦዲተሮችን መሾም ያለበት ሲሆን የኦዲተሮቹ ሹመትም በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት። ብሔራዊ ባንክ በቂ ዕውቀት ወይም ገለልተኝነት የለውም ወይም ተቀባይነት ያላቸውን የሙያ ደረጃዎችን ሥራ ላይ አያውልም ወይም አይከተልም ብሎ ያመነውን የውጭ ኦዲተርን ሹመት ውድቅ የማድረግ እና የመሰረዝ ሥልጣን አለው።

፪/ የሚከተሉት ሰዎች የማንኛውም ባንክ የውጭ ኦዲተር ሆነው መሾም አይችሉም፡-

ሀ) የባንኩ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) የሚሸፈን ሰው የትዳር ጓደኛ ወይም በአንደኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ፤ እና

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ ወይም /ለ/ የሚሸፈን ሰው የሥራ ባልደረባ ወይም ሽሪክ የሆነበት የኦዲት ድርጅት።

፫/ ማንኛውም ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የውጭ ኦዲተር ያልሾመ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ኦዲተር ይሾምለታል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተሾመ የውጭ ኦዲተር የአገልግሎት ዘመን እስከ ቀጣዩ የባንኩ ዓመታዊ መደበኛ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ድረስ ይሆናል።

**27. Appointment of External Auditors**

1/ A bank shall appoint external auditors; and the appointment of such auditors shall be approved by National Bank. National Bank shall have the power to reject and rescind the appointment of an external auditor who is deemed to have inadequate expertise or independence, or is not subject to or does not adhere to established professional standards.

2/ A person may not be qualified for appointment as an external auditor of a bank if:

a) he is a shareholder, director or employee of that bank;

b) he or she is a spouse or relative by consanguinity or affinity to the first degree to a person falling within the categories provided under paragraph (a) of this Sub-Article ; or

c) it is a firm of auditors of which any partner or a staff member falls within the categories provided under paragraph (a) or (b) of this Sub-Article.

3/ If a bank fails to appoint an external auditor in accordance with the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the appointment of external auditor of such bank shall be made by National Bank.

4/ An external auditor appointed in accordance with Sub-Article (3) of this Article shall hold office until the next annual general ordinary meeting of the shareholders of the bank.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ኦዲተር የተሾመለት ማንኛውም ባንክ ለተሾመው ኦዲተር የሚከፈለውን የአገልግሎት ክፍያ ብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው ትእዛዝ መሠረት መፈጸም አለበት።

፮/ በማናቸውም ባንክ የውጭ ኦዲተር ሆኖ የተሾመ ሰው በመደበኛ የሥራ ሂደትና ለማንኛውም ሰው ከሚሰጠው አገልግሎት ባልተለየ ሁኔታ ካልሆን በስተቀር በዚያው ባንክ መያዝ ወይም ከባንኩ ማንኛውንም ዓይነት ብድር ወይም ሌላ አገልግሎት ማግኘት አይችልም።

፯/ የማንኛውም ባንክ የውጭ ኦዲተር የተሾመበት የአገልግሎት ጊዜ ሳያበቃ በማንኛውም ምክንያት ሥራውን ያቋረጠ እንደሆነ ባንኩ ይህንኑ ለብሔራዊ ባንክ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

፰/ የውጭ ኦዲተር የሚሾምበት ሁኔታ፣ የውጭ ኦዲተር የሹመት ዘመን፣ የኦዲት ሥራ ጥልቀትና ሽፋን፣ የኦዲት ባለሙያዎች ዕውቀትና ሙያ፣ በየጊዜው አዲስ ኦዲተር ከመሾም ጋር የተያያዙ መስፈርቶች እንዲሁም ኦዲት ሪፖርት ለብሔራዊ ባንክ እና ለባንኩ ዓመታዊ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

## ፳፰. የውጭ ኦዲት ሪፖርት

፩/ የማንኛውም ባንክ የውጭ ኦዲተር የኦዲት ግኝቶችንና ምክረ-ሀሳቦችን በማካተት የተሟላ የኦዲት ሪፖርት ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ መሠረት ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት።

5/ A bank for which an auditor is appointed in accordance with Sub-Article (3) of this Article shall pay remunerations of the auditor as directed by National Bank.

6/ A person appointed as an auditor of a bank may not operate an account with, or be granted any type of loan or facility from that bank except in the normal course of business and at arm's length.

7/ A bank, the external auditor of which, for any reason, terminates his service before his term of office ends, shall forthwith notify such fact to the National Bank.

8/ Manner of appointment of an external auditor, tenure of external auditor, depth and coverage of audit work, knowledge and expertise of audit professionals, rotation requirements, time limit for submission and presentation of audit reports to the National Bank and to a bank's annual general shareholders meeting and other related requirements shall be determined by National Bank Directive.

## 28. External Audit Report

1/ The auditor of a bank shall submit to the National Bank a complete audit report, including audit findings and recommendations, within the time limit set by National Bank.

፪/ ብሔራዊ ባንክ የቀረበውን የውጭ ኦዲት ሪፖርት ካላመነበት ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመተባበር ሁለተኛ የሒሳብ ምርመራ እንዲከናወን ወይም ሌላ የውጭ ኦዲተር በአስቸኳይ እንዲሾም በማድረግ ሒሳቡ እንደገና እንዲመረመር ማድረግ ይችላል። አዲስ የተሾመው የውጭ ኦዲተር የአገልግሎት ክፍያ በብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው ትእዛዝ መሠረት በባንኩ ይከፈላል።

፫/ የማንኛውም ባንክ የውጭ ኦዲተር የሒሳብ ምርመራ ተግባሩን በሚያከናውንበት ወቅት፦

ሀ) የዚህ አዋጅ፣ የሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎች በከፍተኛ ደረጃ መጣሳቸውን ወይም ያለመከበራቸውን፤

ለ) በባንኩ ወይም በማንኛውም የባንኩ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ የማጭበርበር ወይም ሌላ የእምነት ማጉደል ወንጀል መፈጸሙን፤

ሐ) የባንኩን ካፒታል ፳፭ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ መጠን የሚቀንስ፣ ወይም ከ፳፭ በመቶ በታች በሆነ መጠን የሚቀንስ ቢሆንም ባንኩ ለጥንቃቄ ሲባል በብሔራዊ ባንክ የተቀመጡ የጤናማነት መለኪያ መስፈርቶች ማክበሩን መቀጠል እንዳይችል የሚያደርግ ኪሳራ የደረሰ መሆኑን፤

መ) ባንኩ ሥራውን ማካሄዱን ለመቀጠል ያለውን አቅም የሚጎዳ ወይም የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የአበዳሪዎችን ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል ከባድ የሆነ የአሠራር ጉድለት የተከሰተ መሆኑን፤

2/ The National Bank, if not satisfied with the external audit report, may in collaboration with pertinent regulatory organ initiate and order a second audit or require the prompt appointment of a new auditor who shall make an independent audit. The remunerations of the newly appointed external auditor shall be paid by the bank as directed by National Bank.

3/ Where the external auditor of a bank, in the course of the performance of his audit duties, finds out that:

a) there has been a serious breach of, or non-compliance with, the provisions of this Proclamation, other relevant laws or Regulations or Directives issued in accordance with this Proclamation;

b) a criminal offence involving fraud or other dishonesty has been committed by the bank or any of its directors or employees;

c) losses have been incurred which reduce the total capital of the bank by twenty five percent or more or in an amount less than twenty five percent, but in a way that no-longer allows the bank to comply with the prudential requirements of National Bank;

d) serious irregularities have occurred, which may jeopardize the bank's ability to continue conducting its business or the interest of its depositors or creditors;

ረ) ባንኩ ግዴታውን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለው በቂ የገንዘብ አከል ንብረት የሌለው መሆኑን፤ ወይም

ሠ) ሌሎች ማናቸውም ከባድ የአሠራር ጉድለቶች ወይም ጥፋቶች ተከስተው መገኘታቸውን፤

ሲደርስበት ጉዳዩን ለብሔራዊ ባንክ እና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

፬) ብሔራዊ ባንክ በማንኛውም ጊዜ የማንኛውንም የባንክ የውጭ ኦዲተር ጠርቶ ኦዲት የሚያደርገውን ባንክ የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውይይት ሊያካሂድ ይችላል።

## ክፍል ስምንት
## መረጃ ስለመስጠት፣ ሪፖርት ስለማቅረብ እና በባንኮች ላይ ስለሚካሄድ ምርመራ

### ፳፱. ሪፖርት ስለማቅረብ እና መረጃ ስለመስጠት

፩/ ማንኛውም ባንክ የተፈረመ የፋይናንስ መግለጫዎችንና ሌሎች በብሔራዊ ባንክ የሚወሰኑ ሪፖርቶችን ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ፣ የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ እና የማስገቢያ ዘዴ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት።

፪/ ማንኛውም ባንክ፦

ሀ) በኦዲተር የተመረመረና የሥራ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ የሒሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎችን በሁሉም የባንኩ የሥራ ቦታዎች፣ ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች ግልጽ በሆነ ቦታ ዓመቱን ሙሉ እንዲታዩ ማድረግ አለበት፤ እና

ለ) የሒሳብ ሚዛን እንዲሁም የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ማብራሪያ ጽሑፎችን አባሪ በማድረግ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና በባንኩ ድረ-ገጽ ላይ አሳትሞ ያወጣል።

e) the bank is deemed unable to meet any of its obligations due to lack of sufficient liquid assets; or

f) any other grave irregularities or offences have occurred;

he shall immediately report the matter to the National Bank and other concerned bodies.

4/ National Bank may call at any time the external auditor of a bank to discuss issues related to the bank being audited by the auditor.

## PART EIGHT
## INFORMATION DISCLOSURE, REPORT SUBMISSION AND EXAMINATION OF BANKS

### 29. Report Submission and Information Disclosure

1/ Every bank shall submit to the National Bank duly signed financial statements and other reports as prescribed by it, in accordance with reporting template, submission modality and time period determined by National Bank.

2/ Every bank shall:

a) exhibit at every place of its business, including its branches and sub-branches, in a conspicuous place throughout the year, a copy of the last audited balance sheet and profit and loss account in respect of all of its operations; and

b) cause such balance sheet, and profit and loss account, together with the notes thereto, to be published in a newspaper of wide circulation and in its website.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የፋይናንስ መግለጫዎችን ለሕዝብ እይታ ዝግጁ የማድረጉና የማሳተሙ ተግባር የባለአክሲዮኖች ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በተካሄደ በሁለት ሳምንታት ውስጥ መፈጸም አለበት።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም የመንግሥት ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሒሳብ ዓመቱ በተዘጋ በአራት ወራት ውስጥ የፋይናንስ መግለጫዎቹን ለማጽደቅ ተመሳሳይ ስብሰባ ማድረግ አለበት፤ የፋይናንስ መግለጫዎችን ለሕዝብ እይታ ዝግጁ የማድረጉና ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና በድረ ገጹ ላይ የማሳተሙ ተግባር የመንግሥት ባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የፋይናንስ መግለጫዎቹን ባጸደቀ በሁለት ሳምንታት ውስጥ መፈጸም አለበት።

፭/ ብሔራዊ ባንክ አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ማናቸውንም መረጃዎች ከባንኮች መጠየቅና ማግኘት ይችላል፤ ሆኖም መረጃዎቹ፡-

ሀ)የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም ሲባል፤

ለ)የባንኮችን የፋይናንስ ጤናማነት ለማረጋገጥ፤

ሐ) በሕግ ለተፈቀደላቸው ሰዎች፤

መ) ብሔራዊ ባንክ ተጠሪ ለሆነለት አካል፤

ሠ) በፍርድ ቤት በመታዘዙ፤ ወይም

ረ) ኢትዮጵያ የገባችባቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ለመወጣት ሲባል፤

ካልሆነ በቀር ለማንኛውም ሰው ተላልፈው አይሰጡም።

3/ The exhibition and publishing of financial statements pursuant to Sub-Article (2) of this Article shall occur within two weeks after the annual ordinary general shareholders' meeting.

4/ Notwithstanding Sub-Article (3) of this Article, board of directors of a Government owned bank shall conduct a similar meeting to approve its financial statements within four months after closing its financial year; exhibition and publishi ng of financial statements in a newspaper of wide circulation and in its website shall occur within two weeks after approval of the financial statements by the board of directors of the Government owned bank.

5/ The National Bank may collect any appropriate information from banks; provided, however, that such information may not be disclosed to any person unless the disclosure is:

a) made for the purpose of implementing the provisions of this Proclamation;

b) required to ensure the financial soundness of banks;

c) made to recipients who are legally authorized to obtain such information;

d) made to the body to which the National Bank is accountable;

e) ordered by a court; or

f) required for the purpose of meeting obligations under international agreements which Ethiopia entered into.

፮/ የማንኛውም ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሁኔታዎች በባንኩ ሲከሰቱ ወይም ሊከሰቱ ይችላሉ ብሎ ሲገምት ሁኔታውን በጋራም ሆነ በተናጠል ወዲያውኑ ለብሔራዊ ባንክ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) ለገንዘብ አስቀማጮች እና ለሌሎች አበዳሪዎች ያለበትን ግዴታ ባንኩ መወጣት የማይችል ሲሆን፤

ለ) ለገንዘብ አስቀማጮች ወይም ለሌሎች አበዳሪዎች ክፍያዎችን በወቅቱ ለመፈጸም ባንኩ ሊሳነው የሚችል ከሆነ፤ ወይም

ሐ) ባንኩ የሚገኝበት ሁኔታ መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ ፍሰት እና ጤናማነቱ ላይ አደጋ የሚጥል እንደሆነ።

**፴. <u>በባንኮች ላይ ስለሚካሄድ ምርመራ</u>**

፩/ ብሔራዊ ባንክ በቦታው ሳይገኝ ከሚያደርገው ምርመራ በተጨማሪ በየጊዜው ወይም በማንኛውም ጊዜ ያለ ቅድመ ማስጠንቀቂያ በማንኛውም ባንክ ላይ በቦታው ተገኝቶ ምርመራ ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ ይችላል።

፪/ ከጠቅላላው ገንዘብ አስቀማጮች በቁጥር አንድ አምስተኛ ወይም በባንኩ ዘንድ ካለው ጠቅላላ ገንዘብ ውስጥ አንድ ሦስተኛ አስቀማጭ የሆኑ አመልካቾች በአንድ ባንክ ላይ ምርመራ ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን የሚያስረዳ መረጃ አያይዘው ጥያቄ ካቀረቡ ወይም ከኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ጥያቄ ከቀረበ ብሔራዊ ባንክ ማመልከቻ የቀረበበት ባንክ በጤናማ ሁኔታ ላይ መገኘቱንና የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴ በመምራት ሂደት ውስጥ መከበራቸውን ለማረጋገጥ ሚስጥራዊነቱን በጠበቀ መንገድ ምርመራ ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ለማድረግ ይችላል።

6/ The board of directors of a bank shall, jointly or severally, immediately report in writing to the National Bank where the following happened or likely to happen that the bank:

a) cannot meet its obligations to its depositors and other creditors;

b) is possibly unable to make payments on time to depositors or other creditors; or

c) is in a state of condition detrimental to its smooth business operation and soundness.

**30. <u>Examination of Banks</u>**

1/ In addition to off-site examination, the National Bank may, periodically or at any time, without prior notice, make, or cause to be made, an on-site examination of a bank.

2/ Where an application, accompanied with supporting evidence, is made to the National Bank by one-fifth of the total number of depositors or by any number of depositors holding not less than one-third of the deposits of a bank, or upon request by Ethiopian Deposit Insurance Fund, the National Bank shall examine, or cause to be examined, under conditions of secrecy, the affairs of the bank in order to determine whether it is in a sound condition and the provisions of this Proclamation, Regulations and Directives issued pursuant to this Proclamation have been complied with.

፫/ በባንኮች ላይ የሚካሄድ የምርመራ ሥራ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የብሔራዊ ባንክ መርማሪዎች ወይም ለዚህ ዓላማ ሲባል ብሔራዊ ባንክ በሚቀጥራቸው ሌሎች እምነት በሚጣልባቸውና ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች ሊካሄድ ይችላል።

፬/ በማንኛውም ባንክ ላይ ምርመራ እንዲያካሂዱ በብሔራዊ ባንክ የተመደቡ ሰዎች ምርመራውን በሚገባ ለማከናወን እንዲያስችላቸው የባንኩን መዝገቦችና አሠራሮች በተመለከተ መረጃዎችንና ማብራሪያዎችን የባንኩ ሠራተኞች እንዲሰጧቸው የመጠየቅ ሥልጣን አላቸው።

፭/ ማንኛውንም ባንክ በመመርመር ሂደት የተሰበሰቡ መረጃዎች ምርመራውን ባካሄዱት ሰዎች እና መረጃው በቀረበላቸው የሥራ ኃላፊዎች በሚስጥር መያዝ አለበት።

**፴፩. <u>የምርመራ ሪፖርት</u>**

፩/ የምርመራው ረቂቅ ሪፖርት ለተመርማሪው ባንክ እንዲደርሰው ተደርጎ በሪፖርቱ ላይ አስተያየቱን እንዲሰጥ ዕድል ይሰጠዋል።

፪/ ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው የምርመራ ሪፖርት ይዘት፦

ሀ) ምርመራውን ባካሄዱት ሰዎች እንዲሁም ምርመራው በተደረገበት ባንክ ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች፤ እና

ለ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ስለማቋቋም እና አሠራሩን ለመወሰን የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም ወይም የሕዝብን ጥቅም ለማስከበር ሲባል ካልሆነ በቀር በብሔራዊ ባንክ በሚስጥር መያዝ አለበት።

3/ Examination of banks may be carried out by one or more examiners of the National Bank or by trustworthy and qualified professionals employed by National Bank for this purpose.

4/ Persons assigned by National Bank to examine any bank are authorized to request from employees of the examined bank such information and explanation on the records and transactions of the examined bank that are necessary for the effectiveness of carrying out the examination.

5/ The information gathered in the course of the examination of any bank shall be maintained as confidential by the persons carrying out the examination and management members to whom the information is availed for.

**31. <u>Examination Report</u>**

1/ The draft examination report shall be communicated to the examined bank and the examined bank shall be given an opportunity to express its views on the report.

2/ The content of the examination report submitted to the National Bank shall be considered as confidential by:

a) the persons who carried out the examination, and the directors and employees of the examined bank; and

b) the National Bank, unless it is for the purpose of implementing the provisions of this Proclamation or Establishment and Operation of Ethiopian Deposit Insurance Fund Regulation or to the interest of the public;

## ፴፪. ፈጣን የማስተካከያ እርምጃዎች

፩/ ተመርማሪው ባንክ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች እና መመሪያዎች ያልተከተለ ወይም በተሰጠው የባንክ ሥራ ፈቃድ የተመለከቱ ግዴታዎችን ያልፈጸመ መሆኑ ወይም ባንኩን ወይም የባንክ ሥርዓቱን አደጋ ላይ ሊጥሉ በሚችሉ አስተማማኝ ወይም ጤናማ ያልሆኑ አሠራሮችን ወይም እንቅስቃሴዎችን የሚያካሂድ መሆኑ ወይም የገንዘብ አስቀማጮችን ጥቅም በሚጎዱ ተግባራት ላይ የተሰማራ መሆኑ ወይም በባንኩ ሥራ አመራር ላይ ከባድ ድክመት የተከሰተ መሆኑ ብሔራዊ ባንክ በቦታው ሳይገኝ ወይም በመገኘት ባከናወነው የምርመራ ግኝት የተረጋገጠ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ፦

ሀ) ከምርመራው የሚመነጩ ወይም ከምርመራው ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ጉዳዮች በሚመለከት ለመነጋገር የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ወይም የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ እንዲጠራ ወይም የምርመራው ሂደት ከመጠናቀቁ በፊት የተመርማሪው ባንክ የሥራ ኃላፊዎች ምርመራውን በሚመለከት የብሔራዊ ባንክ ኃላፊዎችን እንዲያነጋግሩ ለማዘዝ፤

ለ) በባንኩ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የቦርድ ኮሚቴዎች ወይም በባንኩ ቦርድ በተሰየመ ማንኛውም ኮሚቴ ወይም ሌላ ማንኛውም አካል በሚያካሂደው ስብሰባ ላይ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ኃላፊዎቹ እንዲገኙ ለመወከልና አስተያየታቸውም በስብሰባዎቹ ላይ እንዲሰማ ባንኩ ዕድል እንዲሰጥ ለማድረግ፤

## 32. Prompt Corrective Actions

1/ Where an off-site or on-site examination of a bank results in a finding that the bank has failed to comply with the relevant laws and Directives or with the terms and conditions of license or has engaged in unsafe or unsound practices or activity that could pose risk to the bank or to the banking system or engaged in practices detrimental to the interests of depositors or has serious weaknesses in its corporate governance, the National Bank may:

a) require the bank to call a board of directors meeting or a general meeting of its shareholders for the purpose of considering any matter arising out of the examination or any other related issues or require officers of the bank to discuss any such matter with officers of the National Bank before the examination process is finalized;

b) assign one or more of its officers to watch the proceedings at any general meeting of the shareholders, board of directors or board committee or any other body constituted by the board of the bank, and require the bank to give an opportunity to the officers to be heard at such meetings;

ሐ) ባንኩ ሊወስዳቸው የሚገባውን የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወስድ በጽሑፍ ለማዘዝ፤

መ) የባንኩን የፋይናንስ ቁመና እንዲሁም ጤናማ እና ጥንቃቄ የተሞላበት የሥራ አመራር ለማሻሻል እና መልሶ ለመገንባት የሚያግዝ ብቃት እና ችሎታ ያለው የውጭ አማካሪ ባንኩ እንዲቀጥር ለማዘዝ፤

ሠ) ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በባንኩ ላይ የገንዘብ መቀጫ ለመጣል፤

ረ) የባንኩን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎች ከሥራ ለማገድ ወይም ለማሰናበት ወይም ለዚሁ ሲባል ባወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በእነዚህ ሰዎች ላይ የገንዘብ መቀጫ ለመወሰን፤

ሰ) በብሔራዊ ባንክ ከሥራ የታገዱ ወይም የተሰናበቱ ሰዎች እገዳው ወይም ስንብቱ ተፈጻሚ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ በዚያው ባንክ ወይም በሌላ ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ሆነው ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ማናቸውም ኃላፊነቶች ላይ እንዳያገለግሉ ለማድረግ፤

ሸ) በባንኩ ሁኔታ እና አሠራር ላይ ልዩ ምርመራ እንዲያካሂድ እና በምርመራው ግኝት መሠረት አስፈላጊ የሆኑ የማስተካከያ እርምጃዎችን እንዲወስድ ባንኩን ለማዘዝ፤

c) instruct in writing corrective actions to be taken by the bank;

d) instruct the bank to hire qualified and competent external advisor that can assist in improving and restoring the financial position, as well as the sound and prudent management of the bank's business.

e) impose fines on the bank as determined by National Bank Directive;

f) order the dismissal or suspension of one or more directors, the chief executive officer or senior executive officers of the bank, or impose fines on such persons in accordance with Directives issued for such purpose;

g) prohibit persons suspended or dismissed by National Bank from assuming board of director, chief executive officer, senior executive officer positions or any other positions as appropriate of the same bank or any other financial institution up to a period where the suspension or dismissal remains active;

h) order the bank to undertake special investigation on the state and affairs of the bank and take necessary remedial actions based on the findings of same;

ቀ) ባንኩ አዲስ ቅርንጫፍ ወይም ንዑስ ቅርንጫፍ እንዳይከፍት ለመከልከል፤

በ) እንደ አግባብነቱ ነባር ቅርንጫፎች ወይም ንዑስ ቅርንጫፎች ከደረጃቸው ዝቅ እንዲሉ ወይም እንዲዘጉ ለማድረግ፤

ተ) የባንኩን የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ለመገደብ፣ ለማገድ ወይም ለመከልከል፤

ቸ) ባንኩ ተጨማሪ ካፒታል ሥራ ላይ እንዲያውል ለማስገደድ፤

ኀ) በቅድመ ማስጠንቀቂያ አመልካቾች መሠረት የተለያዩ የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዎችን ለመውሰድ፤

ነ) ባንኩ ለተወሰነ ጊዜ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የባንክ ሥራ እንዳይሠራ ለማዘዝ፤

ኘ) ባንኩ በሞግዚት አስተዳደር እንዲተዳደር ወይም እንዲፈርስ ሊያደርግ፣ ወይም

አ) የተገኙትን ጉድለቶች ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመፍታት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ማናቸውንም ተመሳሳይ እርምጃዎች ሊወስድ፤

ይችላል።

፪/ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ፈጣን የማስተካከያ እርምጃ በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና/ወይም የአሠራር ማዕቀፍ ሊያወጣ ይችላል፡፡

i) prohibit the bank from opening new branch and sub-branch;

j) cause the down grading or closure of existing branches or sub-branches, as appropriate;

k) restrict, suspend or prohibit payment of dividends by the bank;

l) require the bank to inject additional capital;

m) take precautionary corrective measures based on early warning indicators;

n) order the bank to suspend, for specified time, any or all of its banking businesses;

o) put the bank under official administration or liquidation; or

p) take any other similar actions necessary to address the identified deficiencies effectively.

2/ National Bank may issue Directive and/or operational framework on early intervention and prompt corrective action.

## ክፍል ዘጠኝ

## ውህደት፣ ግዥ እና ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ እንዲሁም ሀብት እና ዕዳ ስለማስተላለፍ

### ፴፫ ውህደት እና ግዥ

፩/ ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ማንኛውም ባንክ በፈቃደኝነት የሚደረግ ውህደት መፈጸም አይችልም።

፪/ ችግር ያለባቸው ባንኮችን ለማዳን እና/ወይም ይበልጥ ጠንካራ የሆነ ባንክ እንዲፈጠር ለማስቻል በብሔራዊ ባንክ አነሳሽነት በሕግ አስገዳጅነት የሚደረግ ውህደት ሊፈጸም ይችላል።

፫/ የፋይናንስ ሥርዓቱን ጤናማነት ለማረጋገጥ ሲባል የውጭ ባንክን ጨምሮ አንድ ባንክ ሌላ ባንክን እንዲገዛ ብሔራዊ ባንክ በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል።

፬/ የማንኛውም የባንክ ውህደት ወይም ግዥ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ወይም የአሰራር ማዕቀፍ፦

ሀ) የባንኩን ጤናማነት እና አጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋት፣

ለ) የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብትና ጥቅም እንዲሁም የፋይናንስ ተደራሽነትን፣ እና/ወይም

ሐ) የባንክ ሥርዓት ውስጥ ያለውን ውድድር እና ቅልጥፍና ይጎዳል ተብሎ ከታመነ፣

ተፈጻሚ አይሆንም።

## PART NINE

## MERGER, ACQUISITION AND TRANSFER OF SIGNIFICANT OWNERSHIP, ASSETS AND LIABILITIES

### 33. Merger and Acquisition

1/ A bank shall not enter into a voluntary merger without the prior written approval of the National Bank.

2/ Statutory merger may be set up by the National Bank to rescue problem banks and/or to create a more viable and stronger bank.

3/ For the purpose of ensuring financial system stability, the National Bank may exceptionally approve the acquisition of a bank by another bank, including a foreign bank.

4/ No bank merger or acquisition transaction shall take place if such transaction, as per a Directive or operational framework to be issued by National Bank, is deemed to be detrimental to:

a) soundness of the bank and the financial system stability at large;

b) financial service consumers' right and interest, and access to finance; and/or

c) competition and efficiency in the banking system.

፭/ የባንክ ውህደት ወይም ግዢ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች የተቀመጠውን የአክሲዮን ይዞታ ገደብ ባከበረ መልኩ መከናወን ይኖርበታል።

፮/ ማንኛውም የባንክ ውህደት ወይም ግዥ የውሳኔ ሐሳብ በባንኩ ባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ መወሰን አለበት።

፯/ ማንኛውም የባንክ ውህደት ወይም ግዥ በተሳካ ሁኔታ እንዲፈጸም የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ከብሔራዊ ባንክ እና ከሚመለከታቸው ባንኮች ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

፰/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የባንክ ውህደት እና ግዥ የሚፈጸምባቸው ዝቅተኛ ሁኔታዎች እና መስፈርቶች እንዲሁም አካሄዶች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና/ወይም የአሰራር ማዕቀፍ የሚወሰን ይሆናል።

**፴፬. ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ስለማስተላለፍ**

፩/ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻን የሚፈጥር ማንኛውም የአክሲዮን ዝውውር ወይም ግዥ በአክሲዮን መዝገብ ላይ ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት።

፪/ ብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ ሳይፈቅድ የተከናወነን ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ለውጥ ለማስተካከል ፣ ለመሻር ወይም በሌላ መልኩ ለማስተናገድ ብሔራዊ ባንክ ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው።

5/ Merger or acquisition of a bank shall be carried out in compliance with shareholding limits of this Proclamation and relevant Directives of the National Bank.

6/ Any merger or acquisition proposal shall be decided by extraordinary general shareholders meeting of the bank.

7/ Pertinent Government organs shall cooperate with the National Bank and concerned banks for the successful execution of any merger or acquisition.

8. Without prejudice to the provisions of this Article, the minimum conditions and requirements and procedures for bank mergers and acquisitions shall be determined by National Bank Directive and/or operational framework.

**34. Significant Ownership Transfer**

1/ Any share transfer or purchase that causes significant ownership in a bank shall be approved by National Bank prior to being recorded in the share register.

2/ National Bank shall have the power to take appropriate action to modify, reverse or otherwise address change of significant ownership that has taken place without its prior approval.

፫/ የፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋትን እንዲሁም የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት እና ጥቅም ይጎዳል ተብሎ በብሔራዊ ባንክ ከታመነበት ማንኛውም ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ዝውውር ተፈጻሚነት አይኖረውም። በወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ ለባንኮች ፈቃድ ለመስጠት ሥራ ላይ ከሚውሉት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲባል ብሔራዊ ባንክ በወሳኝ ባለቤትነት ላይ ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ ማንኛውንም ሀሳብ ውድቅ የማድረግ ወይም እንደዚህ ባለው ኢንቨስትመንት ላይ ድምጽ የመስጠት መብቶች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ የመከልከል ሥልጣን አለው።

፬/ ማንኛውም በሐሰተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተከናወነ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ዝውውር ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ የሚተላለፍባቸው ዝቅተኛ ሁኔታዎች እና መስፈርቶች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል።

## ፴፭. ሀብት እና ዕዳ ስለማስተላለፍ

፩/ በመደበኛ የሥራ ሂደት ካልሆነ በስተቀር ብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ በጽሑፍ ሳይፈቅድ ማንኛውም ባንክ ሀብቱን ወይም ዕዳውን ለሌላ ባንክ ሊያስተላልፍ አይችልም ወይም የባንክ ሥራውን ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ ውል መዋዋል አይችልም።

3/ Significant ownership transfer shall not be allowed if such transfer is believed by National Bank to be detrimental to financial system stability and financial consumers' right and interest. National Bank has the power to reject any proposal for a change in significant ownership, or prevent the exercise of voting rights in respect of such investments to ensure that any change in significant ownership meets criteria comparable to those used for licensing of banks.

4/ Significant ownership transfer carried out based on false information shall be null and void.

5/ Without prejudice to the provisions stated under this Article, minimum conditions and requirements on transfer of significant ownership may be determined by National Bank Directive.

## 35. Assets and Liabilities Transfer

1/ Unless it is under normal course of business; a bank shall not carry out assets and liabilities transfer to another bank; or shall not enter into any agreement for the sale or disposal of its business, without prior written approval of the National Bank.

፪/ ማንኛውም የሀብት ወይም የዕዳ ዝውውር ተግባር በዝውውሩ ውስጥ የሚሳተፉትን ባንኮች ጤናማነት፣ የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ጥቅም እና/ወይም የፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋትን ይጎዳል ተብሎ በብሔራዊ ባንክ ከታመነ ሊፈጸም አይችልም።

፫/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የአንድ ባንክ ሀብት እና ዕዳ ለሌላ ባንክ የሚተላለፍበት ዝቅተኛ ሁኔታዎች እና መስፈርቶች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል።

## ክፍል አሥር

## ስለ እልባት፣ ፈቃድ ስለመሠረዝ እና ስለመፍረስ

### ፴፮. የማገገም ዕቅድ

፩/ ማንኛውም ባንክ ከፍተኛ እና አስጊ ሁኔታዎች የተከሰቱ እንደሆነ የፋይናንስ ቁመናውን መልሶ ለማስተካከል የሚወሰዱ እርምጃዎችን የሚያስቀምጥ የማገገም ዕቅድ አዘጋጅቶ መያዝ አለበት።

፪/ ማንኛውም ባንክ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ወይም የሕግ ወይም የሥራ አወቃቀሩ ወይም የፋይናንስ ሁኔታው ላይ መሠረታዊ ለውጥ በሚከሰት ጊዜ የማገገም ዕቅዱን መከለስ አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ባንኮች ከዚህ ባጠረ የጊዜ ገደብ የማገገም ዕቅዳቸውን እንዲያሻሽሉ ብሔራዊ ባንክ ሊያስገድድ ይችላል።

2/ Assets and liabilities transfer shall have no effect if such transfer is believed by National Bank to be detrimental to soundness of the bank involved in the transfer, financial service consumers' interest and/or financial system stability.

3/ Without prejudice to the provisions stated under this Article, minimum conditions and requirements on transfer of assets and liabilities by a bank to another bank may be determined by National Bank Directive.

## PART TEN

## RESOLUTION, LICENSE REVOCATION AND LIQUIDATION

### 36. Recovery Plan

1/ A bank shall draw up a recovery plan which shows the measures to be taken to restore its financial position in the event of severe situations of stress.

2/ A bank shall update its recovery plan at least annually or following a change to the legal or business structure or its financial situation which could have a material effect.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, National Bank may require banks to update their recovery plan in a shorter period of time.

፬/ ብሔራዊ ባንክ የእያንዳንዱን ባንክ የማገገም ዕቅድ በቀረበለት በስድስት ወራት ውስጥ መርምሮ ያጸድቃል፤ ለዚሁም በዕቅዱ ላይ የተጠቀሱት አሠራሮች አፈጻጸም የባንኩን ወይም የባንክ ቡድኑን አዋጭነት እና የፋይናንስ ቁመና ሊጠብቁ ወይም ሊመልሱ የሚችሉ መሆናቸውን ጨምሮ ዕቅዱ ለማገገሚያ ዕቅድ የተቀመጡ መስፈርቶችን ምን ያህል እንዳሟላ ይገመግማል።

፭/ የማገገም ዕቅድ ይዘት እና ሌሎች ተያያዥ መስፈርቶች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ይወሰናሉ።

## ፴፯. የእልባት ዕቅድ

፩/ ብሔራዊ ባንክ የእልባት ሰጪ ባለሥልጣን እንደመሆኑ፣ ከኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ጋር በመመካከር በፋይናንስ ሥርዓቱ ጤናማነት ላይ ወሳኝ ሚና አለው ተብሎ በብሔራዊ ባንክ በሚመደብ ማንኛውም ባንክ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ በከባድ እና አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች ባንኮች የእልባት ዕቅድ ያዘጋጃል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ እያንዳንዱን የእልባት ዕቅድ እንደ አስፈላጊነቱ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ገምግሞ ይከልሳል።

፫/ ብሔራዊ ባንክ የእልባት ዕቅድ በሚያዘጋጅበት ወቅት ለእልባቱ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ማናቸውንም መሠረታዊ ጉዳዮች ይለያል እንዲሁም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እንቅፋቶቹን ለመፍታት የሚወሰዱ አግባብነት ያላቸው ዝርዝር እርምጃዎች ይወስናል።

፬/ የእልባት ዕቅድ ይዘት እና ሌሎች ተያያዥ መስፈርቶች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ይወሰናሉ።

4/ National Bank shall review and approve recovery plan of a bank within six months of submission of each plan and assess the extent to which it satisfies the requirements of a recovery plan, including whether implementation of arrangements indicated in the plan are reasonably likely to maintain or return viability and financial position of the bank or the bank group.

5/ The content and other related requirements of a recovery plan shall be determined by the National Bank Directive.

## 37. Resolution Plan

1/ National Bank, being a resolution authority, shall, in consultation with Ethiopian Deposit Insurance Fund, draw up a resolution plan for systemically important bank as determined by the National Bank and for other banks under severe distress as may be necessary.

2/ National Bank shall review and update a resolution plan at least on annual basis as may be necessary.

3/ In drawing up the resolution plan, National Bank shall identify any material impediments to the resolvability and, where necessary, outline relevant proportionate actions on how these impediments could be addressed.

4/ The content and other related requirements of a resolution plan shall be determined by National Bank Directive.

## ፴፰. የቀውስ ሁኔታ አመራር

፩/ መረጃ ለመለዋወጥ፣ የቀውስ ሁኔታ አመራር ማዕቀፍ ለማዘጋጀት እና ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም በተለያዩ ተቋማት መካከል ያለውን ቅንጅት እና ትብብር ለማሳለጥ ብሔራዊ ባንክ በሰብሳቢነት የሚመራው እና ገንዘብ ሚኒስቴርን፣ የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድን፣ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣንን እና በብሔራዊ ባንክ የሚወሰኑ ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማትን የያዘ ብሔራዊ የቀውስ ሁኔታ አመራር ኮሚቴ ይቋቋማል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ብሔራዊ ባንክ ማንኛውንም የቀውስ ሁኔታ ለመፍታት የተለያዩ የቁጥጥር እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል።

## ፴፱. የሞግዚት አስተዳዳሪ ስለመሾም

፩/ ብሔራዊ ባንክ፦

ሀ) የባንኩ ዝቅተኛ በቂ የካፒታል ምጣኔ ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው ዝቅተኛ መጠን ሀምሳ በመቶ በታች ከሆነ እና/ወይም የተከፈለ ካፒታል በሀምሳ በመቶ ከተሸረሸረ፤

ለ) ባንኩ ወይም የባንኩ ዳይሬክተሮች፣ ሥራ አመራር ወይም ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች የገንዘብ አስቀማጮችን ጥቅም አደጋ ላይ ሊጥል በሚችል መልኩ በሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎች ተሳትፈዋል ወይም እየተሳተፉ ነው ብሎ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ብሔራዊ ባንክ ካለው፤

## 38. Crisis Management

1/ A national crisis management committee chaired by National Bank and comprising of relevant stakeholders including Ministry of Finance, Ethiopian Deposit Insurance Fund, Ethiopian Capital Market Authority, and other similar institutions to be determined by National Bank, shall be established so as to exchange information, develop and implement crisis management framework and enhance coordination and cooperation among different institutions.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article. National Bank may employ various supervisory measures to address a crisis.

## 39. Appointment of Official Administrator

1/ National Bank may appoint an official administrator for a bank if:

a) The required capital adequacy ratio of the bank falls by fifty percent from the minimum set by National Bank and/or its paid up capital is eroded by fifty percent;

b) National Bank has a reasonable cause to believe that the bank or its directors, management, or shareholders with significant ownership have engaged in or are engaging in illegal activities in a manner likely to jeopardize the interest of depositors;

ሐ) ባንኩ በመደበኛ የሥራ ሂደት ግዴታውን መወጣት ወይም የአስቀማጮቹን የገንዘብ ጥያቄ ማሟላት አይችልም የሚል ጠንካራ ግምት ካለ፤

መ) ባንኩ የባንኩን ሁኔታ ሊያዳክም በሚችል መልኩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌ መጣሱ ወይም በማንኛውም አስተማማኝ ወይም ጤናማ ያልሆነ አሠራር ውስጥ መሳተፉ ወይም የገንዘብ አስቀማጮችን ጥቅም በከፍተኛ ሁኔታ አደጋ ላይ መጣሉ ወይም የባንኩን ሀብት ማባከኑ ከተረጋገጠ፤

ሠ) ባንኩ በቂ ካፒታል እንዲኖረው ሲታዘዝ በቂ ካፒታል ሳይኖረው የቀረ ከሆነ ወይም በብሔራዊ ባንክ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ካፒታሉን መልሶ ለመገንባት የሚያስችል በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለው ዕቅድ ሳያቀርብ ከቀረ ወይም ተቀባይነት ያገኘውን ዕቅድ ተግባራዊ ሳያደርግ ከቀረ፤

ረ) ባንኩ የባንኩን መዛግብት፣ ሒሳቦች፣ መዝገቦች ወይም ማናቸውንም ሰነዶች ለብሔራዊ ባንክ መርማሪዎች ለምርመራ ማቅረብ ካልቻለ ወይም ብሔራዊ ባንክ የቁጥጥር ኃላፊነቱን እንዲያከናውን ለመተባበር ካልቻለ፤ እና

ሰ) ባንኩ ወይም የባንኩ ዳይሬክተሮች ወይም ሥራ አመራር ወይም ሠራተኞች ወይም ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች የብሔራዊ ባንክን ትዕዛዝ ሳያከብሩ ከቀሩ ወይም ይህን አዋጅ ጨምሮ አግባብነት ያላቸው ሕጎችን በተደጋጋሚ ከጣሱ፤

የሞግዚት አስተዳዳሪ ሊሾም ይችላል።

c) There is a strong likelihood that the bank may be unable to fulfill its obligations or meet its depositors' demands in the normal course of business;

d) It is determined that the bank has contravened a provision of this Proclamation or engaged in any unsafe or unsound practice, in a manner that weaken the condition of the bank, or seriously jeopardized the interest of depositors or dissipated assets of the bank;

e) The bank fails to become adequately capitalized when required to do so or fails to submit a capital restoration plan acceptable to the National Bank within the time prescribed by the National Bank or fails to implement the accepted capital restoration plan;

f) The bank fails to submit for examination the books, accounts, records or any other documents of the bank for the National Bank examiners or fails to cooperate with National Bank to perform its supervisory responsibilities; and

g) The bank or directors or management or employees of that bank or its shareholders with significant ownership fail to comply with instruction of the National Bank or persistently violate relevant laws including this Proclamation.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ባንክ በሞግዚት አስተዳደር ሥር እንዲደረግ በባንኩ ባለአክሲዮኖች ውሳኔ በማስደገፍ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ የባንኩን ጥያቄ በማጽደቅ እና ይህን መሠረት በማድረግ የሞግዚት አስተዳዳሪ ሊሾም ይችላል።

፫/ ብሔራዊ ባንክ ለማንኛውም ባንክ የሞግዚት አስተዳዳሪ ለመሾም የወሰነውን ውሳኔ እና ለውሳኔው ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በመግለጽ በጽሑፍ እና መደበኛ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በመጠቀም ያሳውቃል እንዲሁም በድረ-ገጹ ላይ እና ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ያሳትማል።

፬/ የሞግዚት አስተዳዳሪ ለመሾም የተወሰነ ውሳኔ ለባንኩ በተሰጠው ማሳወቂያ ላይ ከተገለጸው ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

**፵. <u>ለሞግዚት አስተዳዳሪነት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

፩/ ማንኛውም የሞግዚት አስተዳዳሪ በብሔራዊ ባንክ በሚወሰነው መሠረት ከፍተኛ የሙያ ብቃት እና ታማኝነት ያለው ሰው መሆን አለበት።

፪/ የሞግዚት አስተዳዳሪው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ፦

ሀ) የሞግዚት አስተዳደሩን በበላይነት የሚመራው ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን የብቃት መስፈርቶች ማሟላት፣ እና

ለ) በሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል በቂ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ከታወቀ የመድን ሰጪ ኩባንያ ወይም ባንክ ማቅረብ አለበት።

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, National Bank may approve request of a bank to be put under official administration as supported with resolution of the bank's shareholders and appoint official administrator accordingly.

3/ National Bank shall inform its decision to appoint official administrator for a bank in writing and through formal electronic media by setting out the reasons for the decision; and post the notice on its website and in a newspaper of wide circulation.

4/ The decision to appoint official administrator shall be effective from the date specified in the notice to the bank.

**40. <u>Qualifications of Official Administrator</u>**

1/ An official administrator shall be of the highest professional qualifications and personal integrity, as determined by National Bank.

2/ Where the official administrator is a juridical person:

a) the principal officer in charge of the official administration shall meet the qualification requirements stipulated under Sub-Article (1) of this Article; and

b) the juridical person shall provide adequate performance guarantee from a reputable insurance company or a bank.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሞግዚት አስተዳዳሪ ተደርጎ የሚሾም ማንኛውም ሰው በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰኑትን ዝቅተኛ የብቃት እና ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article, any person to be appointed as official administrator shall meet the minimum qualification and other requirements to be determined by National Bank Directive.

**፵፩. <u>የሞግዚት አስተዳዳሪ የአገልግሎት ዘመን</u>**

አንድ ባንክ ከላይ በአንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተደነገገው መሠረት በተሰጠው ማሳወቂያ ውስጥ ከተገለጸው ቀን አንስቶ ለስድስት ወራት ለመጀመሪያ ጊዜ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ሊቆይ ይችላል እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባንኩን መልሶ ለማቋቋም አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ጊዜውን እያንዳንዳቸው የሦስት ወራት ርዝመት ላላቸው ሁለት ተከታታይ ጊዜያት ሊያራዝም ይችላል።

**41. <u>Term of Office for Official Administrator</u>**

A bank may remain under official administration for a period of six months effective from the date specified in the notice as stipulated under Article 39 (3) hereinabove for first instance; and the National Bank may extend the period for two consecutive periods of three months each, if it deems it necessary to rehabilitate the bank.

**፵፪. <u>ለሞግዚት አስተዳዳሪ የሚከፈል ክፍያ እና የሞግዚት አስተዳደር ወጪዎች</u>**

፩/ ለሞግዚት አስተዳዳሪ የሚከፈለው ክፍያ በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል።

፪/ ለሞግዚት አስተዳደር የሚወጡ ወጪዎች በሙሉ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ባለው ባንክ ይሸፈናሉ።

፫/ ብሔራዊ ባንክ አግባብ እና አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነበት የሞግዚት አስተዳደር ሥራ የሚካሄድበትን ወጪ ሊሸፍን ይችላል፤ ይህም በባንኩ መልሶ የሚከፈል ይሆናል።

**42. <u>Remuneration of Official Administrator and Expenses of Official Administration</u>**

1/ The remuneration to be paid for the official administrator shall be determined by National Bank.

2/ The bank under official administration shall bear all costs and expenses incurred on account of the official administration.

3/ The National Bank, if deemed appropriate and necessary, may provide funding to cover operating costs of the official administration which shall be reimbursed by the bank.

## ፵፫. የሞግዚት አስተዳዳሪ ሥልጣን እና ተግባራት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱ መሠረት የተሾመ ማንኛውም የሞግዚት አስተዳዳሪ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣ ለዳይሬክተሮች ቦርድ እና ለሥራ አመራር የተሰጡ ሥልጣኖችን እና ተግባራትን ሙሉ በሙሉ እና በብቸኝነት በመውሰድ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ያለውን ባንክ ይቆጣጠራል፤ የሞግዚት አስተዳዳሪው አስቀድሞ ሳይፈቅድ ማንኛውም አካል ባንኩን በመወከል ማንኛውንም እርምጃ መውሰድ አይችልም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የሞግዚት አስተዳዳሪ ሥልጣን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ) ከብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው ትዕዛዝ፣ መመሪያዎች እና አቅጣጫ መሠረት በሞግዚት አስተዳደር ሥር ያለውን ባንክ መምራት እና ሥራውን ማስኬድ፤

ለ) ለዚሁ ዓላማ ሲባል ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ የሚደነገጉ ማናቸውም ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው የባንኩን ንብረቶች በዋስትናነት በማስያዝ ወይም ያለዋስትና ገንዘብ መበደር፤

ሐ) ከብሔራዊ ባንክ በሚሰጥ ፈቃድ መሠረት ማንኛውንም አስፈላጊ ባለሙያ ወይም አማካሪ በመቅጠር ማሠራት፤

መ) ማንኛውንም የሥራ ውል ማቋረጥ፤ እና

ሠ) በባንኩ ስም ማንኛውንም ክፍያ መፈጸም ወይም ማንኛውንም ሰነድ መፈረም ወይም በባንኩ ስም ማንኛውንም ክስ መመሥረት ወይም መከላከል እና ማካሄድ።

## 43. Powers and Duties of the Official Administrator

1/ An official administrator appointed pursuant to Article 39 of this Proclamation shall be vested with the full and exclusive powers and duties of shareholders general meeting, board of directors and management and assume control of the bank under official administration; and no action may be taken by other bodies on behalf of the bank without the prior approval of the official administrator.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the official administrator's powers shall include the power to:

a) manage and operate a bank under official administration in accordance with the instructions, directions and guidance of National Bank;

b) borrow money on the security of the assets of the bank, or unsecured loans, subject to any limitations provided for by a Directive to be issued by National Bank for such purpose;

c) employ any necessary professional or advisor upon approval by National Bank;

d) terminate any contracts of employment; and

e) make any payment or execute any instrument in the name of the bank; initiate or defend and conduct in its name any action or legal proceeding.

፫/ ማንኛውም የሞግዚት አስተዳዳሪ፦

ሀ) የባንኩን ሥራ ለማስቀጠል፣

ለ) የባንኩን ሀብት እና ንብረት ጠብቆ ለማቆየት፣ ወይም

ሐ) ባንኩን በተመለከተ በብሔራዊ ባንክ የጸደቀ ማንኛውንም የድርጊት መርሐ ግብር ተግባራዊ ለማድረግ፣

አስፈላጊ ወይም አግባብ የሆነ ማንኛውንም እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

፬/ ከብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ በሚሰጥ የጽሑፍ ፈቃድ ማንኛውም የሞግዚት አስተዳዳሪ ኃላፊነቶቹን በከፊል ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል።

፭/ የሞግዚት አስተዳዳሪው ለባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ወይም ሌላ አይነት የካፒታል ክፍፍል እንዲሁም ለዳይሬክተሮች ማንኛውም አይነት ክፍያ እንዳይከፈል ወዲያውኑ ሊያግድ ይችላል።

፮/ ሕግ አስፈጻሚ አካላትን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው የመንግሥት አካላት ለሞግዚት አስተዳዳሪው ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለባቸው።

፯/ ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳዳሪ ሲሾም የሞግዚት አስተዳዳሪው በቅድሚያ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በማግኘት ሊወስዳቸው የሚችላቸውን እርምጃዎች በዝርዝር ሊያስቀምጥ ይችላል።

፰/ ማንኛውም የሞግዚት አስተዳዳሪ፦

ሀ) የባንኩን ሀብት እና ዕዳዎች ዝርዝር ከተሾመበት ቀን አንስቶ በሁለት ወራት ውስጥ፣

3/ The official administrator may take any action necessary or appropriate to:

a) carry on the business of the bank;

b) preserve and safeguard the assets and property of the bank; or

c) implement any action plan that has been approved by National Bank with respect to that bank.

4/ The official administrator, upon prior written approval of the National Bank, may delegate a portion of its responsibilities to another person.

5/ The official administrator may immediately suspend dividends or other form of capital distribution to shareholders and any payment to directors.

6/ The official administrator shall get appropriate assistance from relevant Government organs, including law enforcement organs.

7/ National Bank may, upon appointing the official administrator, specify certain actions for which the official administrator shall obtain prior approval from National Bank.

8/ An official administrator shall prepare and submit to the National Bank:

a) an inventory of the assets and liabilities of the bank within two months from the appointment date;

ለ) ቢያንስ የሚከተሉትን ያካተተ የባንኩን የፋይናንስ ሁኔታ እና ቅድመ ትንበያ የሚያሳይ ሪፖርት ከተሾመበት ቀን አንሥቶ በሦስት ወራት ውስጥ፦

፩) የባንኩ ንብረት ሲጣራ ሊገኝ የሚችለው ሀብት መጠን ምዘና፤

፪) ባንኩን መልሶ ለማቋቋም እና የጥንቃቄ ደንቦችን እና ሕጎችን የተከተለ ለማድረግ የቀረበ የድርጊት መርሀ-ግብር፤ እና

፫) በገንዘብ አስቀማጮች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ እና የፋይናንስ ሥርዓቱን መረጋጋት ለማስጠበቅ የቀረቡ የእርምጃ ሐሳቦች፤

ማዘጋጀት እና ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት።

፱/ የሞግዚት አስተዳዳሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) በተገለጹት ሪፖርቶች ላይ ወዲያውኑ ከብሔራዊ ባንክ ጋር ተወያይቶ ስምምነት ያደርጋል።

፲/ በሞግዚት አስተዳደር ወቅት የሞግዚት አስተዳዳሪው የባንኩን ንብረቶች፣ ቢሮዎች፣ ሀብት እና የሒሳብ መዛግብት እንዲሁም ሌሎች መዝገቦች ያለገደብ ማግኘት እና መቆጣጠር አለበት።

፲፩/ ማንኛውም ሕግ አስፈጻሚ አካል በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የሞግዚት አስተዳዳሪው ወደ ማንኛውም የባንኩ የሥራ ስፍራዎች በመግባት የባንኩን ንብረቶች፣ ቢሮዎች፣ ሀብት፣ መዛግብት እና ሰነዶች መቆጣጠር እና መያዝ እንዲችል እገዛ ማድረግ አለበት።

b) a report on the financial condition and prospects of the bank within three months from the appointment date, that at least include:

1) an assessment of the amount of assets likely to be realized in a liquidation of the bank;

2) a proposed action plan to rehabilitate and make the bank comply with the prudential Regulations and Laws; and

3) the proposed measures to minimize damage to depositors and preserve the stability of the financial system.

9/ The official administrator shall promptly discuss with National Bank and agree on the reports indicated under Sub-Article (8) of this Article.

10/ During official administration, the official administrator shall have unrestricted access to and control over the properties, offices, assets and books of accounts and other records of the bank.

11/ A law enforcement body shall, on request, assist the official administrator to gain access to any premises of the bank, to gain control over and to secure the properties, offices, assets, books, and records of the bank.

፲፪/ የባንኩ ዳይሬክተሮች፣ ቁልፍ የሥራ አመራር ኃላፊዎች እና ሠራተኞች፦

ሀ) ለሞግዚት አስተዳዳሪው ሙሉ ትብብር እና እገዛ ማድረግ፤እና

ለ) ከባንኩ ጋር የተያያዙ መዛግብትን እና ሰነዶችን እንዲሁም የሞግዚት አስተዳዳሪው የሚጠይቃቸውን ሌሎች ማናቸውም መረጃዎች እና ሪፖርቶች የሞግዚት አስተዳዳሪው ማግኘት እንዲችል ማድረግ አለባቸው።

፲፫/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ያላከበረ ወይም በሌላ መልኩ ብሔራዊ ባንክ ወይም የሞግዚት አስተዳዳሪው ሥራቸውን እንዳይሠሩ እንቅፋት የሆነ ማንኛውም ሰው በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል።

፲፬/ የሞግዚት አስተዳዳሪው በብሔራዊ ባንክ የሚጠየቀውን ማንኛውም ተጨማሪ ሪፖርት ወይም መረጃ ወዲያው ያቀርባል።

፲፭/ ማንኛውም የሞግዚት አስተዳዳሪ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ያለውን ባንክ ሥራ የተመለከተ ሚስጥራዊ መረጃ ይፋ ማድረግ የለበትም።

**፵፬. <u>የሞግዚት አስተዳዳሪ መሾምን በመቃወም ስለሚቀርብ አቤቱታ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱(፫) መሠረት የሞግዚት አስተዳዳሪ ስለመሾሙ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰላሳ ቀናት ውስጥ ከባንኩ አክሲዮኖች ቢያንስ ሀያ አምስት በመቶ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖችን የያዙ ባለአክሲዮኖች የሞግዚት አስተዳዳሪውን መሾም በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

12/ The directors, key management personnel and employees of the bank shall :

a) cooperate fully with and assist the official administrator; and

b) make available to the official administrator all records and documentation pertaining to the bank and any additional information or reports requested by the official administrator.

13/ A person who does not comply with the provision of Sub-Article (12) of this Article or otherwise obstructs the National Bank or an official administrator in the performance of functions shall be criminally liable.

14/ The official administrator shall promptly provide any additional report or information requested by National Bank.

15/ An official administrator shall not disclose confidential information regarding the affairs of the bank under official administration.

**44. <u>Review Against Appointment of Official Administrator</u>**

1/ Shareholders of a bank holding in the aggregate at least twenty-five percent of the voting shares of the bank may submit a request for review to the Federal High Court against the appointment of an official administrator within thirty days after the date on which the official administration is announced in newspaper pursuant to Sub-Article (3) of Article 39 of this Proclamation.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አቤቱታ የቀረበ እንደሆነ፦

ሀ) ፍርድ ቤቱ በአቤቱታው ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የሞግዚት አስተዳደሩ ይቀጥላል፤

ለ) ፍርድ ቤቱ አቤቱታው በቀረበ በአሥር ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ይሰማል፤ ምርመራው በተጠናቀቀ በሀያ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት አቤቱታ ሲቀርብ በፍርድ ቤቱ መታየት የሚችለው ብቸኛ ጭብጥ ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳዳሪውን የሾመው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱ ከተደነገጉት መስፈርቶች አንጻር ሲታይ ተጨባጭነት በሌለው እና ባልተገባ መልኩ መሆን አለመሆኑን ብቻ ነው።

፬/ ፍርድ ቤቱ ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳዳሪውን የሾመው፦

ሀ/ ተጨባጭነት በሌለው እና ባልተገባ መልኩ ነው ብሎ ከወሰነ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በአስተዳደራዊ ቅጣት ወይም በጉዳት ካሣ የተወሰነ ይሆናል እንጂ የሞግዚት አስተዳዳሪውን ሹመት እና የወሰናቸውን ውሳኔዎች የሚሽር ሊሆን አይችልም፤

ለ/ ተጨባጭነት በሌለው እና ባልተገባ መልኩ አይደለም ብሎ ከወሰነ አቤቱታው ውድቅ ሆኖ የሞግዚት አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጥላል።

2/ Where a review is lodged in accordance with Sub-Article (1) of this Article:

a) the official administrator shall continue until the court delivers a final ruling on the review;

b) the court shall hold a hearing on the matter within ten days of the filing of the review and shall decide the review within twenty days from the end of the investigation.

3/ The sole issue to be adjudicated by the court shall be whether the National Bank acted in unrealistic and inappropriate manner in establishing the official administration, in light of the criteria set forth under Article 39 of this Proclamation.

4/ If the court determines that National Bank, in appointing the official administrator:

a) did act in unrealistic and inappropriate manner, decision of the court shall be limited to administrative penalty or compensation to the damage and shall not reverse the appointment of the official administrator and decisions taken thereof;

b) did not act in unrealistic and inappropriate manner, the review shall be denied and the official administrator shall continue in accordance with the provisions of this Proclamation.

**፵፭. በሞግዚት አስተዳደሪ ላይ ስለሚደረግ የበላይ ቁጥጥር**

፩/ የሞግዚት አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ባንክ ብቻ ነው እንዲሁም በማንኛውም ጊዜ ሥራውን ማከናወን ያለበት በጸደቀ የድርጊት መርሐ ግብር፣ ከብሔራዊ ባንክ በሚሰጥ ትእዛዝ፣ አቅጣጫ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ነው።

፪/ ለብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባለው ደረጃ ሥራውን ባለመፈጸም፣ ተገቢ ያልሆነ ድርጊት በመፈጸም፣ የጥቅም ግጭትን ወይም አግባብነት ያላቸው ሕጎችን ካለማክበር ጋር በተያያዘ ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳደር ጊዜው ከማብቃቱ አስቀድሞ የሞግዚት አስተዳዳሪውን ሊያነሣ እና በምትኩ ሌላ የሞግዚት አስተዳዳሪ ሊሾም ይችላል።

፫/ ማንኛውም የሞግዚት አስተዳዳሪ የጥቅም ግጭትን ሊያስከትል የሚችል ማንኛውንም ጥቅም ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ እና ሪፖርት ማድረግ አለበት።

፬/ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ያለው ባንክ በሚሳተፍበት ማንኛውም ሥራ ላይ የሞግዚት አስተዳዳሪው መሠረታዊ ጥቅም ወይም ግንኙነት ያለው እንደሆነ የሞግዚት አስተዳዳሪው በጉዳዩ ላይ መሳተፍ የሚችለው ብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ በጽሑፍ የፈቀደለት እንደሆነ ብቻ ነው።

፭/ የሞግዚት አስተዳዳሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፬) መሠረት ፈቃድ ያልጠየቀ እንደሆነ ሥራው እንዲቆም ተደርጎ ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳዳሪውን ሊሽር እና በባንኩ ወይም በብሔራዊ ባንክ ላይ ለደረሰ ማንኛውም ጉዳት የሞግዚት አስተዳዳሪው ካሣ እንዲከፍል ሊጠይቅ ይችላል።

**45. Oversight Over Official Administrator**

1/ The official administrator shall be accountable only to the National Bank and shall at any time act in accordance with the approved action plan, instructions and guidance from the National Bank and relevant laws.

2/ National Bank may remove the official administrator before the expiry of the official administration period and appoint a replaceme nt due to failure to perform in a manner satisfactory to the National Bank, misconduct, conflict of interest or failure to act in compliance with the relevant laws.

3/ An official administrator shall disclose and report any interests that potentially result in conflict of interest to the National Bank.

4/ Any transaction involving the bank in official administration in which the official administrator has a material interest or relationship in the matter shall be engaged in only with the prior written approval of National Bank.

5/ If the official administrator fails to seek approval in line with Sub-Article (4) of this Article, the transaction may be set aside and the National Bank may remove the official administrator and claim compensation from the official administrator for any losses caused to the bank or to the National Bank.

፮/ የሞግዚት አስተዳደሩ ካበቃ በኋላ ቢያንስ ለሁለት ዓመታት የሞግዚት አስተዳዳሪው በሞግዚት አስተዳደር ሥር በነበረው ባንክ ውስጥ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ መያዝ ወይም በዳይሬክተርነት፣ በቁልፍ የሥራ አመራር ኃላፊነት ወይም በሌላ ማንኛውም ቢሮ ወይም የኃላፊነት ቦታ እንዲያገለግል ሊሾም አይችልም።

**፵፮. <u>የትርፍ ክፍፍልን ስለማገድ</u>**

የሞግዚት አስተዳዳሪው ከደመወዝ ወይም ለባንኩ ለተሰጠ አገልግሎት ከሚከፈል ክፍያ ውጭ ማንኛውም የትርፍ ድርሻ ወይም ሌላ ዓይነት የካፒታል ክፍፍል ለባለአክሲዮኖች እና ለዳይሬክተሮች እንዳይከፈል ወዲያውኑ ማገድ አለበት።

**፵፯. <u>መብቶችን ስለማገድ</u>**

፩/ለማዕከላዊ የክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ወገን እንዲሁም ለክፍያ፣ ለሒሳብ ማወራረድ እና ማጣራት ሥርዓቶች ካልሆነ በስተቀር ብሔራዊ ባንክ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ባለ ማንኛውም ባንክ የሚከፈሉ ክፍያዎችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊያግድ ወይም ሊያዘገይ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ተቀማጭ ገንዘብን ወጪ በማድረግ ላይ የሚጣል እገዳ ከአምስት የሥራ ቀናት መብለጥ አይችልም።

፫/ ብሔራዊ ባንክ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ሰው፦

ሀ) በሞግዚት አስተዳደር ሥር ባለ ባንክ ላይ ክስ መመሥረት ወይም የፍርድ ቤት ክርክር መቀጠል አይችልም፣

6/ The official administrator shall not acquire significant shares or accept appointment as a director, key management personnel or to any other office or position in the bank, which was the subject of the administration for a minimum period of two years after the end of official administration.

**46. <u>Suspension of Dividends</u>**

The official administrator shall immediately suspend the payment of any dividends or other form of capital distribution to shareholders and any payment to directors other than for salaries or services provided to the bank.

**47. <u>Suspension of Rights</u>**

1/ National Bank may impose a moratorium or suspend some or all payments by a bank under official administration except for payments to central clearing counter parties and to payment, settlement and clearing systems.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a suspension on the withdrawal of deposits shall not exceed five working days.

3/ Unless permitted by National Bank, a person shall not:

a) institute a claim or continue proceedings in acourt against a bank under official administration;

ለ) በሞግዚት አስተዳደር ሥር ባለ ባንክ ንብረት ላይ የብድር መያዣ፣ የከፍያ ወይም ሌላ የባንክ ዋስትና መብትን ተግባራዊ ማድረግ አይችልም፤

ሐ) በሞግዚት አስተዳደር ሥር ካለ ማንኛውንም ባንክ ጋር ምንም አይነት ዕዳ ማያያዝ ወይም ባንኩን በተመለከተ የተሰጠ ማንኛውንም ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ማስፈጸም ወይም እንዲፈጸም መጠየቅ አይችልም።

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ዓላማ በሕግ ወይም በውል የተቀመጠ ማንኛውም የይርጋ ጊዜ በሚያበቃበት ወቅት በሞግዚት አስተዳደር ሥር ባለው ባንክ ላይ ያለ የይገባኛል ጥያቄ የሚያበቃ ከሆነ የይርጋ ጊዜው የሞግዚት አስተዳደሩ እስከሚያበቃ ድረስ ይራዘማል።

፭/ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ያለ ባንክ ተዋዋይ ወገን በሆነበት ማንኛውም ውል ማንኛውም ሦስተኛ ወገን ያለው መብት ወይም ግዴታ የሞግዚት አስተዳዳሪ በመሾሙ ወይም የሞግዚት አስተዳዳሪው ማንኛውንም እርምጃ በመውሰዱ ምክንያት ብቻ አይቋረጥም፣ ቀድሞ እንዲፈጸም ሊጠይቅ አይችልም ወይም አይለወጥም።

b) exercise rights under a mortgage, charge or other security interest over the property of a bank under official administration; and

c) attach any debt, or otherwise enforce or seek to enforce any judgment or order obtained in respect of a bank under official administration.

4/ For the purpose of Sub-Article (3) of this Article, any period of limitation either statutory or contractual on the expiry of which a claim against the bank under official administration would expire shall extend for the period of official administration.

5/ A right or obligation of a third party under any contract to which a bank under official administration is a party shall not be terminated, accelerated or modified solely because of the appointment of the official administrator or any action taken by the official administrator.

**፵፰. የሞግዚት አስተዳዳሪው ስላሉት መልሶ የማቋቋሚያ አማራጮች**

፩/ ካፒታልን መልሶ ለማደራጀት ሲባል ብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት የሞግዚት አስተዳዳሪው በሥራ ላይ ባሉ ማናቸውም ሕጎች የተደነገጉ ማናቸውም ክልከላዎች ቢኖሩም በባለአክሲዮኖች የተያዙ አክሲዮኖችን ዋጋ ሊቀንስ ይችላል። ይህንንም ለማቀላጠፍ የሞግዚት አስተዳዳሪው የኪሳራውን መጠን መወሰን እና የባንኩን ኪሳራ በባንኩ ትርፍ፣ የመጠባበቂያ ተቀማጭ እና አስፈላጊ ከሆነም በባንኩ ካፒታል በመሸፈን የባንኩን የሒሳብ መግለጫ ማዘጋጀት አለበት።

፪/ ለባንኩ እልባት ለማበጀት በተዘጋጀ ሪፖርት እና የድርጊት መርሐ ግብር መሠረት እንዲሁም ብሔራዊ ባንክን አስቀድሞ ማስፈቀድ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ረገድ በንግድ ሕጉ የተደነገገው ቢኖርም የሞግዚት አስተዳዳሪው ለነባር ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት በሞግዚት አስተዳደር ሥር ያለውን ባንክ ካፒታል ሊያሳድግ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም፦

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተደነገገው መሠረት ነባር ባለአክሲዮኖች የባንኩን ካፒታል መልሶ ለመገንባት የሚያስፈልጉ ተጨማሪ አክሲዮኖችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መግዛት ካልቻሉ፤

**48. Rehabilitation Options for Official Administrator**

1/ In order to implement recapitalization, the official administrator, with the approval of National Bank, may reduce the value of shares held by shareholders regardless of any prohibition in any existing laws. To facilitate this, the official administrator shall determine the extent of losses and prepare the financial statements of the bank covering the amount of losses through the profits of the bank, reserves and if necessary, capital of the bank.

2/ On the basis of a report and action plan prepared to resolve the bank and subject to prior approval by National Bank, the official administrator may increase the capital of the bank under official administration through issuance of new shares to existing shareholders, despite the provision of Commercial Code in this regard.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the official administrator, with the approval of National Bank, may increase the capital of the bank through issuance of shares to new shareholders if:

a) existing shareholders are unable to partially or fully subscribe additional shares needed to restore the capital of the bank as provided under Sub-Article (2) of this Article;

ለ) ነባር ባለአክሲዮኖች በባንኩ ውስጥ ወሳኝ የካፒታል ቁመናን ለማስጠበቅ አይችሉም ብሎ ብሔራዊ ባንክ ከወሰነ፤ ወይም

ሐ) በአፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ መሠረት የተሰጠን የባንኩን ካፒታል የማሳደግ ውሳኔ አልተተገበረም ብሎ ብሔራዊ ባንክ ሲወስን፤

ሞግዚት አስተዳዳሪው በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለአዲስ ባለአክሲዮኖች አክሲዮኖችን በማውጣት የባንኩን ካፒታል ሊያሳድግ ይችላል።

፬/ ካፒታልን መልሶ ለማደራጀት እና ከኪሳራ ጋር ለማጣጣም ሲባል በሥራ ላይ ባሉ ማናቸውም ሕጎች የተደነገገ ማንኛውም ክልከላ ቢኖርም የሞግዚት አስተዳዳሪው በባለአክሲዮኖች የተያዙ አክሲዮኖችን ዋጋ ሊቀንስ ይችላል።

፭/ ብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ በጽሑፍ የፈቀደ እንደሆነ የሞግዚት አስተዳዳሪው የባንክ ውህደት ወይም ግዢ ሊፈጽም ወይም የባንኩን ሀብት እና ዕዳ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊያስተላልፍ ይችላል።

፮/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተግባራዊ ለማድረግ ሲባል የባንኩን ሀብት እና ንብረት ማስተላለፍ የሚለው ለማንኛውም የሽግግር ባንክ እና/ወይም የንብረት አስተዳደር ተቋም ማስተላለፍን ሊያጠቃልል ይችላል። ማንኛውም የሽግግር ባንክ ወይም የንብረት አስተዳደር ተቋም ወይም ሌላ ማንኛውም የተፈቀደለት ሶስተኛ ወገን ገዢ ባንክ የሚቋቋምበት እና ሥራ የሚያካሂድበት ሥነ-ሥርዓት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊወሰን ይችላል።

b) National Bank determines that existing shareholders are no longer suitable to maintain a significant capital position in the bank; or

c) National Bank determines that there has been a failure to comply with a remedial measure under prompt corrective action requiring an increase in the capital of the bank.

4/ To conduct recapitalization and reflect the losses, the official administrator may reduce the value of shares held by shareholders despite any prohibition in any existing laws.

5/ With prior written approval of National Bank, the official administrator may carry out merger or acquisition of a bank; or a transfer, in whole or in part, of the assets and liabilities of the bank.

6/ For the purpose of implementing the provision of Sub-Article (5) of this Article, transfer of the assets and liabilities of the bank may include a transfer to a bridge bank and/or an asset management vehicle. The procedures for establishing and operating a bridge bank and an asset management vehicle or any other approved third-party purchaser bank may be determined by National Bank Directive.

፯/ ብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ የፈቀደ እንደሆነ የሞግዚት አስተዳዳሪው ከአበዳሪዎች ጋር ስምምነቶች በማድረግ የአበዳሪዎችን የገንዘብ ጥያቄዎች መቀነስን፣ ማስተካከልን፣ የጊዜ ሰሌዳ መቀየርን እና ማደስን ጨምሮ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የዕዳ መልሶ ማዋቀር ሊያከናውን ይችላል።

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) የተደነገገው ቢኖርም ብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ የፈቀደ እንደሆነ የሞግዚት አስተዳዳሪው የሚመለከታቸው አበዳሪዎች ወይም ባለአክሲዮኖች ሳያስፈቅድ አግባብነት ባላቸው ሕጎች በተደነገገው መሠረት በባንኩ ዕዳዎች ላይ አስገዳጅ የሆነ መልሶ ማዋቀር ሊያከናውን ይችላል።

፱/ ብሔራዊ ባንክ አስገዳጅ የዕዳ መልሶ ማዋቀር እንዲከናወን በሚፈቅድበት ጊዜ ዕዳን መልሶ ማዋቀሩ ለብቻው ወይም ካፒታልን መልሶ ከመገንባት ጋር ባንኩን ወደ ነበረበት የሚመልሰው ስለመሆኑ ያረጋግጣል። ለዚህ ዓላማ ሲባልም ብሔራዊ ባንክ መልሶ ማዋቀሩ ምን ያህል፦

ሀ) የባንኩን ዋጋ እንደሚጨምር፣

ለ) የገንዘብ አስቀማጮችን እና የሌሎች አበዳሪዎችን ኪሳራ እንደሚቀንስ፣

ሐ) የባንኩን ህልውና ቀጣይነት እንደሚያስጠብቅ፣ እና

መ) በፋይናንስ ሥርዓቱ ላይ የሚከሰት ማንኛውንም ከፍተኛ አለመረጋጋት እንደሚከላከል ወይም እንደሚቀንስ፣

ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

7/ The official administrator, with written approval from National Bank, may conclude with creditors a consensual debt restructuring which may include reduction, modification, rescheduling and renovation of the claims of the creditors.

8/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (7) of this Article, the official administrator, with written approval from National Bank, may carry out mandatory debt restructuring of a bank in accordance with the provisions provided in the relevant laws without the approval of concerned creditors or shareholders.

9/ In approving mandatory debt restructuring, National Bank may determine that the restructuring, either alone or combined with recapitalization, will restore the bank. To this end, National Bank shall consider the extent to which the restructuring would:

a) maximize the value of the bank;

b) minimize losses to depositors and other creditors;

c) preserve going-concern value of the bank; and

d) prevent or mitigate any severe disruption in the stability of the financial system.

፲/ ዕዳን መልሶ የማዋቀሩ ተግባር በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፷፪) በተደነገገው መሠረት ንብረት በሚጣራበት ወቅት የሚኖረውን የክፍያ ቅደም ተከተል የተከተለ መሆን አለበት።

፲፩/ አስገዳጅ የሆነ መልሶ ማዋቀር በዋስትና በተጠበቀ ዕዳ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም። በተጨማሪም ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም የቅደም ተከተል ደረጃ ሥር ያሉ ዕዳዎች ሥርዓታዊ ወይም ስትራቴጂክ ወሳኝነት ያላቸው በመሆኑ ከሌሎች በዋስትና ያልተጠበቁ የክፍያ ቅድሚያ ያላቸው ዕዳዎች በተለየ ሁኔታ መስተናገድ እንዳለባቸው የወሰነ እንደሆነ እንዲህ ያሉ የክፍያ ቅድሚያ ያላቸው በዋስትና ያልተጠበቁ ዕዳዎችን ከመልሶ ማዋቀር ነጻ ሊያደርግ ይችላል።

፲፪/ በሥራ ላይ ባሉ ማናቸውም ሕጎች የተደነገገው ቢኖርም መልሶ ከማቋቋሙ ተግባር ጋር በተያያዘ የሞግዚት አስተዳዳሪው ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በማግኘት አንድ ወይም ሁሉንም ዳይሬክተሮች እና የሥራ አመራር ኃላፊዎች በመሻር የብሔራዊ ባንክን ዝቅተኛ መስፈርቶች በሚያሟሉ ሌሎች ሰዎች ሊተካ ይችላል፤ በዚህ አግባብ የተሾሙ አባላት ሹመታቸው በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ ይኖርበታል።

10/ The restructuring of debts shall follow the order of priorities applicable in liquidation process as stipulated under Article 62 of this Proclamation.

11/ Mandatory debt restructuring shall not apply to secured debt. In addition, National Bank may exempt classes of senior unsecured debt from restructuring if it determines that the classes to be systemic or of strategic importance and hence necessitate differential treatment from other senior unsecured debt.

12/ As part of the rehabilitation effort and subject to approval of National Bank, the official administrator, despite any existing laws, may remove one or all of the directors and management members and replace with others who fulfill the minimum requirement of the National Bank and secure approval accordingly.

፲፫/ የባንኩ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች፣ ዳይሬክተሮች፣ ሥራ አመራር፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ የሒሳብ ባለሙያዎች ወይም ሌሎች ባለሙያዎች ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን ወይም የማጭበርበር ድርጊቶችን ፈጽመዋል ብሎ ለማመን የሞግዚት አስተዳዳሪው በቂ ምክንያት ያለው እንደሆነ ወዲያውኑ ለብሔራዊ ባንክ እና ለሌሎች የሚመለከታቸው ሕግ አስፈጻሚ አካላት ማሳወቅ እና ለደረሰው ጉዳት ካሣ ለማስከፈል እና ንብረት ለማስመለስ የፍትሐ ብሔር ክስ መመስረት አለበት።

፵፱. **<u>የሞግዚት አስተዳደርን ስለማቋረጥ እና/ወይም የሞግዚት አስተዳዳሪን ስለማሰናበት</u>**

፩/ ማንኛውም የሞግዚት አስተዳደር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፩ በተደነገገው መሠረት የመጀመሪያው ጊዜ ወይም በዚያ ላይ የተደረገ ማንኛውም ማራዘሚያ ሲያበቃ ይቋረጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፡-

ሀ) የሞግዚት አስተዳዳሪው ለብሔራዊ ባንክ አሳማኝ በሆነ መልኩ ሥራዎቹን ሳይሠራ የቀረ እንደሆነ፤

ለ) የሞግዚት አስተዳዳሪውን ለመሾም ምክንያት የነበሩ ጉዳዮች የቀሩ በመሆኑ የሞግዚት አስተዳዳሪው በኃላፊነቱ ላይ መቀጠሉ አስፈላጊ ያልሆነ እንደሆነ፣

13/ If the official administrator has sufficient reason to believe that shareholders with significant ownership, directors, management, legal professionals, accountants, or other professionals of the bank have engaged in illegal activities or fraudulent activities, it shall immediately notify to the National Bank and other law enforcement authorities and shall initiate civil action to claim damages and restitution.

49. **<u>Termination of Official Administration and/or Official Administrator</u>**

1/ An official administration shall be terminated at the expiry of the first instance period or any extension made thereof as specified under Article 41 of this Proclamation.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, an official administration may be terminated before the expiry of the period if:

a) official administrator fails to perform his functions in a manner satisfactory to the National Bank;

b) the grounds on which the appointment of the official administrator was made no longer justify the continuance of the official administrator in office;

ሐ) በሞግዚት አስተዳደር ሥር ያለው ባንክ ፈቃድ እንዲሰረዝ ወይም የባንኩ ንብረት መጣራት መጀመር እንዳለበት ብሔራዊ ባንክ የወሰነ እንደሆነ፤

ማንኛውም የሞግዚት አስተዳደር ጊዜው ከማብቃቱ በፊት ሊቋረጥ ይችላል።

፫/ የሞግዚት አስተዳዳሪው በዝርዝር ሪፖርት አስደግፎ የሞግዚት አስተዳደሩ እንዲቋረጥ በሚያቀርበው ምክረ ሐሳብ መሠረት ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳደሩን ለማቋረጥ ሊወስን ይችላል።

፬/ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ያለ ማንኛውም ባንክ የሞግዚት አስተዳደር ጊዜ ማብቃት ወይም የሞግዚት አስተዳደር መጠናቀቅ ወይም የሞግዚት አስተዳዳሪ መሰናበት በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ወዲያውኑ እንዲታተም ያደርጋል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) የተደነገገው ቢኖርም የሞግዚት አስተዳደሩ በሚቋረጥበት ጊዜ ባንኩ ያልተዘጋ እንደሆነ ሹመታቸው በብሔራዊ ባንክ የጸደቀ አዲስ ዳይሬክተሮች ሥራ እስኪጀምሩ ድረስ የሞግዚት አስተዳዳሪው በኃላፊነት ላይ ይቆያል፤ እንዲሁም ሥራውን ይቀጥላል።

c) National Bank decides that the license of a bank under official administration be revoked or liquidation of the bank needs to commence.

3/ National Bank may decide to terminate the official administration based on recommendation of the official administrator accompanied with detailed report supporting the recommendation.

4/ Expiration of the period of official administration or completion of official administration or dismissal of an official administrator of a bank under official administration shall be immediately published by the National Bank in newspapers of wide circulation.

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1), (2) and (3) of this Article, where termination of an official administration does not involve a closure of the bank, the official administrator shall stay in office and carry on his duties up until new directors whose appointments have been approved by National Bank are instituted.

፮/ የሞግዚት አስተዳዳሪው የሞግዚት አስተዳደሩ ወይም ሹመቱ በተቋረጠ በስድሳ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ እና የተሟላ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለብሔራዊ ባንክ ያቀርባል። በተጨማሪም የባንኩን ንብረቶች፣ ቢሮዎች፣ ሀብት፣ መዛግብት እና ሰነዶች አዲስ ለተሾመው የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ መሠረት ለተሾመ ንብረት አጣሪ ያስረክባል።

፯/ ብሔራዊ ባንክ በማንኛውም ጊዜ እንዲፈርስ የተወሰነን ባንክ ፈቃድ ወዲያውኑ እንዲሰረዝ እና ባንኩ ሥራውን እንዲያቆም ሊያደርግ ይችላል።

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት እንዲፈርስ የተወሰነ ባንክ "የባንኩን ንብረት ማጣራት ላይ ያለ" የሚለው ሐረግ በስሙ ላይ ተጨምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፫ መሠረት መፍረሱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሕጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ ይቀጥላል።

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሞግዚት አስተዳደሩ ጊዜው ከማብቃቱ በፊት የተቋረጠ ከሆነ ለሞግዚት አስተዳዳሪው ካገለገለበት ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ ይከፈለዋል።

## ፶. ፈቃድ ስለመሰረዝ

፩/ ብሔራዊ ባንክ በሚከተሉት ምክንያቶች የማንኛውንም ባንክ ፈቃድ ወዲያውኑ ሊሰርዝ ይችላል፦

ሀ) የባንኩ ፈቃድ የተሰጠው በሐሰት ወይም በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመስርቶ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

6/ The official administrator shall within sixty days of the termination of the official administration or termination of the appointment, prepare and submit a final and comprehensive report to the National Bank. Moreover, he shall handover the properties, offices, assets, books, and records of the bank to the newly constituted board of directors of the bank or a liquidator as appointed in line with Article 51 of this Proclamation.

7/ National Bank may immediately revoke the license of a bank decided to be liquidated at any point in time and cease operation of the bank.

8/ A bank decided to be liquidated on the basis of Sub-Article (7) of this Article shall get the phrase "under liquidation" added to its name and retain its legal personality until the liquidation is concluded in accordance with Article 63 of this Proclamation.

9/ If the official administration is terminated before expiry of the office period in line with Sub-Article (2) of this Article, remuneration of the official administrator shall be proportional to the period it served.

## 50. Revocation of License

1/ National Bank may revoke the license of any bank immediately if:

a) it is confirmed that the licensing of the bank was made on the basis of false or wrong information;

ለ) ፈቃድ በተሰጠው በአሥራ ሁለት ወራት ውስጥ ባንኩ ሥራውን ያልጀመረ እንደሆነ፤

ሐ) ባንኩ የገንዘብ አከል ንብረት እጥረት የገጠመው እንደሆነ፤

መ) ባንኩ ዕዳ መክፈል የማይችልበት ወሰን ላይ ከደረሰ ወይም በቀጣዮቹ ስልሳ ቀናት ውስጥ ዕዳ መክፈል የማይችልበት ወሰን ላይ ሊደርስ የሚችል ከሆነ፤

ሠ) ባንኩ ሥራውን የሚያከናውነው የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የሕዝቡን ጥቅም በሚጻረር ወይም በሚጎዳ መልኩ ከሆነ፤

ረ) ባንኩ ሕገ-ወጥ ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወይም ለሽብርተኛ የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ ወንጀል በሀገር ውስጥ ወይም ሕጋዊ ሥልጣን ባለው ሌላ ማንኛውም ፍርድ ቤት ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ ከሆነ ወይም እንዲህ ባለው ወንጀል ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ እናት ባንክ ወይም ሆልዲንግ ኩባንያ አጋር ወይም ተቀጥላ ከሆነ፤

ሰ) ባንኩ ብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ በጽሑፍ ሳይፈቅድ ከሌላ ባንክ ጋር ውህደት ከፈጸመ፣ በሌላ ባንክ ከተገዛ ወይም ለሌላ ባንክ ሥራውን ካስተላለፈ ወይም በፈቃደኝነት መፍረስ ከጀመረ፤

ሸ) ባንኩ በሕግ ራሱን እንደቻለ ድርጅት ያለው ህልውና ከከሰመ፤

ቀ) ባንኩ በፈቃደኝነት ለመፍረስ ያቀረበውን ጥያቄ ብሔራዊ ባንክ ካጸደቀው፤

በ) ባንኩ ይህን አዋጅ፣ መመሪያዎችን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎችን በተደጋጋሚ የጣሰ እንደሆነ።

b) the bank has failed to commence operations within twelve months following the grant of the license;

c) the bank becomes illiquid;

d) the bank becomes insolvent or is likely to become insolvent over the next sixty days;

e) the bank carries on business in a manner contrary to or detrimental to the interest of depositors or the public;

f) the bank has been convicted by a domestic court or any other court of competent jurisdiction of a crime related to money laundering or terrorist financing or is an affiliate or subsidiary of a parent or holding company which has been so convicted;

g) the bank is merged with, or acquired by, or transferred its business to another bank or started voluntary liquidation without the prior written authorization of National Bank;

h) the bank has ceased to exist as a legally independent entity;

i) National Bank approves the voluntary liquidation request of the bank; or

j) the bank persistently contravenes this Proclamation, Directives or other relevant laws.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ባንክ በአስቸኳይ ሁኔታዎች ውስጥ የሕዝብን ጥቅም ከግምት በማስገባት የማንኛውንም ባንክ ፈቃድ ያለ ማስጠንቀቂያ ሊሰርዝ ይችላል።

፫/ ብሔራዊ ባንክ የማንኛውንም ባንክ ፈቃድ ለመሰረዝ ሲወስን ፈቃዱ የተሰረዘበት ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት አካባቢ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ እንዲሁም በድረ-ገጹ ላይ ውሳኔውን አሳትሞ ያወጣል።

፬/ የፈቃድ ስረዛ ውሳኔው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ወይም ብሔራዊ ባንክ ከሚወስነው ማንኛውም ሌላ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

፭/ ፈቃድ የተሰረዘበት ማንኛውም ባንክ የፈቃድ ስረዛ ውሳኔው ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ማንኛውንም ዓይነት የባንክ ሥራ መሥራት አይችልም።

፮/ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለመሰረዝ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው የፈቃድ ስረዛው ውሳኔ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል።

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተደነገገው ቢኖርም ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ መሠረት ሥልጣኑን፣ ተግባራቱን እና ሥራዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ለመፈጸም እና ለመወጣት የሚወስናቸውን ውሳኔዎች ለማሳገድ በማንኛውም ፍርድ ቤት ክስ መመሥረት አይቻልም፤ ሆኖም ግን በዚህ እርምጃ የተነሣ ማናቸውንም መብቶች ማስጠበቅ ያልተቻለ እንደሆነ መብቱን ማስጠበቅ ያልቻለው ሰው ከብሔራዊ ባንክ የገንዘብ ካሣ የማግኘት መብት አለው።

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the National Bank, in cases of emergency and consideration of public interest, may revoke the license of a bank without notice.

3/ The decision to revoke the license of a bank shall be published by National Bank in a newspaper of wide circulation at the place where the head office of the bank is situated and through its website.

4/ The revocation of license of the bank shall become effective on the date of its publication or on any other date as the National Bank may specify.

5/ A bank shall be prohibited from engaging in any banking business starting from the effective date of the revocation of its banking license.

6/ Any person aggrieved by the decision of the National Bank to revoke the license may submit review to the Federal High Court within thirty days from the effective date of the revocation.

7/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (6) of this Article, no action or proceeding may be instituted in any court for the purpose of staying the decisions by the National Bank in the exercise, performance and discharge the powers, duties and functions under this Proclamation, provided however, that if any specific protection of rights is rendered impossible taken as a consequence of this measure, the affected party shall have the right

፰/ ማንኛውም ፈቃድ በዚህ ክፍል መሠረት በሚሰረዝበት ጊዜ የባንኩን ንብረት ማጣራት ሂደት በብሔራዊ ባንክ አነሳሽነት ይጀመራል።

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለመሰረዝ የወሰነው ውሳኔ እንዲሻር በማንኛውም ፍርድ ቤት ክስ መመሥረት አይቻልም።

**፶፩. ንብረት አጣሪ ስለመሾም**

፩/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የማንኛውንም ባንክ ፈቃድ የሰረዘ እንደሆነ ባንኩን የሚቆጣጠር እና ንብረቱን የሚያጣራ ንብረት አጣሪ ይሾማል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ ለአንድ ባንክ ንብረት አጣሪ መሾሙን፣ ለሹመት ምክንያት የሆነውን ጉዳይ፣ የንብረት አጣሪውን ስም፣ ሹመቱ የሚጸናበትን ቀንና ማናቸውንም ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች በመጥቀስ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ ላይ እና በድረ-ገጹ አሳትሞ ያወጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሾመ ማንኛውም ንብረት አጣሪ ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ባንክ ይሆናል።

፬/ ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እራሱ በንብረት አጣሪነት ሊሠራ ይችላል።

to financial compensation payable by National Bank.

8/ Where a license is revoked under this section, National Bank shall initiate the liquidation process.

9/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (6) of this Article, no action or proceeding may be instituted in any court for reversing the decision taken by National Bank to revoke the license.

**51. <u>Appointment of Liquidator</u>**

1/ National Bank shall appoint a liquidator to take control and liquidate a bank if it has revoked the license of the bank as stipulated under Article 50 (1) and (2) of this Proclamation.

2/ National Bank shall publish the appointment of a liquidator, the reason for the appointment, the name of the liquidator, the effective date and any other relevant information, through a newspaper of wide circulation and its website.

3/ A liquidator appointed pursuant to this Article shall be accountable to the National Bank.

4/ National Bank may act as a liquidator if it deems it necessary.

**፶፪. የንብረት አጣሪ መሾምን በመቃወም ስለሚቀርብ አቤቱታ**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ (፪) መሠረት ንብረት አጣሪ ስለመሾሙ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሠላሳ ቀናት ውስጥ ከባንኩ አክሲዮኖች ቢያንስ ሀያ አምስት በመቶ የመምረጥ መብት ያላቸው አክሲዮኖችን የያዙ ባለአክሲዮኖች የንብረት አጣሪውን መሾም በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አቤቱታ የቀረበ እንደሆነ፦

ሀ) ፍርድ ቤቱ በአቤቱታው ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ንብረት ማጣራቱ ይቀጥላል፤

ለ) ፍርድ ቤቱ አቤቱታው በቀረበ በአሥር ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ይሰማል፤ ምርመራው በተጠናቀቀ በሀያ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት አቤቱታ ሲቀርብ በፍርድ ቤቱ መታየት የሚችለው ብቸኛ ጭብጥ ብሔራዊ ባንክ ንብረት አጣሪውን የሾመው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶ እና ፶፩ ከተደነገጉት መስፈርቶች አንጻር ሲታይ ተጨባጭነት በሌለው እና ባልተገባ መልኩ መሆን አለመሆኑን ብቻ ነው።

፬/ ፍርድ ቤቱ ብሔራዊ ባንክ ንብረት አጣሪውን የሾመው፦

ሀ) ተጨባጭነት በሌለው እና ባልተገባ መልኩ ነው ብሎ ከወሰነ የንብረት አጣሪው ሹመት እንዲቋረጥ ትዕዛዝ ይሰጣል፤ ወይም

ለ) ተጨባጭነት በሌለው እና ባልተገባ መልኩ አይደለም ብሎ ከወሰነ አቤቱታው ውድቅ ሆኖ ንብረት ማጣራቱ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጥላል።

**52. Review Against Appointment of Liquidator**

1/ Shareholders of a bank holding in the aggregate at least twenty-five percent of the voting shares of the bank may request a review to the Federal High Court against the appointment of a liquidator within thirty days after the date on which the liquidation is announced in newspaper pursuant to Article 51(2) of this Proclamation.

2/ Where a request for review is lodged in accordance with Sub-Article (1) of this Article:

a) The liquidation shall continue until the court delivers a final ruling on the review;

b) The court shall hold a hearing on the matter within ten days of the filing of the review and shall decide the review within twenty days of the end of the investigation.

3/ The sole issue to be adjudicated by the court shall be whether the National Bank acted in unrealistic and inappropriate manner in establishing the liquidation, in light of the criteria set forth in Article 50 and 51 of this Proclamation.

4/ If the court determines that the National Bank, in appointing the liquidator:

a) did act in unrealistic and inappropriate manner, it shall order the termination of the appointment of the liquidator; or

b) did not act in unrealistic and inappropriate manner, the review shall be denied and the liquidation shall continue in accordance with the provisions of this Proclamation.

**፶፫. <u>ለንብረት አጣሪነት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>**

፩/ በብሔራዊ ባንክ የሚሾም ማንኛውም ንብረት አጣሪ በብሔራዊ ባንክ አተያየት ከፍተኛ የሙያ ብቃት እና ታማኝነት ያለው ሰው መሆን አለበት።

፪/ ንብረት አጣሪው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በሚሆንበት ጊዜ፦

ሀ) ንብረት ማጣራቱን በበላይነት የሚመራው ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን መስፈርት ማሟላት፤እና

ለ) በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በቂ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ከታወቀ የመድን ሰጪ ኩባንያ ወይም ባንክ ማቅረብ

አለበት።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ንብረት አጣሪ ተደርጎ የሚሾም ማንኛውም ሰው ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ የሚያወጣቸውን ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

**፶፬. <u>የንብረት አጣሪ የአገልግሎት ክፍያዎች</u>**

፩/ ለንብረት አጣሪ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ መጠን በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል።

፪/ የንብረት አጣሪ የአገልግሎት ክፍያ ንብረቱ በመጣራት ላይ ባለው ባንክ እጅ በሚገኝ ገንዘብ ወይም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የባንኩ ንብረት ተሸጦ በሚገኝ ገቢ ይሸፈናል።

**53. <u>Qualifications of Liquidator</u>**

1/ A liquidator to be appointed by National Bank shall, in the opinion of the National Bank, be of the highest professional qualifications and personal integrity.

2/ Where the liquidator is a juridical person:

a) the principal officer in charge of liquidation shall meet the qualification requirements stipulated under Sub-Article (1) of this Article; and

b) the juridical person shall provide adequate performance guarantee from a reputable insurance company or a bank.

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article, any person to be appointed as liquidator shall meet such other additional requirements as may be specified by National Bank Directive.

**54. <u>Remunerations for the Service of Liquidator</u>**

1/ The amount of remunerations for services of a liquidator shall be determined by National Bank.

2/ The remuneration of a liquidator shall be paid either from a fund available with the bank under liquidation or from the proceeds of liquidation pursuant to the provisions of this Proclamation.

**፶፭. ንብረት ማጣራት የሚቆይበት ጊዜ**

፩/ የማንኛውም ባንክ ንብረት ማጣራት የሚቆይበት ጊዜ በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም የባንክ ንብረት አጣሪ የተጣለበትን ኃላፊነት አጥጋቢ በሆነ መንገድ አልተወጣም ብሎ ሲያምን በማንኛውም ጊዜ ከሥራ ሊያሰናብተው ይችላል።

፫/ ብሔራዊ ባንክ የንብረት ማጣራት የሥራ ጊዜ እንደተጠናቀቀ ወይም ንብረት አጣሪው ከሥራ እንደተሰናበተ ወዲያውኑ ይህንኑ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ አሳትሞ ያወጣል።

**፶፮. የንብረት አጣሪ መሾም የሚያስከትለው ውጤት**

ማንኛውም ባንክ ንብረት አጣሪ እንደተሾመለት ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በጋዜጣ እና ድረ-ገጽ እንዳስታወቀ፦

፩/ ከንብረት አጣሪው ቅድሚያ ፈቃድ ካልተገኘ በስተቀር በባንኩ ስም ምንም ዓይነት እርምጃ ሊወሰድ አይችልም፤

፪/ የባንኩ ባለአክሲዮኖች፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ሥልጣን ታግዶ ለንብረት አጣሪው ይተላለፋል፤

፫/ የባንኩ መብትና ሥልጣን እንዲሁም ማንኛውም ገንዘብ አስቀማጭ ወይም አበዳሪ በባንኩ ወይም በባንኩ ንብረቶች ላይ ያለው መብትና ሥልጣን ወዲያውኑ ወደ ንብረት አጣሪው ይተላለፋሉ፤

፬/ ንብረት አጣሪው የባንኩን ንብረቶች እና መዛግብት በሙሉ ይቆጣጠራል፤

**55. Duration of Liquidation**

1/ The duration of liquidation of any bank shall be determined by National Bank.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, National Bank may, at any time, dismiss liquidator of a bank on grounds of failure to perform his functions in a manner satisfactory to the National Bank.

3/ Expiration of the period of liquidation or dismissal of liquidator of a bank shall immediately be published by the National Bank in newspapers of wide circulation.

**56. Effects of Appointment of Liquidator**

Upon the publication of the appointment of a liquidator to a bank by the National Bank in newspaper of wider circulation and its website pursuant to Sub-Article (2) of Article 51 of this Proclamation:

1/ No action may be taken on behalf of the bank without the prior approval of the liquidator;

2/ The powers of the shareholders, board of directors and the executive management of the bank shall be suspended and vested in the liquidator;

3/ All rights and powers of the bank and all rights and powers that any depositor or creditor has over the bank or its assets shall automatically be vested in the liquidator;

4/ The liquidator shall take control over the assets and records of the bank;

፭/ የባንኩ ንብረት በሚጣራበት ጊዜ በባንኩ ንብረት ላይ አዲስ የፍርድ ቤት እግድ ሊተላለፍ ወይም ዋስትና ሊሰጥ አይችልም፤

፮/ የሕግ፣ የውልም ሆነ ሌላ ማንኛውም የይርጋ ጊዜ በሚያበቃበት ጊዜ ማንኛውም የባንኩ የይገባኛል ጥያቄ ወይም መብት የሚያበቃ ወይም የሚጠፋ ከሆነ የይርጋ ጊዜው ከሚያበቃበት ቀን አንስቶ ለስድስት ወራት ይራዘማል፤

፯/ በባንኩ ግዴታዎች ላይ ወለድ እና ቅጣት መሰላቱ ይቆማል እንዲሁም በባንኩ ግዴታዎች ላይ ማንኛውም ሌላ ክፍያ ወይም ዕዳ አይታሰብም፤

፰/ በባንኩ ላይ የቀረበ ማንኛውም ክስ እንዲሁም በባንኩ ሀብት ላይ ያለ ማንኛውም የመብት አፈጻጸም ይታገዳል፤

፱/ የባንኩ ንብረት በሚጣራበት ጊዜ የሦስተኛ ወገን መብት በባንኩ ንብረት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም እንዲሁም ማንኛውም አበዳሪ ማንኛውንም የይገባኛል ጥያቄ ለማስፈጸም ወይም ማንኛውንም ክስ በመመስረት ወይም በማስቀጠል በባንኩ ንብረት ላይ ያለን ዕዳ ለመሸፈን ወይም ፍጹም የዋስትና ጥቅም ለማስጠበቅ የባንኩን ንብረት በፍርድ ቤት ማሳገድ፣ መሸጥ ወይም መያዝ አይችልም።

፲/ የሚከተሉት ክፍያዎች ወይም የባንክ ንብረት ዝውውሮች የገንዘብ አስቀማጮችን ጥቅም የሚጎዱ ከሆነ ወይም ከሌሎች የባንኩ አበዳሪዎች ወይም ገንዘብ አስቀማጮች በላይ ለተቀባዩ ቅድሚያ የመስጠት ውጤት አላቸው ብሎ ብሔራዊ ባንክ ካመነ ተፈጻሚ አይሆኑም፡-

5/ No new attachment or lien shall be effected to any of the assets of the bank during liquidation;

6/ Any period of limitation, either statutory, contractual, or otherwise, on the expiration of which a claim or right of the bank would expire or be extinguished, shall extend by six months from the date of such expiration;

7/ The calculation of interests and penalties against the obligations of the bank shall be suspended and no other charge or liability shall accrue on the obligations of the bank;

8/ Any legal proceeding against the bank shall stay and the exercise of any right on the assets of the bank shall be suspended;

9/ The right of a third-party shall not be exerted over assets during liquidation of the bank and a creditor shall not attach, sell, or take possession of any assets of the bank as a means of enforcing a claim or initiating or continuing any legal proceeding to recover the debt or perfect security interest in the assets of the bank;

10/ The following payments or transfers of assets of the bank shall be void if they are detrimental to depositors' interest or if it is believed by National Bank that it has the effect of bestowing a preference of the recipient over other creditors or depositors of the bank:

ሀ) ንብረት ማጣራቱ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን በፊት ባሉት ሶስት ወራት ውስጥ የተደረጉ ማናቸውም የፋይናንስ ግብይቶች፤

ለ) ንብረት ማጣራቱ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን በፊት ባለው አንድ ዓመት ውስጥ ከባንኩ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ሠራተኛ ወይም አጋር ጋር የተደረጉ የፋይናንስ ግብይቶች፤

ሐ) ንብረት ማጣራቱ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን አስቀድሞ ባለው አንድ ዓመት በፊት ለሦስተኛ ወገን በነጻ የተላለፉ፤

መ) በማንኛውም ጊዜ የሐሰት ወይም የተጭበረበሩ ሰነዶችን መሠረት በማድረግ የተደረገ የፋይናንስ ግብይት፤

ሠ) ከባንኩ አበዳሪዎች ንብረቶችን ለመያዝ ወይም በሌላ መልኩ መብታቸውን ለመጉዳት በማሰብ ንብረት ማጣራቱ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን በፊት ባለው አንድ ዓመት ውስጥ የተፈጸመ ማንኛውም ድርጊት፤

ረ) የባንኩ ንብረት በሚጣራበት ጊዜ አበዳሪው የሚያገኘውን ገንዘብ መጠን የመጨመር ውጤት ያለው ሆኖ፤ ንብረት ማጣራቱ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን በፊት ባለው አንድ ዓመት ውስጥ የተገባን ዕዳ ለመክፈል ሲባል ለማንኛውም አበዳሪ የተደረገ የባንክ ንብረት ዝውውር፤

ሰ) ንብረት ማጣራቱ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን በፊት ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ከነበረ የፍርድ ቤት እግድ ወይም ዋስትና ውጭ የሆነ ማንኛውም የፍርድ ቤት እግድ ወይም ዋስትና፡፡

a) any transactions made before a period of three months from the effective date of liquidation;

b) transactions with shareholder, director, an employee or affiliate of the bank made within one year before the effective date of liquidation;

c) gratuitous transfers to third parties made within one year before the effective date of the liquidation;

d) a transaction made based on a forged or fraudulent documents at any time in point;

e) any act done with the intention to withhold assets from the creditors of the bank or otherwise impair their rights, within one year before the effective date of the liquidation;

f) transfers of property of the bank to, or for the benefit of a creditor on account of a debt incurred within one year before the effective date of liquidation, which has the effect of increasing the amount that the creditor would receive in a liquidation of the bank; or

g) any attachment or security interest other than an attachment or security interest that existed six months before the effective date of the liquidation.

፲፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፲ የተደነገገው፦

ሀ) መጠኑ ብሔራዊ ባንክ ለዚሁ ዓላማ ሲባል በሚያወጣው መመሪያ ከተወሰነው ጣሪያ በማይበልጥ ለእያንዳንዱ አስቀማጭ በተከፈለው የተቀማጭ ገንዘብ ክፍያ፣

ለ)እንዲተላለፍ የተደረገው ንብረት ዋጋ ገበያ ከሚሰጠው ዋጋ አኳያ ሲታይ ተነጻጻሪነት ያለው ሆኖ በዚሁ አግባብ የተደረገ የንብረት ማስተላለፍ፣

ሐ) ጉርሻና ሌሎች ልዩ ክፍያዎችን ሳይጨምር ለባንኩ ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች በተከፈለ መደበኛ ክፍያና ጥቅማ ጥቅም፣

መ) በተመሳሳይ ጊዜ የሚደረግ ተመሳሳይ ዋጋ ያለው ግብይት አካል የሆነ ክፍያ ወይም የንብረት ማስተላለፍ፣ ወይም

ሠ) በመደበኛ የሥራ ሂደት እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሞግዚት አስተዳዳሪ የሚደረግ ክፍያ ወይም የንብረት ማስተላለፍ፣

ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## ፶፯. ውል ስለማፍረስ

፩/ ንብረት አጣሪው የገንዘብ አስቀማጮችን ጥቅም ማስጠበቅን ከግምት ውስጥ በማስገባት ውሉን መፈጸም ለባንኩ ከባድ ይሆናል ብሎ ያመነ እንደሆነ ከተሾመበት ቀን አንስቶ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ማንኛውንም ያልተፈጸመ ወይም በከፊል የተፈጸመ ውል ሊያፈርስ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት ውል ከመፍረሱ የሚመነጭ ማንኛውም ተጠያቂነት ውል በፈረሰበት ቀን ይወሰናል እንዲሁም በተጨባጭ በቀጥታ በተከሰተው ጉዳት መጠን የሚወሰን እና ለታጣ ትርፍ የሚከፈል ማንኛውንም የጉዳት ካሣ የማያካትት ይሆናል።

11/ The provisions of Sub-Article (10) of this Article may not apply to the:

a) payment of deposits in an amount per depositor not exceeding the limit to be set in a Directive to be issued by National Bank for this purpose;

b) transfer of an asset of the bank made in any consideration the value of which is equal to the fair market value of the asset;

c) payment of ordinary remuneration and benefits, excluding bonuses and special payments, to the directors and employees of the bank;

d) payment or transfer that was made as part of a contemporaneous exchange for reasonably equivalent value; or

e) payment or transfer made by an official administrator in the ordinary course of business and in line with this Proclamation.

## 57. Repudiation of Contracts

1/ The liquidator may, within thirty days of the date of appointment, repudiate any non-performed or partially performed contract if it is believed that the fulfillment of the contract is burdensome for the bank in consideration of protecting the interests of depositors.

2/ Any liability arising from the repudiation as provided under Sub-Article (1) of this Article shall be determined as of the date of repudiation and shall be limited to actual direct damages incurred and exclude any damage for lost profits.

፫/ የማይንቀሳቀስ እና የተንቀሳቃሽ ንብረት የኪራይ ውል በሚፈርስበት ጊዜ ንብረት አጣሪው የሠላሳ ቀናት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት።

**፶፰. የንብረት አጣሪ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ መሠረት የተሾመ ንብረት አጣሪ ንብረቱ የሚጣራውን ባንክ የማስተዳደርና የመቆጣጠር ሙሉና ብቸኛ ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

፪/ በብሔራዊ ባንክ ንብረት አጣሪ ሲሾም ንብረት አጣሪው በቅድሚያ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ ሊወስዳቸው የማይችላቸውን እርምጃዎች ሊወስን ይችላል።

፫/ በስርቆት ወይም በሌላ አግባብ ያልሆነ ድርጊት የተነሳ የሚከሰት ብክነትን ለመከላከል ሲባል ንብረት አጣሪው ንብረቱ በመጣራት ላይ ያለውን ባንክ ንብረቶች፣ ቢሮዎች፣ መዛግብትና ሰነዶች እና ሀብት ይቆጣጠራል።

፬/ ንብረት አጣሪው የተሰጡትን መብቶች እና ሥልጣኖች ተግባራዊ በሚያደርግበት ወቅት፦

ሀ) ከንብረቶች ሽያጭ የላቀ ገቢ እንዲገኝ ያደርጋል፤ እና

ለ) የባንኩን ንብረት ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማጣራት አስፈላጊ የሆነ ማንኛውንም እርምጃ ይወስዳል።

፭/ የባንኩ ባለአክሲዮኖች፣ ዳይሬክተሮች፣ ኃላፊዎች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ የሒሳብ ባለሙያዎች ወይም ሌሎች ባለሙያዎች ከባንኩ ሥራ ጋር በተያያዘ ሕገ-ወጥ ወይም የማጭበርበር ድርጊት ፈጽመዋል ወይም እየፈጸሙ ነው ብሎ ለማመን ንብረት አጣሪው በቂ ምክንያት ያለው እንደሆነ ወዲያውኑ ለብሔራዊ ባንክ እና ለሌሎች የሚመለከታቸው ሕግ አስፈጻሚ አካላት ማሳወቅ እና ለደረሰ ጉዳት ካሣ ለማስከፈል እና ንብረት ለማስመለስ

3/ In case of the repudiation of a contract for the lease of immovable and movable property, the liquidator shall give a notice of thirty days.

**58. Powers and Duties of the Liquidator**

1/ A liquidator appointed pursuant to Article 51 of this Proclamation shall be vested with the full and exclusive powers and duties of management and control of the bank under liquidation.

2/ The National Bank may, upon appointing the liquidator, specify certain actions for which the liquidator shall obtain prior approval from the National Bank.

3/ The liquidator shall secure the property, offices, books and records, and assets of the bank under liquidation so as to prevent dissipation by theft or other improper action.

4/ The liquidator in exercising the rights and powers vested in itself, shall:

a) maximize the proceeds from the sale of assets; and

b) take any action necessary for the efficient liquidation of the bank.

5/ The liquidator shall notify National Bank and other pertinent law enforcement bodies immediately and institute a civil action to claim damages and restitution, if it has sufficient reason to believe that the shareholders, directors, officers, legal professionals, accountants, or other professionals have engaged or are engaging in unlawful or fraudulent activity in relation to the business of a bank.

የፍትሐ ብሔር ክስ መመስረት አለበት።

፮/ ንብረት አጣሪው ባንኩን በያዘ በሁለት ወራት ውስጥ የባንኩን የሀብት እና ንብረት ቆጠራ በማከናወን የሀብት እና ንብረት ቆጠራ ሪፖርቱን ቅጂ ለብሔራዊ ባንክ ያስተላልፋል፤ ብሔራዊ ባንክም የሀብት እና ንብረት ቆጠራ ሪፖርቱን በመላው ሀገሪቱ ስርጭት ባላቸው በሁለት ዕለታዊ ጋዜጣዎች፣ በመደበኛ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ እንዲሁም በብሔራዊ ባንክ ድረ-ገጽ ላይ ያሳትማል።

፯/ ንብረት አጣሪው ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው ቅጽ መሠረት በየወሩ የአፈጻጸም ሪፖርት ለብሔራዊ ባንክ ያቀርባል እንዲሁም በብሔራዊ ባንክ የሚጠየቀውን ማንኛውንም መረጃ ይሰጣል።

፰/ ንብረት አጣሪው ማንኛውም ገንዘብ አስቀማጭ በባንኩ ያለውን የተቀማጭ ገንዘብ ከባንኩ ለተበደረው እና ላልከፈለው ገንዘብ ማቻቻያ ሊያደርገው ይችላል።

፱/ አንድ ባንክ ፈቃዱ ቢሰረዝም እንኳን ንብረት አጣሪው በተሾመበት ሰዓት ተፈጻሚ በነበረ ውል መሠረት እና ብሔራዊ ባንክ በግልጽ ሲፈቅድ ንብረት አጣሪው ለማንኛውም ነባር ደንበኛ ብድር ሊሰጥ ይችላል።

፲/ ንብረት አጣሪው የንብረት ማጣራቱን ዓላማ ለማሳካት በአግባቡ ጥቅም ላይ ይውላል ብሎ የሚያምነውን የገንዘብ መጠን በተሾመ በሠላሳ ቀናት ለገንዘብ አስቀማጮች እና ለሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ክፍያ ሊፈጽም ይችላል።

6/ The liquidator shall, within two months of taking possession of a bank, take an inventory of the assets and property of that bank and transmit a copy of the inventory report to the National Bank; and the National Bank shall publish the inventory report in two daily newspapers of national circulation, formal electronic media and on its website.

7/ The liquidator shall monthly submit progress report to the National Bank in the form prescribed by National Bank and provide any information upon the request of the National Bank.

8/ The liquidator may set-off the deposit liabilities to any depositor against outstanding loan payments owed by that depositor.

9/ Despite the revocation of the license of a bank, a liquidator may extend credit to an existing customer in accordance with the terms of an agreement in force at the time of the appointment of the liquidator and with the express approval of National Bank.

10/ Within thirty days from the date of appointment, the liquidator may make payments to depositors or to other creditors of such amounts that in the opinion of the liquidator may appropriately be used for meeting the objective of the liquidation.

፲፩/ የሕግ፣ የውልም ሆነ ሌላ ማንኛውም የይርጋ ጊዜ በሚያበቃበት ጊዜ ማንኛውም የባንኩ የይገባኛል ጥያቄ ወይም መብት የሚያበቃ ወይም የሚጠፋ ከሆነ የይርጋ ጊዜው ከሚያበቃበት ቀን አንሥቶ ለስድስት ወራት ይራዘማል።

፲፪/ በባንኩ ግዴታዎች ላይ ወለድ እና ቅጣት መሰላቱ ይቆማል እንዲሁም በባንኩ ግዴታዎች ላይ ማንኛውም ሌላ ክፍያ ወይም ዕዳ አይታሰብም።

፲፫/ በባንኩ ላይ የተመሠረተ ማንኛውም ክስ እንዲሁም በባንኩ ሀብት ላይ ያለ ማንኛውም መብት አፈጻጸም ይታገዳል።

፲፬/ የባንኩ ንብረት በሚጣራበት ጊዜ የሦስተኛ ወገን መብት በባንኩ ንብረት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም እንዲሁም ማንኛውም አበዳሪ ማንኛውንም የይገባኛል ጥያቄ ለማስፈጸም ወይም ማንኛውንም ክስ በመመሥረት ወይም በማስቀጠል በባንኩ ንብረት ላይ ያለን ዕዳ ለመሸፈን ወይም ፍጹም የዋስትና ጥቅም ለማስጠበቅ የባንኩን ንብረት በፍርድ ቤት ማሳገድ፣ መሸጥ ወይም መያዝ አይችልም።

**፶፱. <u>ባንክ ሲፈርስ በቅድሚያ ስለሚፈጸሙ ሥርዓቶች</u>**

፩/ ንብረት አጣሪው የባንኩን ቢሮዎች፣ የሒሳብ መዛግብት እንዲሁም ሌሎች ሰነዶች እና ሀብት ያለገደብ ማግኘት እና መቆጣጠር ይችላል።

፪/ ንብረት አጣሪው ጥያቄ በሚያቀርብበት ወቅት ማንኛውም ሕግ አስፈጻሚ አካል፦

ሀ) ንብረት አጣሪው ወደ ባንኩ የሥራ ቦታ መግባት እንዲችል እገዛ ማድረግ አለበት፤ ወይም

11/ Any period of limitation, either statutory, contractual, or otherwise, on the expiration of which a claim or right of the bank would expire or be extinguished, shall extend by six months from the date of such expiration;

12/ The calculation of interests and penalties against the obligations of the bank shall be suspended and no other charge or liability shall accrue on the obligations of the bank;

13/ Any legal proceeding against the bank shall stay and the exercise of any right on the assets of the bank shall be suspended; and

14/ The right of a third party shall not be exerted over assets during liquidation of the bank and a creditor shall not attach, sell, or take possession of any assets of the bank as a means of enforcing a claim or initiating or continuing any legal proceeding to recover the debt or perfect security interest in the assets of the bank.

**59. <u>Preliminary Procedures for Liquidation of a Bank</u>**

1/ The liquidator shall have unrestricted access to and control over the offices, books of account, other records and other assets of the bank.

2/ Upon the request of the liquidator, a law enforcement organ shall:

a) assist the liquidator to gain access to the premises of the bank; or

ለ) ንብረት አጣሪው የባንኩን መዛግብት መቆጣጠር እንዲችል እገዛ ማድረግ አለበት።

፫/ በስርቆት ወይም በሌላ አግባብ ባልሆነ ድርጊት የተነሳ የሚከሰት ብክነትን ለመከላከል ሲባል ንብረት አጣሪው የባንኩን ንብረቶች፣ ቢሮዎች፣ መዛግብት፣ ሰነዶች እና ሀብት ይቆጣጠራል።

፬/ ንብረት አጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገውን ሥልጣን ተግባራዊ በሚያደርግበት ወቅት የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል፦

ሀ) የባንኩን የፋይናንስ ሀብት ወይም መረጃዎች ወይም መሣሪያዎች የያዙ እና ማንኛውም ሰው ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ እንዲያገኛቸው የሚያስችሉ የባንኩ ውጫዊ እና ውስጣዊ መግቢያዎች ላይ ያሉ ቁልፎችን ይቀይራል እንዲሁም የአዲሶቹን ቁልፎች ተደራሽነት ውስን ያደርጋል፤

ለ) የባንኩን የይለፍ ኮዶች ይቀይራል ወይም ያበጃል እንዲሁም የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ኮምፒዩተሮች እና ሰዎች ብቻ መግባት እንዲችሉ ያደርጋል፤

ሐ) የተፈቀደላቸው ሰዎች ወደ ባንኩ የሥራ ቦታ የሚገቡባቸው ፎቶ ያላቸው መታወቂያዎችን በመስጠት ሌሎች ሰዎች ወደ ባንኩ የሥራ ቦታ እንዳይገቡ ይቆጣጠራል፤

መ) የባንኩን የፋይናንስ ኃላፊነት እንዲወጡ ለሰዎች የተሰጡ ፈቃዶችን በመሰረዝ እንደ አስፈላጊነቱ አዲስ ፈቃዶችን ይሰጣል እንዲሁም ለሚመለከታቸው ሦስተኛ ወገኖች ያሳውቃል፤

b) assist the liquidator to gain control over the records of the bank.

3/ The liquidator shall secure the property, offices, books, records, and assets of the bank to prevent dissipation by theft or other improper action.

4/ The liquidator shall in exercising its power under Sub-Article (3) of this Article, take the following actions:

a) change the locks and limit access to the new keys on external and internal entrances to the bank premise which contain financial assets or information or equipment which could enable a person to gain unlawful access;

b) change or establish access codes to the bank and grant access only to a limited number of computers and persons;

c) issue new identification passes bearing photo for entry by authorized persons to the premises of the bank and control the access of other persons to the premises of the bank;

d) cancel authorizations permitting persons to discharge the financial responsibility of the bank and issue new authorizations, as appropriate and notify to concerned third parties;

ሠ) ከዚህ ቀደም የባንኩን ንብረቶች ወይም ባንኩ በአደራ የያዛቸውን ንብረቶች በተመለከተ ከሚሠሩ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ባንኩን በመወከል ትዕዛዝ እንዲሰጡ ሥልጣን ተሰጥቷቸው የነበሩ ሰዎች ትዕዛዝ እንዲሰጡ የተሰጣቸው ሥልጣን የቀረ መሆኑን እንዲሁም ትዕዛዝ መስጠት የሚችሉት ንብረት አጣሪው እና በንብረት አጣሪው ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ብቻ እንደሆኑ፦

፩/ ለአገናኝ ባንኮች፤
፪/ ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሬጂስትራሮች እና አስተላላፊ ወኪሎች፤ እና
፫/ ለባንኩ የውጭ ሀብት አስተዳዳሪዎች፤

ያሳውቃል፡፡

ረ) የካፒታል ክፍፍልን በአጠቃላይ እንዲሁም ለዳይሬክተሮች ወይም ለቁልፍ የሥራ አመራር ኃላፊዎች ከሚከፈሉ የአገልግሎት ክፍያዎች በስተቀር ለቁልፍ የሥራ አመራር ኃላፊዎች እና ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ላላቸው ባለአክሲዮኖች የሚከፈሉ ክፍያዎችን ያግዳል፤ እና

ሰ) የንብረት አጣሪውን ሥልጣን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመወጣት አስፈላጊ የሆነ ማንኛውንም እርምጃ ይወስዳል።

e) inform

1) correspondent banks,
2) registrars and transfer agents of securities; and
3) external asset managers of the bank

that persons who previously had authorization to give instructions on behalf of the bank and were involved in the dealing of the asset of the bank or assets held in trust by the bank are no longer authorized to give instructions and that only the liquidator and persons authorized by the liquidator have authority to give instructions;

f) suspend the payment of capital distributions in general and payment to key management personnel, and significant shareholders, except the compensation that may be paid to directors or key management personnel; and

g) any action necessary for the efficient exercise of the powers of the liquidator.

፭/ ማንኛውም ንብረት አጣሪ የተሾመበትን ባንክ ቢሮዎች፣ ሀብት፣ የሒሳብ መዛግብት እና ሌሎች መዝገቦች እንዳያገኝ ወይም እንዳይቆጣጠር ሆን ብሎ ያስተጓጎለ ማንኛውም ሰው ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት ቅጣት ይጣልበታል።

፮/ ንብረት አጣሪው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፰(፮) መሠረት ወደ ሌላ ባንክ የሚተላለፉትን ወይም በማጣሪያ የሚሸጡትን የባንኩን ሀብት የሚያሳይ ዝርዝር አዘጋጅቶ የዝርዝሩን ቅጅ ለሕዝብ እይታ ክፍት ያደርጋል።

፯/ ንብረት አጣሪው በአደራ የተቀመጡ ሀብቶችን በሙሉ ለባለቤቶቻቸው ለመመለስና የባንኩን የአደራ ሒሳቦች ለመዝጋት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

፰/ ንብረት አጣሪው በባንኩ መዛግብት መሠረት ማንኛውም ሰው ከባንኩ ስለሚፈልገው ዕዳ የሒሳብ መግለጫ አዘጋጅቶ ይሰጣል፣ ከዚሁ ጋር በማያያዝ በሒሳብ መግለጫው ላይ ተቃውሞ ያለው ማንኛውም ሰው ተቃውሞውን ተገቢ በሆነና ተለይቶ በተገለጸ ጊዜ ውስጥ ለንብረት አጣሪው ማቅረብ እንደሚችል ማሳሰቢያ ይሰጣል።

## ፷. በይገባኛል ጥያቄዎች ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱(፰) ከተመለከተው የተቃውሞ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን በኋላ ባሉት ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ንብረት አጣሪው፦

5/ A person who willfully interferes with the access of a liquidator to or the control of a liquidator over the offices, assets, books of account and other records of a bank for which that person has been appointed, commits an offence and shall be subject to a penalty as provided under Sub-Article (7) of Article 90 of this Proclamation.

6/ The liquidator shall prepare an inventory of assets of the bank that are to be transferred to another bank or liquidated in accordance with Sub-Article (6) of Article 58 of this Proclamation and make a copy of the inventory available for examination by the public.

7/ The liquidator shall take any necessary steps to return all assets held by the bank as a fiduciary to the owners thereof and settle the bank's fiduciary accounts.

8/ The liquidator shall provide to every person a statement of claim shown on the bank's records in favor of that person, together with a notice that any objection to the bank's records in that respect may be filed with the liquidator within a specified reasonable period of time.

## 60. Decision on Claims

1/ Within two months after the last day for filing objections specified in the notice referred to in Sub-Article (8) of Article 59 of this Proclamation, the liquidator shall:

ሀ) በቀረበው የይገባኛል ጥያቄ አግባብነት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው የይገባኛል ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል፤

ለ) እያንዳንዱ ገንዘብ አስቀማጭና ሌላ አበዳሪ ሊከፈለው የሚገባውን የገንዘብ ልክና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩ እና ፷፪ ድንጋጌ መሠረት የክፍያውን ቅደም ተከተል ይወስናል፤ እና

ሐ) የተፈቀዱትን የይገባኛል ጥያቄዎች የሚያሳይ ኘሮግራም ያዘጋጃል።

፪/ ንብረት አጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሐ) የተጠቀሰው ኘሮግራም ለዕይታ የሚቀርብበትን ቀንና ቦታ እንዲሁም በኘሮግራሙ ላይ ተቃውሞ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ የባንኩ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ባሉባቸው አካባቢዎች በሙሉ በሰፊው በሚሰራጭ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጋዜጦች ላይ በሣምንት አንድ ጊዜ ለሦስት ተከታታይ ሣምንታት እንዲሁም በባንኩ ድረ-ገጽ ላይ አሳትሞ ያወጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተጠቀሰው ማስታወቂያ የሚገለጸው ተቃውሞ የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ የመጨረሻው ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከሃያ ቀናት ያነሰ መሆን የለበትም።

፬/ የይገባኛል ጥያቄው ሙሉ በሙሉ ያልተፈቀደለት ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው መረጃ በቀጥታ እንዲደርሰው ንብረት አጣሪው የተቻለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል።

፭/ የማንኛውም የይገባኛል ጥያቄ አግባብነት እና ቅደም ተከተል፣ የባንኩ ሀብት ተሽጦ የሚከፋፈልበት፣ የማንኛውም የባንኩ ደንበኛ

a) reject any claim if he doubts the validity thereof;

b) determine the amount owed to each depositor and other creditor and the priority classification of the claim in line with the provisions of Article 61 and 62 of this Proclamation; and

c) prepare a schedule of allowable claims.

2/ The liquidator shall publish once a week for three consecutive weeks, in one or more newspapers of wide circulation in every locality where the bank has a branch office and on the banks' website, a notice of the date and place where the schedule referred to in Sub-Article 1(c) of this Article shall be available for examination, and the time limit by which any objections to it may be filed.

3/ The time limit to be specified in the notice referred to in Sub-Article (2) of this Article for filing objections may not be less than twenty days from the date of the last publication of the notice.

4/ The liquidator shall make all reasonable efforts to notify directly each person whose claim has not been allowed in full, in order to provide to such person the information referred to in Sub-Article (2) of this Article.

5/ The procedure for determining the validity and priority of a claim, liquidation of the asset of a bank, returning the property of a customer of a

ንብረት የሚመለስበት፣ የፋይናንስ ውሎች ብቁነት እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የሚወሰኑበት ሥነ ሥርዓት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊወሰን ይችላል።

**፷፩. ስለተፈቀዱ የይገባኛል ጥያቄዎች የመጨረሻ ፕሮግራምና ድልድል**

፩/ ማንኛውም የባንኩ ገንዘብ አስቀማጭ፣ ወይም አበዳሪ ወይም ባለአክሲዮን የተፈቀዱ የይገባኛል ጥያቄዎች ፕሮግራም ይዘትን በተመለከተ የሚኖረውን ተቃውሞ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷(፪) መሠረት ይፋ ከተደረገው ተቃውሞ የማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን በፊት በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል።

፪/ ንብረት አጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቃውሞ በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በተቃውሞው ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት።

፫/ ንብረት አጣሪው ተቀባይነት ያገኙ ተቃውሞዎችን መሠረት በማድረግ የመጨረሻውን ፕሮግራም ያዘጋጃል። የመጨረሻውን ፕሮግራም ቅጂ በብሔራዊ ባንክ እንዲጸድቅለት ያቀርባል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የመጨረሻው ፕሮግራም ዝግጅት እንደተጠናቀቀ ንብረት አጣሪው በተቻለ ፍጥነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፪ በተደነገገው መሠረት የመጨረሻውን ድልድል ማድረግ አለበት።

bank, eligible financial contracts and related issues may be determined by National Bank Directive.

**61. Finalization of Schedule of Allowable Claims and Distribution**

1/ Any depositor or creditor or shareholder of the bank may file an objection to the content of the schedule of allowable claims before the final date for objections announced pursuant to Sub-Article (2) of Article 60 of this Proclamation.

2/ Any objection filed in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be decided upon by the liquidator within one month of its filing.

3/ The liquidator shall finalize the schedule based on the accepted objections, and a copy of the finalized schedule shall be submitted for the approval of National Bank.

4/ As soon as the schedule is finalized as provided under Sub-Article (3) of this Article, the liquidator shall make final distribution in accordance with the provisions of Article 62 of this Proclamation.

፷፪. **የይገባኛል ጥያቄዎች አከፋፈል ቅደም ተከተል**

፩/ በማናቸውም የባንክ ንብረት የማጣራት ተግባር በዋስትና የተጠበቁ የይገባኛል ጥያቄዎች ካሉ ከንብረት ማጣራቱ የተገኘው ገቢ ከይገባኛል ጥያቄው ያነሰ ቢሆንም እንኳን በተቻለ መጠን በተገባላቸው ግዴታ መሠረት መከፈል አለባቸው። ሌሎች በባንኩ ጠቅላላ ሀብት ላይ የሚቀርቡ የይገባኛል ጥያቄዎች አከፋፈል በሚከተለው ቅደም ተከተል መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፦

ሀ) ለንብረት አጣሪው የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያና ንብረት አጣሪው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም ያወጣቸው አስፈላጊና አግባብነት ያላቸው ወጪዎች፤ ሆኖም ብሔራዊ ባንክ ንብረት አጣሪ ሆኖ በሚሠራበት ጊዜ የንብረት አጣሪነት ተግባሩን ለመፈጸም ያወጣው ወጪ ብቻ ታስቦ ተመላሽ ይሆንለታል፤

ለ) የሞግዚት አስተዳዳሪው ወይም ንብረት አጣሪው ከተሾመ በኋላ ለባንኩ አዲስ ብድር የሰጡ አበዳሪዎች፤

ሐ) የንብረት አጣሪው ሹመት ከጸናበት ቀን በፊት ባለው የሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ የባንኩን የሥራ አስፈጻሚዎች ሳይጨምር የሠራተኞች ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች፤ ሆኖም የዚህ ዓይነቱ ክፍያ፦

፩/ ጉርሻን ወይም ከሚጠበቀውና ከመደበኛው በላይ የሆኑ ክፍያዎችን፤ ወይም

፪/ የባንኩ ንብረት ይጣራል በሚል ግምት አላግባብ የተጨመሩ ክፍያዎችን፤

62. **Priorities in Payment of Claims**

1/ In any liquidation of the assets of a bank, secured claims, if any, shall be paid in accordance with their terms to the extent of the realization if proceeds are lower than the claim. Other claims shall have priority against the general assets of the bank in the following order:

a) Remuneration of the liquidator and necessary and reasonable expenses incurred by him in implementing the provisions of this Proclamation; provided, however, that in a case where National Bank is the liquidator, it shall be reimbursed only the costs it incurred to carry out the business of liquidation;

b) Creditors who extended new credit to the bank after the appointment of the official administrator or liquidator;

c) Outstanding salaries and other benefits of non-managerial staff of the bank for the three-month period preceding the effective date of liquidation; provided, however, that such payments may not include:

1/ bonuses or payments exceeding the expected and normal amount; or

2/ payments which have been added in anticipation that the bank would be put under liquidation;

አያጠቃልልም፣

መ) ተቀማጭ ገንዘቦች፣

ሠ) ለፌደራልና ለክልል መንግሥታት መከፈል ያለበት ግብር፣

ረ) በባንኩ ላይ የሚቀርቡ ሌሎች የይገባኛል ጥያቄዎች፣

ሰ) ንብረት አጣሪው በሚወስነው ተመን መሠረት በዚህ ንዑስ አንቀጽ በተዘረዘሩት የይገባኛል ጥያቄዎች ላይ የሚከፈል ወለድ።

፪/ ባንኩ ያለው የሀብት መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተዘረዘሩትን የይገባኛል ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ለመክፈል በቂ ሆኖ ሲገኝ፣ ቀሪው ሀብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱(፰) መሠረት በጊዜው ማመልከቻ ላልቀረበባቸውና ተቀባይነት ላላቸው የይገባኛል ጥያቄዎች ክፍያ ይውላል።

፫/ ያለው ገንዘብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው በማንኛውም የቅደም ተከተል ደረጃ ሥር ያሉ የይገባኛል ጥያቄዎችን ሙሉ በሙሉ ለማስተናገድ በቂ በማይሆንበት ጊዜ በዚያ ደረጃ ውስጥ ላሉት የይገባኛል ጥያቄዎች ተመጣጣኝ በሆነ ስሌት መከፈል አለበት።

፬/ ሁሉም ተቀባይነት ያገኙ የይገባኛል ጥያቄዎች ከተከፈሉ በኋላ የሚተርፈው የባንኩ ሀብት በባንኩ ውስጥ ባላቸው የባለቤትነት ድርሻ መሠረት ለባለአክሲዮኖች ይከፋፈላል።

d) deposits;

e) taxes owed to the Federal and Regional Governments;

f) other claims against the bank;

g) interest on claims listed under this Sub-Article at a rate to be fixed by the liquidator.

2/ If the amount available for payment of claims is adequate to pay all claims listed in Sub-Article (1) of this Article, any remaining valid claims, which were not filed within the prescribed time pursuant to Sub-Article (8) of Article 59 of this Proclamation, shall be paid.

3/ If the amount available for payment for any class of claims listed in Sub-Article (1) of this Article is insufficient to provide payment in full, the amount available shall be distributed on a pro-rata basis among the claimants within that class.

4/ any assets remaining after all claims have been paid shall be distributed among the shareholders in proportion to their ownership share in the bank.

**፷፫. ስለንብረት የማጣራት ተግባር መጠናቀቅ**

፩/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የባንኩ ንብረቶች በሙሉ ተሸጠው ከተከፋፈሉ በኋላ ንብረት አጣሪው ንብረት በማጣራት ተግባር ወቅት ስለተከናወኑት ሥራዎች ንብረት የማጣራት ተግባራት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለብሔራዊ ባንክ አቅርቦ ማጸደቅ አለበት። ብሔራዊ ባንክም የጸደቀውን ሪፖርት ወዲያውኑ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀስ (፩) የተመለከተው ሪፖርት ለሕዝብ ይፋ እንደተደረገ ንብረት የማጣራት ተግባሩ እንደተጠናቀቀ ይቆጠራል፤ በመፍረስ ላይ የሚገኘው ባንክም ከንግድ መዝገብ እንዲሰረዝ ንብረት አጣሪው ማመልከቻ ያቀርባል።

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፬ መሠረት ክስ ካልተመሰረተ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ሪፖርት ለሕዝብ ይፋ በተደረገ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ንብረት አጣሪው እና ብሔራዊ ባንክ የባንኩን ንብረት ከማጣራት ጋር ከተያያዙ ማናቸውም ግዴታዎች ነፃ ይሆናሉ።

፬/ ጥያቄ ቀርቦባቸውና ተፈቅደው በጥያቄ አቅራቢዎቹ ያልተሰበሰቡ የይገባኛል ጥያቄዎችን የሚመለከት ገንዘብ ካለ በብሔራዊ ባንክ ይቀመጣል። ሆኖም ብሔራዊ ባንክ የባንኩን ንብረት የማጣራቱ ተግባር ካበቃበት ቀን ጀምሮ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ከተቀመጠው ገንዘብ ጋር በተያያዘ ከማናቸውም የይገባኛል ጥያቄ ነፃ ይሆናል።

**63. Conclusion of Liquidation**

1/ Once all assets of the bank have been disposed of in accordance with the provisions of this Proclamation, the liquidator shall prepare a report on the transactions and liquidations carried out under the liquidation, and submit it to National Bank for approval. The National Bank shall, upon its approval, make the report available for public review.

2/ Where the report referred to in Sub-Article (1) of this Article is made available for public review, the liquidation shall be considered concluded; and the liquidator shall apply for cancellation of the bank under liquidation from the commercial registry.

3/ Unless an action has been filed in accordance with Article 64 of this Proclamation, the liquidator and National Bank shall be relieved of any liability in connection with the liquidation after thirty days from the date on which the account referred to in Sub-Article (1) of this Article has been made available for public review.

4/ Any funds, in respect of which claims were made and allowed but not collected, shall be deposited with the National Bank; provided, however, that the National Bank shall be relieved of any responsibility to the claimants after five years from the end of the liquidation.

፭/ ንብረት አጣሪው በሚከተሉት ሁኔታዎች የባንኩን ንብረት መሸጡን ሊተው ወይም ንብረቱን የህብረተሰብ ጤናን ወይም ትምህርትን ለማስፋፋት ለሚሰራ የተራድኦ ድርጅት በእርዳታ ሊሰጥ ይችላል፦

ሀ) ንብረቱ ቁሳዊ ዋጋ የሌለው ከሆነ፤

ለ) ንብረት አጣሪው ንብረቱን መሸጥ ካልቻለ፤ ወይም

ሐ) ንብረቱን ለመሸጥ የሚወጣው ወጪ ከሽያጩ ይገኛል ተብሎ ከሚጠበቀው ገንዘብ የሚበልጥ ከሆነ።

፮/ ማንኛውም የባንክ አበዳሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በተዘረዘረ ማንኛውም ንብረት ላይ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ አይችልም።

፷፬. <u>በንብረት አጣሪ እርምጃዎች ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ</u>

፩/ ማንኛውም የባንክ ንብረት አጣሪ በወሰደው እርምጃ ላይ እርምጃው በተወሰደ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት የሚከተሉት ሰዎች ብቻ ናቸው፦

ሀ) ከጠቅላላው ተቀማጭ ገንዘብ ቢያንስ ሀያ አምስት በመቶ ድርሻ ያላቸው ሰዎች፣

ለ) ገንዘብ አስቀማጮችን ሳይጨምር፣ በጠቅላላው የይገባኛል ጥያቄ ካላቸው ሰዎች ቢያንስ ሀምሳ በመቶ ያህል ድርሻ ያላቸው አበዳሪዎች፣ ወይም

ሐ) ከጠቅላላው የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ቢያንስ ሀያ አምስት በመቶ ድርሻ የሚወክሉ የባንኩ ባለአክሲዮኖች።

5/ A liquidator may abandon the sale of an asset of a bank or donate the asset to a charitable institution that promotes public health or education, where:

a) the asset is of an immaterial value;

b) the liquidator is unable to sell the asset; or

c) the cost of sale of the asset would exceed the amount expected to be received.

6/ A creditor of a bank shall not have a claim against an asset identified under Sub-Article (5) of this Article.

**64. <u>Review Against Actions of Liquidator</u>**

1/ A request for review against the action of any liquidator may be brought before the Federal High Court within thirty days from the date on which such action has been taken.

2/ A review under Sub-Article (1) of this Article may only be brought by:

a) persons representing at least twenty five percent of the aggregate amounts of deposits;

b) creditors comprising at least fifty percent in value of the aggregate claims of creditors, excluding depositors; or

c) shareholders representing at least twenty five percent in value of the aggregate subscribed capital of the bank.

፫/ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን አቤቱታ ሲመረምር ሊያይ የሚችለው ጭብጥ ንብረት አጣሪው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ተግባሩን ሲፈጽም ፍጹም ተጨባጭነት በሌለው እና ባልተገባ መልኩ የሠራ መሆን አለመሆኑን ብቻ ይሆናል።

፬/ ንብረት አጣሪው ተግባሩን ያከናወነው ፍጹም ተጨባጭነት በሌለው እና ባልተገባ መልኩ ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ የወሰነ እንደሆነ፤ ንብረት አጣሪው ካሣ እንዲከፍል ሊያዘው ይችላል፤ ሆኖም ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው የንብረት አጣሪው ድርጊት የሚለወጥ አይሆንም።

፭/ ንብረት አጣሪው ተግባሩን ያከናወነው ፍጹም ተጨባጭነት በሌለው እና ባልተገባ መልኩ አይደለም ብሎ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ፤ ንብረት አጣሪው ክሱን ለመከላከል ያወጣቸውን ወጪዎች አቤቱታ አቅራቢዎቹ እንዲከፍሉ ያዛል።

**፷፭. <u>በፈቃደኝነት ስለመፍረስ</u>**

፩/ ማንኛውም ባንክ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ ሳያስተላልፍ እና ብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ በጽሑፍ ፈቃድ ሳይሰጥ በፈቃደኝነት ሊፈርስ አይችልም።

፪/ የአንድ ባንክ በፈቃደኝነት መፍረስ በብሔራዊ ባንክ የሚፀድቀው በልዩ ሁኔታ እና ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ በሚወስነው መሠረት ብቻ ነው፡፡

፫/ በብሔራዊ ባንክ መፅደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም ማንኛውም ባንክ እንደ ንብረት አጣሪ ሆኖ ሊሰራ ወይም በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰኑትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሌላ ሰው ሊሾም ይችላል፡፡

3/ The sole issue to be adjudicated by the court in any such review shall be whether the liquidator acted in unrealistic and inappropriate manner in discharging his functions according to the provisions of this Proclamation.

4/ The court may require the liquidator to pay compensation if it determines that he has acted in unrealistic and inappropriate manner, provided, however; that the action being challenged may not be reversed.

5/ If the court determines that the liquidator has not acted in unrealistic and inappropriate manner; it shall order the persons who have brought the action to pay the costs incurred by the liquidator in defending the action.

**65. <u>Voluntary Liquidation</u>**

1/ A bank shall not enter into voluntary liquidation without resolution of general meeting of its shareholders as per relevant laws and prior written approval by National Bank.

2/ Voluntary liquidation of a bank shall only be approved by National Bank in special cases as determined by National Bank Directive.

3/ For the purpose of this Article, a bank, subject to approval by National Bank, may act as liquidator or may appoint any other person fulfilling the requirements to be determined by National Bank Directive.

፬/ በፈቃደኝነት ለመፍረስ የሚያመለክት ማንኛውም ባንክ በሚያመለክትበት ወቅት ለገንዘብ አስቀማጮቹ እና ለሌሎች አበዳሪዎች ያለበትን ዕዳ በሙሉ ለመክፈል የሚያስችል በቂ ሀብት ሊኖረው ይገባል።

፭/ በፈቃደኝነት ለመፍረስ ዕቅድ ያለው ማንኛውም ባንክ ዝርዝር የንብረት ማጣራት ዕቅድ አዘጋጅቶ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት፤ ዕቅዱም ቢያንስ የባንኩ ንብረቶች የሚለዩበትን፣ ዋጋቸው የሚገመትበትን እና ተሸጠው የሚከፋፈሉበትን ሥነ-ሥርዓት፤ ዕዳዎች በሙሉ የሚከፈሉበትን የጊዜ ሰሌዳ እንዲሁም የገንዘብ አስቀማጮችን እና የአበዳሪዎችን የይገባኛል ጥያቄዎች እና የሠራተኞች ደመወዝ ጨምሮ ሌሎች በብሔራዊ ባንክ የሚወሰኑ ጉዳዮችን ያካተተ መሆን አለበት።

፮/ ብሔራዊ ባንክ ባንኩ በፈቃደኝነት እንዲፈርስ በሚፈቅድበት ጊዜ፦

ሀ) ብሔራዊ ባንክ ወዲያውኑ የባንኩን የባንክ ሥራ ፈቃድ ይሰርዛል፤ ሆኖም ግን ንብረት የማጣራቱ ተግባር እስኪጠናቀቅ ድረስ ባንኩ "በመፍረስ ላይ ያለ" የሚለውን ሐረግ በስሙ ላይ በመጨመር የሕግ ሰውነት እንደተሰጠው አካል መንቀሳቀሱን ይቀጥላል፤ እና

ለ) ባንኩ ሥራውን አቁሞ ሥርዓቱን በተከተለ መልኩ ንብረቱን ለማጣራት የሚያስፈልግ ሥልጣኑን ብቻ ተግባራዊ ያደርጋል።

4/ A bank requesting for voluntary liquidation shall have sufficient assets to repay its depositors and other creditors in full at the time of initiating voluntary liquidation.

5/ A bank planning to undergo voluntary liquidation shall develop and submit detailed liquidation plan to National Bank, and the plan shall at a minimum contain procedures for identifying, valuing and disposing the bank's asset, a timeline for settling all liabilities including depositors and creditors claims; employees compensation and others to be determined by National Bank.

6/ When the National Bank approves voluntary liquidation of a bank:

a) National Bank shall immediately revoke its banking business license, but the bank shall continue as legal entity by adding the phrase "Under Liquidation" to its name until the liquidation process is completed; and

b) the bank shall cease its operations and exercise its powers only to activities necessary for its orderly liquidation.

፯/ ማንኛውም ባንክ በፈቃደኝነት ንብረቱ እንዲጣራ በብሔራዊ ባንክ በተፈቀደለት በአንድ ሳምንት ውስጥ በፈቃደኝነት ሊፈርስ መሆኑን በመግለጽ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ ያወጣል እንዲሁም ለእያንዳንዱ ገንዘብ አስቀማጭ እና አበዳሪ ወይም በባንኩ በአደራ፣ በኪራይ ወይም ደህንነቱ በተጠበቀ ሳጥን የተያዘ ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት ላላቸው ሰዎች ለማሳወቅ አግባብ በሆኑ ሌሎች መንገዶች ለሕዝብ ያሳውቃል።

፰/ ማንኛውም ባንክ በፈቃደኝነት እንዲፈርስ በብሔራዊ ባንክ መፈቀዱ መብት ላላቸው ገንዘብ አስቀማጮች ወይም ለሌሎች አበዳሪዎች መደበኛ ክፍያዎችን ሙሉ በሙሉ መፈጸምን እንዲሁም ባንኩ በአደራ፣ በኪራይ ወይም ደህንነቱ በተጠበቀ ሳጥን የያዘውን ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት ለባለቤቱ መመለሱን የሚያስቆም አይሆንም።

፱/ በፈቃደኝነት በመፍረስ ላይ ያለ ማንኛውም ባንክ ሕጋዊ የሆኑ የይገባኛል ጥያቄዎችን በሙሉ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚወሰነው ከፍተኛ የጊዜ ገደብ ውስጥ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፪ መሠረት ወዲያውኑ ይከፍላል።

፲/ በፈቃደኝነት በመፍረስ ላይ ያለ ማንኛውም ባንክ በየጊዜው የአፈፃፀም እና የመጨረሻውን የንብረት ማጣራት ሪፖርት ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ እና ንብረት የማጣራት ሂደቱ መጨረሻ ላይ በብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ማጸደቅ አለበት።

7/ A bank, within one week from the receipt of approval from National Bank, shall publish a notice of voluntary liquidation in a newspaper of wide circulation in Ethiopia and communicate the same to the public via other reasonable means as may be necessary to notify to every depositor and creditor, or persons entitled to any funds or property held by the bank as fiduciary, lessor or safe deposit box.

8/ Approval issued by National Bank for the voluntary liquidation of a bank shall not stop effecting of the regular payments to the rightful depositors or others creditors in full of a claim, nor handing over of the funds or property held by the bank as fiduciary, lessor or safe deposit box to the rightful owners.

9/ A bank shall settle all lawful claims promptly within a maximum period to be set by National Bank Directive and in line with Article 62 of this Proclamation.

10/ A bank shall prepare and submit periodic progress and final liquidation report and shall secure written approval from National Bank at the end of the liquidation process.

፲፩/ ብሔራዊ ባንክ የንብረት ማጣራት ሪፖርቱን ከማጽደቁ በፊት የባንኩን ንብረት የማጣራት ሂደት በዝርዝር መርምሮ በዚህ አዋጅ እና በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት።

፲፪/ ባንኩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፪ ሕጋዊ የሆኑ የይገባኛል ጥያቄዎችን በሙሉ በጊዜአቸው ስለመፈጸሙ ማረጋገጫ መፈረም አለበት።

፲፫/ ለማንኛውም ገንዘብ አስቀማጭ ወይም ሌላ አበዳሪ መከፈል ያለበት ሆኖ ጥያቄ ባለመቅረቡ የተነሣ ያልተከፈለ ማንኛውም ገንዘብ የንብረት ማጣራት ሪፖርቱ ከጸደቀበት ቀን አንሥቶ በሁለት ወራት ውስጥ በብሔራዊ ባንክ መቀመጥ አለበት።

፲፬/ ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት ለብሔራዊ ባንክ ከተላለፈበት ቀን አንሥቶ በሰባት ዓመታት ውስጥ በሚመለከተው ሰው ካልተጠየቀ እንደተተወ ይቆጠራል።

፲፭/ ባንክ በፈቃደኝነት የሚፈርስባቸውን ተጨማሪ ሁኔታዎች እና መስፈርቶች ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

## ፷፮. <u>ስለሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት</u>

የንግድ ሕግና አግባብነት ያላቸው ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ ድረስ በሞግዚት አስተዳደር እና በመፍረስ ላይ ባሉ ባንኮች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

11/ The National Bank, before approving the liquidation report, shall conduct detailed examination on liquidation process of the bank and ensure that it is done in line with this Proclamation and Directive issued by National Bank.

12/ A bank shall sign undertaking that it has settled all lawful claims promptly in line with Article 62 of this Proclamation.

13/ Any fund payable to a depositor or other creditor that has not been claimed shall be deposited with the National Bank within two months from the date of approval of the liquidation report.

14/ Any fund or property not claimed within seven years from the date of transfer to the National Bank shall be assumed to be abandoned.

15/ National Bank may determine additional conditions and requirements for voluntary liquidation of a bank by a Directive.

## 66. <u>Applicability of Other Laws</u>

The provisions of the Commercial Code and other relevant laws shall be applicable with respect to official administration and liquidation of banks in so far as they are not inconsistent with the provisions of this Part.

## ክፍል አሥራ አንድ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፷፯. ተቀጥላ ስለማቋቋም**

፩/ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ባንክ ተቀጥላ እንዲያቋቁም ሊፈቅድ ይችላል።

፪/ ማንኛውም ባንክ ተቀጥላ ማቋቋም የሚችልባቸው ሁኔታዎችና መስፈርቶች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል።

**፷፰. ልዩ ባንክ ስለማቋቋም**

፩/ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ልዩ ባንክ እንዲቋቋም ወይም ማንኛውም ልዩ ባንክ ወደ መደበኛ ዓይነት ባንክ ወይም ከመደበኛ ዓይነት ባንክ ወደ ልዩ ባንክ እንዲቀየር ሊፈቅድ ይችላል።

፪/ ማንኛውም ልዩ ባንክ አግባብነት ያላቸው የባንክ ሥራ ሕጎችን እና የቁጥጥር ሥርዓቶች ማክበር አለበት።

፫/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የማንኛውንም ልዩ ባንክ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ቁጥጥር እና የሥራ ዘርፎች የተመለከቱ ሁኔታዎች እና መስፈርቶች ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

**፷፱. ዕዳ መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ ስለደረሰ ባንክ**

ማናቸውም ዕዳ መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ የደረሰ ባንክ ተቀማጭ ገንዘብ መሰብሰብ አይችልም።

**፸. የባንክ ባልሆኑ ሥራዎች ስለመሰማራት**

፩/ ማንኛውም ባንክ የባንክ ባልሆኑ ሥራዎች ላይ መሠማራት አይችልም።

## PART ELEVEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**67. Establishment of Subsidiary**

1/ National Bank may allow a bank to establish a subsidiary.

2/ The conditions and requirements under which a bank may establish subsidiary shall be determined by a Directive to be issued by National Bank.

**68. Establishment of a Specialized Bank**

1/ National Bank may allow for the establishment of a specialized bank; or the conversion of a specialized bank to conventional bank or vice versa.

2/ A specialized bank is required to comply with relevant banking laws and supervisory framework, as appropriate.

3/ Without prejudice to the provisions of this Proclamation; National Bank may issue Directive to prescribe conditions and requirements for the licensing, supervision and areas of business operation of a specialized bank.

**69. Insolvent Bank**

Any insolvent bank shall not accept deposits.

**70. Engagement in Non-Banking Undertakings**

1/ A bank shall not engage in non-banking undertaking.

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚወሰኑ ዝርዝር ሁኔታዎች መሠረት ብሔራዊ ባንክ በልዩ ሁኔታ ባንኮች የባንክ ባልሆኑ ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ሊፈቅድ ይችላል።

**፸፩. ስለምርመራ አገልግሎት ክፍያ**

ብሔራዊ ባንክ ለዚሁ ዓላማ ሲባል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በቦታው በመገኘት እና በቦታው ሳይገኝ በባንክ ላይ ለሚያካሂደው ምርመራ የሚያወጣውን ወጪ ቁጥጥር የሚያደርግበት ባንክ እንዲሸፍን ሊያደርግ ይችላል።

**፸፪. የይገባኛል ጥያቄ ስላልቀረበባቸው ተከፋይ ሒሳቦች**

፩/ ለ፲፭ ተከታታይ ዓመታት የይገባኛል ጥያቄ ያልቀረበበትን፣ በዋናው ገንዘብ ላይ የመጨመር ወይም የመቀነስ እንቅስቃሴ ያልታየበትን፣ የባንክ ደብተር ወይም ሌላ የጽሑፍ መረጃ ያልቀረበበትን ወይም ማንኛውም አይነት ልውውጥ ያልተደረገበትን ተከፋይ ሒሳብ የያዘ ማንኛውም ባንክ በዚሁ ሒሳብ ውስጥ ያለውን ገንዘብ ለብሔራዊ ባንክ ማስተላለፍ አለበት።

፪/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሊተላለፍለት የሚገባውን ዝቅተኛ የገንዘብ መጠንና ባንኮች የዚህ አይነቱን ገንዘብ ሲያስተላልፉ ሊከተሉ የሚገባቸውን ሥርዓት በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል።

፫/ ማንኛውም ባንክ የይገባኛል ጥያቄ ያልቀረበበትን ተከፋይ ገንዘብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለብሔራዊ ባንክ ካስተላለፈበት ቀን ጀምሮ በዕዳው ከመጠየቅ ሙሉ በሙሉ ነፃ ይሆናል።

2/ Notwithstanding to Sub-Article (1) of this Article, National Bank my allow banks to engage in non-banking undertaking on exceptional basis subject to specific conditions to be determined by National Bank Directive.

**71. Examination Fee**

National Bank, in accordance with a Directive to be issued for this purpose, may require a bank under its supervision to cover the cost of off-site and on-site examination.

**72. Unclaimed Liabilities**

1/ A bank holding any account of liabilities which have not been claimed, the principal balance of which has not increased or decreased, for which pass-book or other records have not been presented or any correspondence has not been made, for fifteen consecutive years shall transfer the fund in such account to the National Bank.

2/ National Bank shall determine by Directive, the minimum amount of fund to be transferred to it in accordance with Sub-Article (1) of this Article and the procedures to be followed by banks in transferring such funds.

3/ A bank shall, upon the date of transferring unclaimed funds to the National Bank in accordance with Sub-Article (1) of this Article, be fully relieved of such liabilities.

፬/ ማንኛውም ሕጋዊ ባለመብት ጥያቄ ካቀረበ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተላለፈውን ሙሉውን ገንዘብ ለባለመብቱ መክፈል አለበት፣ ሆኖም በእንደዚህ ዓይነት የይገባኛል ጥያቄዎች ላይ ብሔራዊ ባንክ ወለድ አይከፍልም።

፭/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተላለፉትንና በሕጋዊ ባለመብቱ ጥያቄ ያልቀረበበትን ገንዘብ አጠቃቀም በመመሪያ ይወስናል።

**፸፫. የደንበኞችን ማንነት ማወቂያ መስፈርቶች**

ባንኮች የደንበኞቻቸውን ማንነት በቀጣይነት ተከታትለው የሚያውቁባቸውንና አጠራጣሪ የሒሳብ እንቅስቃሴዎችን ሪፖርት የሚያደርጉባቸውን መስፈርቶች ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

**፸፬. የባንኮችና የመድን ሰጪ ኩባንያዎች ግንኙነት**

፩/ ብድር መስጠትን፣ ተቀማጭ ገንዘብ መቀበልንና የባንክና የመድን አገልግሎቶችን ጨምሮ በባንኮችና በመድን ሰጪ ኩባንያዎች መካከል የሚደረጉ የሥራ ግንኙነቶች በማናቸውም ረገድ ከሌላ ማንኛውም ሰው ጋር ከሚደረጉት የሥራ ግንኙነቶች ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ሁኔታዎች መደረግ አለባቸው።

፪/ በባንኮችና በመድን ሰጪ ኩባንያዎች መካከል የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት በሚመለከት ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

4/ If claimed by any rightful person, National Bank shall pay to such person full amount of the claim transferred to it under Sub-Article (1) of this Article; provided, however, that it shall pay no interest on such claims.

5/ National Bank shall determine by a Directive the use of funds transferred to it under Sub-Article (1) of this Article and not claimed by the rightful person.

**73. Know-Your-Customer Standards**

The National Bank may issue a Directive prescribing standards on a bank's due diligence in knowing its customers and reporting of suspicious transactions.

**74. Relation Between Banks and Insurance Companies**

1/ Transactions, including the provision of loans, the acceptance of deposits and the provision of banking and insurance services, between a bank and an insurance company shall be undertaken on the same terms and conditions as provided to any other person.

2/ National Bank may issue, from time to time, a Directive that governs relationships between a bank and an insurance company.

**፸፭. የደህንነት እርምጃዎች እና የመረጃ አስተዳደር**

፩/ የደንበኞችን መረጃ ሚስጥራዊነት፣ ምሉዕነትና ዝግጁነት ለመጠበቅ ሲባል ማንኛውም ባንክ ሁሉን አቀፍ የሆነ የመረጃ ደህንነት ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ እና መያዝ አለበት፤ ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

ሀ) የደንበኞች መረጃ ካለፈቃድ እንዳይገኝ፣ ይፋ እንዳይሆን፣ እንዳይለወጥ ወይም እንዳይጠፋ አግባብነት ያላቸው አካላዊ፣ ምክንያታዊ እና አስተዳደራዊ የመከላከያ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣

ለ) ደረጃውን የጠበቀ የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ጣቢያ መያዝ፤ እና

ሐ) በባንኩ ሥርዓት ላይ ያሉ ለጥቃት ተጋላጭ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ለመለየት እና ለመፍታት የደህንነት ግምገማዎችን እና ዘልቆ የመግባት ሙከራዎችን በመደበኛነት ማከናወን።

፪/ የማንኛውም ባንክ የሥራ ቦታ እና የመረጃ ቋት ላይ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገቡ ዝቅተኛ የደህንነት እርምጃዎችን፣ የደንበኞችን መረጃ ባለቤትነት እና የደንበኞች መረጃ አያያዝ ሁኔታ በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

**፸፮. በቋሚ ንብረቶች እና በፋይናንስ ሀብት ላይ ስለሚደረግ ኢንቨስትመንት**

ማንኛውም ባንክ በቋሚ ንብረት እና በፋይናንስ ሀብት ላይ የሚያደርገው ኢንቨስትመንት ጣሪያ፣ ስብጥር እና ሌሎች ሁኔታዎች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊወሰን ይችላል።

**75. Security Measures and Data Management**

1/ In order to protect the confidentiality, integrity, and availability of customer data, a bank shall implement and maintain a comprehensive data security program, including:

a) maintenance of appropriate physical, logical, and administrative safeguards to prevent unauthorized access, disclosure, alteration, or destruction of customer data;

b) maintenance of standard disaster-recovery site; and

c) regularly conducting security assessments and penetration testing to identify and address vulnerabilities in the bank's system.

2/ National Bank may determine by a Directive the minimum security measures to be taken on a bank's physical premise and its database, ownership of customer's data and manner of storage of customer's information.

**76. Investment in Fixed and Financial Assets**

The maximum limit, composition and other conditions of investment in fixed and financial assets by a bank may be determined by National Bank Directive.

**፸፯. <u>በባንክ ስለሚደረግ ማስታወቂያ</u>**

፩/ ብሔራዊ ባንክ የማንኛውም ባንክ የሬድዮ ወይም የቴሌቪዥን ማስታወቂያ፣ ዲጂታል ማስታወቂያ፣ ፖስተር፣ ቢል ቦርድ፣ በራሪ ወረቀት፣ ሠርኩላር ወይም ሌላ ሰነድ እና የጋዜጣና የመጽሔት ማስታወቂያ ሐሰተኛ፣ አሳሳች፣ አደናጋሪ፣ አጸያፊ ወይም የማንኛውንም ባንክ ወይም የባንክ ሥርዓቱን ደኅንነትና ጤናማነት የሚጎዳ ነው ብሎ ካመነ በማንኛውም ጊዜ ባንኩ ማስታወቂያውን እንዲያቋርጥ፣ እንዲያሻሽል ወይም ከማስተዋወቅ እንዲቆጠብ ሊያደርግ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በባንክ የሚደረግ ማስታወቂያን የሚመለከቱ ሌሎች ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ሊወሰኑ ይችላሉ።

**፸፰. <u>በብድር እና በውጭ አገር ገንዘብ ላይ ስለሚጣል የፖርትፎሊዮ ገደብ</u>**

ብሔራዊ ባንክ አንድ ባንክ የሚሰጠውን ብድር እና የውጭ አገር ገንዘብ ፖርትፎሊዮ ድልድል ገደቦችን በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**፸፱. <u>ድንበር ተሻግሮ ስለመበደር፣ ስለማበደር እና ኢንቨስት ስለማድረግ</u>**

፩/ ማንኛውም ባንክ ከውጭ ምንጮች እንዲበደር ሊፈቀድለት ይችላል፤ እንዲህ ያሉ የብድር ሁኔታዎችን በተመለከተ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

፪/ በብሔራዊ ባንክ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደለት በስተቀር ማንኛውም ባንክ ድንበር ተሻግሮ የማበደር ወይም የኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ መሰማራት አይችልም።



**77. <u>Advertisement by a Bank</u>**

1/ National Bank may, at any time, direct a bank to withdraw, amend or refrain from announcing radio or television advertisement, digital advertisement, a poster, billboard, brochure, circular, or other document, and advertisement in a newspaper or magazine that it considers to be false, misleading, deceptive, offensive or detrimental to the safety and soundness of a bank or banking system.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article; other conditions of advertisement by a bank may be determined by National Bank Directive.

**78. <u>Loan and Foreign Currency Portfolio Limits</u>**

National Bank may issue a Directive on loan and foreign currency portfolio allocation limits of a bank.

**79. <u>Cross Border Borrowing, Lending and Investment</u>**

1/ A bank may be allowed to borrow from foreign sources, and conditions for such borrowings shall be determined by National Bank Directive.

2/ A bank, unless exceptionally permitted by the National Bank, shall not engage in cross border lending or investment activities.

**፹. የባንክ ሥራዎችን በውጭ አካላት ስለማሠራት**

ባንኮች ሥራዎቻቸውን በውጭ አካላት የሚያሠሩባቸው ዝቅተኛ ሁኔታዎች እና መስፈርቶች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**፹፩. የባንክ አገልግሎቶችን ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እና ምቹ ስለማድረግ**

፩/ ማንኛውም ባንክ ለአካል ጉዳተኛ ደንበኞች ተደራሽ እና ምቹ የባንክ አገልግሎት ማቅረብ ይኖርበታል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ የባንክ አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እና ምቹ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መመሪያ ያወጣል።

**፹፪. ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት**

፩/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች የተቀመጡ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ከወለድ ነጻ የባንክ ሥራ ለሚሠራ ባንክ ፈቃድ የሚሰጥበትን እና ቁጥጥር የሚያከናውንበትን ተጨማሪ ሁኔታዎችና መስፈርቶች የሚወስንበት እንዲሁም ከመደበኛው የባንክ አገልግሎት በተለየ መልኩ የወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት ያሉትን ልዩ ባህሪያት እና አሰራሮች አስመልክቶ ለወለድ ነጻ ባንኮች እና ከወለድ ነጻ አገልግሎት መስኮት የሚሰጡ ባንኮችን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ያወጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማዕከላዊ የሸሪዓ ቦርድ ማቋቋምን ጨምሮ የወለድ ነፃ ባንክን አጠቃላይ የሸሪዓ አስተዳደር ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣል።

**80. Outsourcing Banking Activities**

The minimum conditions and requirements for outsourcing of activities by a bank shall be determined by National Bank Directive.

**81. Accessibility and Suitability of Banking Services for Persons with Disabilities**

1/ A bank shall provide accessible and suitable banking services for persons with disabilities.

2/ National Bank shall issue a Directive to ensure accessibility and suitability of banking services for persons with disabilities.

**82. Interest Free Banking Service**

1/ Without prejudice to the requirements specified under the provisions of this Proclamation, the National Bank shall issue Directive to prescribe additional conditions and requirements for the licensing and supervision of an interest free bank and for supervising an interest free bank and a bank providing interest free banking window service in respect of the peculiar nature and modality of interest free banking service from that of conventional banking service.

2/ Notwithstanding to Sub-Article (1) of this Article, National Bank shall issue Directive for regulating the overall sharia governance framework of interest free banking business, including establishment of central sharia board.

**፹፫. ለፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ስለሚደረግ ጥበቃ**

ባንኮች ለፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ማድረግ ያለባቸውን ጥበቃ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የተመለከቱ ዝቅተኛ መስፈርቶች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ይወሰናል።

**፹፬. ከውጭ አገር እና የአገር ውስጥ መሰል ባለሥልጣን አካላት ጋር ተባብሮ እና ተቀናጅቶ ስለመሥራት**

፩/ የሚከተሉትን ተግባራት ለመፈጸም ብሔራዊ ባንክ ከማናቸውም የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ተቆጣጣሪ፣ እልባት ሰጪ ወይም የገንዘብ ባለሥልጣን አካላት ጋር ለመቀናጀት፣ ለመተባበር እና መረጃ ለመለዋወጥ የስምምነት ውል እንደ አግባብነቱ ከሚመለከተው የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ጋር በመመካከር ሊፈራረም ይችላል:-

ሀ) የባንክ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የተጠናከረ ቁጥጥር፣ የቅድመ መፍትሔ እርምጃዎች እና እልባት ለመስጠት የሚያስፈልጉ መረጃዎች ለማግኘት፤

ለ) በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጠው የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ ወይም ተቀጥላ ወይም በውጭ ሀገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ባንክ ቅርንጫፍ ወይም ተቀጥላ ላይ ምርመራ ለማካሄድ፤

ሐ) የጋራ ቁጥጥር ማዕቀፍ ውስጥ መቀመጫ ለመያዝ፤

መ) የብሔራዊ ባንክ ወይም የሚመለከተው መሰል ባለሥልጣን ተግባራት አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ የሚችል ማንኛውም እርምጃ በማንኛውም ባንክ ወይም ቅርንጫፍ ላይ ከመውሰድ በፊት ለማሳወቅ ወይም ለመቀናጀት፤ እና

**83. Protection of Financial Service Consumers**

Minimum conditions for financial service consumers' protection by banks and other related issues shall be determined by National Bank Directive.

**84. Cooperation and Coordination with Similar Cross-Border and Domestic Authorities**

1/ The National Bank, in consultation with relevant Government bodies as appropriate, may conclude an agreement with domestic or foreign regulatory, resolution, or monetary authority for the purpose of coordinating, cooperating, and exchanging information concerning any of the following matters:

a) to gain information necessary for the licensing, consolidated supervision, early intervention measures, and the resolution of a bank;

b) performing examination at a foreign bank branch or subsidiary licensed by the National Bank, or the branch or subsidiary of an Ethiopian bank abroad;

c) taking seat in supervisory colleges;

d) coordination or prior notification before taking in respect of any bank or branch any action that may affect the fulfillment of the duties of the National Bank or a counterpart authority; and

ሠ) የፋይናንስ ቀውስ ሁኔታን ለማስተዳደር በብሔራዊ ባንክ እና በሚመለከታቸው መሰል ባለሥልጣናት የሚወሰዱ እርምጃዎች እንዲቀናጁ ለማስቻል፡፡

፪/ ማንኛውም ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ ሀገር ባለሥልጣን የተወሰደ ወይም ለሌላ አካል የተላለፈ መረጃ ለታለመለት ዓላማ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።

፫/ በሕግ አስገዳጅነት ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በፍርድ ሂደት ውስጥ የብሔራዊ ባንክን ጥቅም ለማስጠበቅ ካልሆነ በስተቀር ብሔራዊ ባንክ ከውጭ ባለሥልጣን የተገኘ ማንኛውንም ሚስጥራዊ መረጃ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ውጭ ለሌላ ማንኛውም አካል አሳልፎ መስጠት አይችልም።

**፹፭. <u>ዓለም አቀፍ የባንክ ሥራ ቁጥጥር መርሆዎችን እና ደረጃዎችን በሥራ ላይ ስለማዋል</u>**

ብሔራዊ ባንክ የባዝል ኮሚቴ የባንክ ሥራ ቁጥጥር መርሆዎች እና ደረጃዎችን እንዲሁም የኢትዮጵያን የባንክ ሥርዓት ደህንነት፣ ጤናማነት እና መረጋጋት ያጎለብታሉ ተብለው የሚታመኑ ሌሎች ዓለም አቀፍ የባንክ ሥራ ቁጥጥር ደረጃዎችን በሥራ ላይ ለማዋል መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**፹፮. <u>መረጃዎች እንዲታተሙ ስለማድረግ</u>**

ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበን ወይም የተሰበሰበን ማናቸውንም መረጃ ወይም አሀዞች በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ አግባብ ነው ብሎ ባመነበት አቀራረብ እና ጊዜ አሳትሞ ሊያወጣ ይችላል፤ ሆኖም የባንክ ሥርዓቱን ጤናማነት ለማጠናከር ሲባል የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር፣ የማንኛውንም ባንክ ወይም የባንክ ደንበኛ ዝርዝር መረጃ ይፋ ሊያደርግ አይችልም።

e) the coordination of measures by the National Bank and its counterpart authorities to manage a financial crisis.

2/ Any information received from or shared with a domestic or foreign authority may only be used for the purpose that such information is provided for.

3/ National Bank may not disclose any confidential information received from a foreign authority to any other body without the prior consent of the foreign authority, unless such disclosure is required by law or ordered by court or to protect the National Bank's interests in legal proceedings.

**85. <u>Implementation of International Banking Supervision Principles and Standards</u>**

National Bank may issue Directives to implement Basel Committee for Banking Supervision Principles and Standards; and other international standards on banking supervision that are supposed to enhance safety, soundness and stability of Ethiopian banking system.

**86. <u>Publication of Information</u>**

National Bank may publish, in whole or in part, in such form and at such time as it may consider fit, any information or data furnished or collected under this Proclamation; provided, however, that no information or data may be published that might disclose the particular affairs of a bank or of a customer of a bank, unless such publication is in the interest of strengthening the financial soundness of the banking system.

**፹፯. <u>የብሔራዊ ባንክ የቦርድ አባላት፣ ሠራተኞች እና ተወካዮችን ከግል ተጠያቂነት ስለመጠበቅ</u>**

፩/ ይህን አዋጅ እና ከብሔራዊ ባንክ ሥልጣን እና ተግባራት ጋር የተያያዙ ሌሎች ሕጎችን ለማስፈጸም ሲባል ማንኛውም የብሔራዊ ባንክ የቦርድ አባል፣ ሠራተኛ ወይም ተወካይ በቅን ልቦና ለሚፈጽሙት ማናቸውም ድርጊት በግል በዕዳ ሊጠየቁ ወይም ማናቸውም ሌላ ጥያቄ ሊቀርብባቸው አይችልም። ይህ ድንጋጌ በማንኛውም የብሔራዊ ባንክ የቀድሞ ገዥ፣ ምክትል ገዥ፣ የቦርድ አባል፣ ሠራተኛ ወይም ተወካይ ላይ እኩል ተፈጻሚነት አለው።

፪/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻፀም ሲባል በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ(፩) ሥር የተዘረዘሩ ሰዎች ግዴታቸውን በሚወጡበት ወቅት በፈጸሙት ወይም ባልፈጸሙት ድርጊት የቀረበባቸውን ክስ ወይም ጥያቄ ለመከላከል ያወጧቸው ሕጋዊ ወጪዎች መልሶ ይከፈላቸዋል፤ ሆኖም ግን ይህ የሚሆነው ግዴታቸውን በቅን ልቦና እንዳልተወጡ የሚያረጋግጥ የመጨረሻ የፍርድ ቤት ውሳኔ ካልተሰጠ ነው።

**፹፰. <u>ለባንክ የሥራ አስፈጻሚዎች የሚፈጸም ክፍያ</u>**

ጤናማ ያልሆነ እና ለአደጋ የተጋለጠ አሠራርን ለመቅረፍ እና የባንኮችን አስተማማኝነት እና ጤናማነት ለማስጠበቅ ለባንክ ሥራ አስፈጻሚዎች የሚፈጸም የክፍያ አስተዳደር፣ አሠራር እና አወቃቀር ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ብሔራዊ ባንክ ሊያወጣ ይችላል።

**87. <u>Protection of Board Members, Employees and Agents of the National Bank from Personal Liability</u>**

1/ Any board member, employee or agent of the National Bank may not be subject to any personal liability or any other claim for their bona fide acts done for the purpose of carrying out this Proclamation and other laws related to the authority and functions of the National Bank. This provision equally applies to any former Governor, Vice Governor, board member, employee or agent of the National Bank.

2/ For the purpose of this Article, the persons mentioned under Sub-Article (1) of this Article shall be entitled to be indemnified for legal expenses incurred by them while defending against a lawsuit or claim for their actions or inactions in the discharge of their duties, provided that no final court ruling has ascertained they did not act in a bona fide manner.

**88. <u>Remuneration of Bank Executives</u>**

In order to address imprudent and risky behavior and ensure safety and soundness of banks, the National Bank, through a Directive, may regulate the governance, arrangement and structure of bank executive's remuneration.

**፹፱. የሙከራ የቁጥጥር ማዕቀፍ ተግባራዊ ስለማድረግ**

፩/ የፋይናንስ ፈጠራን እና የፋይናንስ አካታችነትን ለማጎልበት ሲባል ብሔራዊ ባንክ አዲስ እና ፈጠራ የታከለባቸው የባንክ አገልግሎቶችን ለመሞከር እና ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግበት እና በጊዜ የተገደበ የሙከራ የቁጥጥር ማዕቀፍ ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ በሙከራ የቁጥጥር ማዕቀፉ ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስችሉ የብቁነት መስፈርቶችን፣ የማመልከቻ ሂደትን እና ሌሎች ተጨማሪ ሁኔታዎችን በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

**፺. ቅጣት**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫(፩) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው የጥፋት ድርጊቱ ለቀጠለበት ለእያንዳንዱ ቀን በብር ፳ሺ መቀጫ እና ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫(፭) የተዘረዘሩትን ሰነዶች እንዲያቀርብ በብሔራዊ ባንክ ተጠይቆ ያላቀረበ ወይም እምቢተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው ከብር ፶ሺ እስከ ብር ፻ሺ በሚደርስ መቀጫ እና ከ፯ እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ጥፋት የተፈጸመው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት ከሆነ የእሥራት ቅጣቱ ተፈጻሚ የሚሆነው በሚመለከተው የባንኩ ወይም የድርጅቱ ኃላፊ(ዎች) ላይ ይሆናል።

**89. Implementation of Regulatory Sandbox**

1/With the objective of fostering financial innovation and promoting financial inclusion, National Bank may establish and implement a regulatory sandbox framework that will enable testing and introduction of new and innovative banking services and products to the market.

2/ National Bank may issue a Directive to determine eligibility criteria, application process, and other additional conditions for participation in the regulatory sandbox.

**90. Penalties**

1/ Any person who contravenes the provisions of Sub-Article (1) of Article 3 of this Proclamation shall be punished with a fine of Birr 20,000 in respect of each day on which the contravention continues and with a rigorous imprisonment from 10 to 15 years.

2/ Any person who, having been called upon by the National Bank under Sub-Article (5) of Article 3 of this Proclamation, and fails or refuses to submit the documents described therein shall be punished with a fine from Birr 50,000 to Birr 100,000 and with a rigorous imprisonment from 7 to 10 years.

3/ Where the offence under Sub-Article (1) or (2) of this Article is committed by a legal entity, the penalty of imprisonment shall be imposed on the relevant official/s of the bank or institution.

፬/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) ወይም አንቀጽ ፲፱ ድንጋጌዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከብር ፶ሺ እስከ ብር ፻ሺ በሚደርስ መቀጫ እና ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፭/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፳፱(፮) ድንጋጌ የተላለፈ ማናቸውም የባንክ ዳይሬክተር ከብር ፶ሺ እስከ ብር ፻ሺ በሚደርስ መቀጫ እና ከ፯ እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፮/ ማንኛውም የባንክ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ፡-

ሀ) ማንኛውም ኦዲተር በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መፈጸም እንዳይችል ወይም በብሔራዊ ባንክ ሥልጣን የተሰጠው ተቆጣጣሪ በባንኩ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዳያካሂድ እንቅፋት ከሆነ፤ ወይም

ለ) ለማታለል በማሰብ የሐሰት ወይም አሳሳች መግለጫ የሰጠ ወይም በባንኩ መዝገብ፣ ሒሳብ፣ ሪፖርት ወይም መግለጫ ውስጥ የመዘገበ እንደሆነ ወይም መመዝገብ የነበረበትን መግለጫ ወይም መረጃ ሳይመዘግብ የቀረ እንደሆነ፤

ሐ) ባንኩ ዕዳ መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ተቀማጭ ገንዘብ የተቀበለ ወይም ሌላ ሰው እንዲቀበል ያዘዘ ወይም የፈቀደ እንደሆነ፤

ከብር ፶ሺ እስከ ብር ፻ሺ በሚደርስ መቀጫ እና ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

4/ Any person who contravenes the provisions of Sub-Article (1) or (2) of Article 18 or Article 19 of this Proclamation shall be punished with a fine from Birr 50,000 to Birr 100,000 and with a rigorous imprisonment from 10 to 15 years.

5/ Any director of a bank who contravenes the provisions of Sub-Article (6) of Article 29 of this Proclamation shall be punished with a fine from Birr 50,000 to Birr 100,000 and with a rigorous imprisonment from 7 to 10 years.

6/ Any director or employee of a bank who:

a) obstructs the proper performance by an auditor of his duties in accordance with the provisions of this Proclamation or examination of a bank by an examiner duly authorized by the National Bank; or

b) with intent to deceive, makes any false or misleading statement or entry or omits any statement or entry that should be made in any book, account, report or statement of a bank;

c) knows or ought to know the insolvency of the bank and receives or authorizes or permits the acceptance of a deposit;

shall be punished with a fine from Birr 50,000 to Birr 100,000 and with a rigorous imprisonment from 10 to 15 years.

፯/ ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈጻጸማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ እስከ ብር ፶ሺ በሚደርስ መቀጫና እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።

**፺፩. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል።

**፺፪. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

በዚህ አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ (በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፱/፪ሺ፲፩ በተሻሻለው) መሠረት አክሲዮን ገዝተው የነበሩ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጭ ሀገር ዜጎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት እንደ ሀገር ውስጥ ኢንቨስተር የመቆጠር መብት አላቸው።

**፺፫. <u>የማቆያ ድንጋጌ</u>**

በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ (በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፱/፪ሺ፲፩ በተሻሻለው) መሠረት እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ብሔራዊ ባንክ ያወጣቸው በሥራ ላይ ያሉ መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የማይቃረኑ እስከሆኑ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል። እነዚህ መመሪያዎች አስፈላጊው ማሻሻያ እስኪደረግባቸው ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

7/ Any person who contravenes or obstructs the provisions of this Proclamation or Regulations or Directives issued to implement this Proclamation shall be punished with a fine up to Birr 50,000 and with an imprisonment up to 3 years.

**91. <u>Power to Issue Regulation and Directive</u>**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The National Bank may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulation issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

**92. <u>Transitional Provision</u>**

Notwithstanding the provisions of this Proclamation, Foreign Nationals of Ethiopian Origin who have acquired shares in bank in accordance with Banking Business Proclamation No 592/2008 (As amended by Proclamation No 1159/2019) shall be entitled to be treated as a domestic investor, in accordance with relevant laws.

**93. <u>Saving Provision</u>**

Existing Directives issued by the National Bank under the Banking Business Proclamation No. 592/2008 (as amended by Proclamation No. 1159/2019) and other relevant laws in so far as they are consistent with this Proclamation shall remain in effect. These Directives will continue to apply until necessary amendments are made accordingly.

**፺፬. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩/ የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ እና የባንክ ሥራ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፱/፪ሺ፲፩ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

፪/ በኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር ፬፻፸፬/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፬(፩) ላይ ስለባንክ የተደነገገው በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፫/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በንግድ ሕግ፣ በመንግሥት የልማት ድርጅት አዋጅ ወይም በሌሎች ሕጎች መሠረት ሊፈጸሙ ከሚገባቸው ግዴታዎች ይህ አዋጅ ማንኛውንም ባንክ ነጻ አያደርግም።

**፺፭. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት ፫ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀ ሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

**94. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

1/ Banking Business Proclamation No. 592/2008 and Banking (Amendment) Proclamation No. 1159/2019 are hereby repealed.

2/ Issues related to bank in Sub-Article 4 (1) of the Investment Regulation No. 474/2020 are hereby repealed.

3/ No law, Regulation, Directive or practice may, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

4/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (3) of this Article, nothing in this Proclamation shall be construed so as to relieve a bank from compliance with the provisions of the Commercial Code, the Public Enterprises Proclamation or other relevant laws, as appropriate.

**95. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 12th Day of March, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ